
# አውራምባ ታይምስ


በመረጃ ቅርብ ይሁኑ

3ኛ ዓመት ቁጥር 123 ሐምሌ 03 ቀን 2002 ዋጋ 5.00 ብር

«ኦ! ያያያ
መድረክ እና መኢአድ
ወደ ሰበር አመሩ»
አቤ ቶኪቻው
9

አሜሪካ አጥብቃ
የምትደግፋቸው ሁለት
አዳዲስ ሀሳቦች
በዶናልድ ቡዝ (አምባሳደር)
7



# ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ሐውልት በስተጀርባ

ገፅ 4 እና 10

- «የሐውልቱ መተከል ከኦርቶዶክስ እምነት ጋር ይጋጫል»
  የቦሌ መድኃኒዓለም ሰበካ ጉባኤ
- «ጉባኤው ከእኛ እውቅና ውጪ ነው»
  ሰብከቱ ወንጌል መምሪያ
- የልማትና ክርስትያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ኮሚሽነር ተሰናበቱ

በውስጥ ገፅ
የ165 ኢንቨስተሮች ፍቃድ ተሰረዘ

በውስጥ ገፅ
ክረምትና የፔንሲዮን ጓዳዎች

በውስጥ ገፅ
የተቋማት የገለልተኝነት ጥያቄ

▷ ማስታወቂያ ◁

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

አውራምባ ታይምስ
ለመረጃ ቀርብ ይሁኑ

የካቲት 2000 ዓ.ም ተመሠረተ

አውራምባ ታይምስ፡- በብሉ አርዝ ጀነራል ቢዝነስ ኃላ/የተ/የግል/ማህበር ስር የሚታተም፣በፖለቲካዊ ና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በቁጥር 020/2/6572/2001 የተመዘገበ ሳምንታዊ ጋዜጣ ነው፡፡

ማኔጂንግ ኤዲተር
ዳዊት ከበደ

ዋና አዘጋጅ
ፍፁም ማሞ
(አድራሻ የካ ክ/ከ
ቀበሌ 03/04 የቤ.ቁ 1540)

ም/ዋና አዘጋጅ
ግዛው ለገሰ

አዘጋጅ
አቤል ዓለማየሁ

ከፍተኛ ሪፖርተሮች

ሰናይት ግርማ
ኤልያስ ገብሩ
ሱራፍኤል ግርማ

ዓምደኞች
አበበ ቶላ
ትዕግስት ወንድሙ

ማርኬቲንግ ዳይሬክተር
ለውጡ ኃይሌ

ሽያጭና ማስታወቂያ
ተሻለ ሰይፉ
ሲሳይ ጌትነት

ኮምፒውተር ፅሁፍ
መቅደስ ፍስሐ

ግራፊክስ ኤዲተር
ነብዩ መስፍን
(0911 18 09 33)
E-Mail:nebiyou1st@yahoo.com

የዝግጅት ክፍሉ ስልክ
ስልክ፡- 0911 62 92 78
0911 62 92 82
0911 11 03 90
ፖ.ሣ.ቁ 19325
awrambatimes@gmail.com
http://www.awramba.com

የአሳታሚው አድራሻ
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 01/02
የቤት ቁጥር 181
ዋናው ፖስታ ቤት ጀርባ
ከአምሳደር ወደ ንግድ ማተሚያ
ቤት በሚወስደው መንገድ ላይ
ከተስፋ ድርጅት ፊት ለፊት

ብሉ ኤርዝ ጀነራል ቢዝነስኃላ/የተ/የግል/ማ
Blue Earth General Business PLC

አታሚ፡-
ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ፡-አራዳ
ቀበሌ፡-17
የቤት፡-ቁ.984

## ርዕሰ አንቀፅ

# ዳያስፖራው፣የፖለቲካ አመለካከቱን እንደያዘ አገሩን እንዲያሳድግ ልባዊ ጥሪ ይቅረብለት

በ1990 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ኢህአዴግ በጅማ ከተማ ባካሄደው 3ኛ ጉባኤ ላይ የግንባሩ ሊቀመንበር የሆኑት አቶ መለስ ዜናዊ «ኢህአዴግ የአገራችን ባለሀብቶች የፖለቲካ አመለካከት ምንም ይሁን ምን በልማቱ ስራ ላይ አጋሮቻችን እንደሆኑ ያምናል» ብለው ነበር፡፡ አቶ መለስ ይህንን ጥሪ ባስተላለፉበት ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ባለሀብቶች ኢህአዴግን ቢቃወሙም ቢደግፉም በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ይህ ነው የሚባል ጫና ስለማይደርስባቸው የመሰላቸውን የፖለቲካ አቋም ይዘው የንግድ እንቅስቃሴያቸውን በነጻነት ያከናውኑ ነበር፡፡ የኋላ ኋላ ግን በተለይ አንዳንድ ባለሀብቶች የፖለቲካ ልዩነት በፈጠረው ክፍተት ምክንያት በአገር ጉዳይ ላይ ባይተዋር መሆን ሲጀምሩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩነታችውን እንደያዙ በአገር ልማትና እድገት ላይ አጋር ይሆኑ ዘንድ ጥሪውን አቀረቡላቸው፡፡

ከ1997 ዓ.ም በኋላ ግን ሁኔታዎች ይለወጡ ዘንድ ግድ ሆነ፡፡ ዛሬ አንድ ባለሀብት በስኬት ጎዳና ላይ እንዲራመድ በትርፍ ላይ ትርፍ እንዲጨምር ከፈለገ ከኢህአዴግ ጋር እጅና ጓንት እንዲሆን አለበለዚያ በዚህ የማይተባበር ከሆነ ምን አይነት ዋጋ እንደሚከፍል በግልጽ ተቀምጦለታል፡፡ ዛሬ የተለየ አመለካከት ልያዝ የሚል ባለሀብት ቢያንስ በታክስ ማጭበርበርም ይሁን በሌላ ቃሊቲ እስር ቤትን ሊጎበኝ ግድ ስለሚለው ባለሃብቱ ልማታዊ ባለሃብት ይሆን ዘንድ እጅ ሰጥቷል፡፡ በዛሬዋ ኢትዮጵያ ያለው ባለሃብት ከኢህአዴግ ጋር የተለየ የፖለቲካ አመለካከት እንዳለው በይፋ ሊናገር ቀርቶ መንግስትን ይተቻሉ በሚባሉ የግል ሚዲያዎች ላይ እንኳን ምርቱንና ድርጅቱን አያስተዋውቅም፡፡ በተለያየ መንገድ አንገቱን እንዲደፋ ተደርጓልና፡፡

ባለሀብቱ ይህንን አማራጭ የያዘው ወዶ ነው ወይስ ተገዶ የሚል አጀንዳ አንስቶ ለመከራከር አይደለም የጋዜጣችን መልእክት፡፡ ይልቅስ በ1990 ዓ.ም ኢህአዴግ እንደገለጸው ለአገር እድገትና ልማት ሲባል የፖለቲካ አመለካከትን እንደያዙ መስራት የሚቻል ከሆነ በመግቢያችን ላይ የጠቀስነው የአቶ መለስ ንግግር በውጭ ለሚገኘው ኢትዮጵያዊ ለምን አይቀርብም የሚል ጥያቄ ልናነሳ ወደድን፡፡

እንደሚታወቀው አገራችን ኢትዮጵያ በቂ እውቀትና ክህሎት ኖሯቸው ነገር ግን በትንሽ ፖለቲካዊ ልዩነት ምክንያት ከአገራቸው ርቀው የፈረንጅ አገልጋይ የሆኑ አያሌ ልሂቃን አሏት፡፡

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስር በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን የሚመለከት ዳይሮክተሬት ቢቋቋምም፣የመስሪያ ቤቱ የትኩረት አቅጣጫ የኢህአዴግን ፖሊሲ በሚደግፉት ላይ ብቻ በማነጣጠሩ በውጭ የሚገኙ በርካታ ኢትዮጵያዊያን በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ ለአገራቸውና ለወገናቸው ቤዛ ሊሆኑ አልቻሉም፡፡ ለዚህ አንዱና ብቸኛው ምክንያት የፖለቲካ ልዩነት እንደሆነ ይታወቃል፡፡

በመሰረቱ የፖለቲካ ልዩነት ማለት ሁለት ወገኖች የየራሳቸው የሆነ የፖለቲካ አቋም ሲኖራቸውና አንዱ «ለአገር የሚጠቅመው አካሄድ ይህ ነው» ሲል ሌላው በበኩሉ «የለም ጠቃሚውማ ይኸኛው አማራጭ ነው» ሲል ነው፡፡ ይህ ማለት እንግዲህ በመርህ ደረጃ አገር ልትጠቀም ይገባል በሚለው መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳብ ሁለቱም ይስማማሉ ማለት ነው፡፡

እንግዲህ በመርህ ደረጃ ሁለቱም ወገኖች በዚህ መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳብ ልዩነት ከሌላቸው (አገር አትጠቀም የሚል ዜጋ በመርህ ደረጃ ሊኖር ስለማይችል) ሁለቱም ወገኖች የሚስማሙ ከሆነ ይህችን በየአመቱ ሚሊዮኖች የሚራቡባት ድሀ አገር አሳፋሪ ገጽታዋ እንዲለወጥ ሲባል በመቻቻልና በሆደ ሰፊነት በሰው አገር የሚገኘው የተማረ ኃይል አገሩን እንዲጠቅም ልባዊ ጥሪ የማይደረግለት ለምንድነው? ይህንን የማመቻቸቱ ኃላፊነትስ ከሚመለከታቸው አገር ወዳድ ወገኖችም ሆነ ከመንግስት ቢቀርብ ምን ክፋት አለው?

ፕ/ር መሳይ ከበደ ከሁለት ሳምንት በፊት ለአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ በሰጡት ቃለ-ምልልስ «የኢትዮጵያ ህዝብ ለማገልገል በሚል ሙሉ ዓላማ የአገሬ ህዝብ ከፍሎ አስተምሮኝ አሁን ግን የአሜሪካ ዜጎችን ፍልስፍና እያስተማርኩ እገኛለሁ፡፡ ይህ ፍፁም አመክንዮአዊ አይደለም፡፡ ይህንን መብት ደግሞ የነፈገኝ የኢትዮጵያን ህዝብ ይወክላል የሚባለው መንግስት መሆኑ እጅግ ያሳዝነኛል» ብለው ነበር፡፡

ይህንን የፕ/ር መሳይ ሀሳብ የሚጋሩ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ፕሮፌሰሮች በአውሮፓ አና በሰሜን አሜሪካ ዩኒቨርስቲዎች ባዕዳንን እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ በርካታ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአስተማሪ እጥረት ኦና ሆነው ኢትዮጵያ በውጭ እርዳታና ብድር ትናንት ያስተማረቻቸው ብርቅዬ ምሁራን ባገኙት ዕውቀት ነገ አገር የሚረከቡ ወጣት ወንድሞቻቸውና ልጆቻቸውን እንዳያስተምሩ ዕድል ማጣታቸው እንደ አገር እና እንደ ህዝብ ሊያንገበግበን ይገባል፡፡ አገሩን የሚወድ ዜጋ በዚህ ምቾት ይሰማዋል ብለን አናስብም፡፡


ኢትዮጵያዊያን በአውሮፓና አሜሪካ ያላቸው ተቀባይነት ቀላል ቦታ የሚሰጠው አይደለም፡፡ በ2006 የሴኔትና የኮንግረስ ምርጫ አፈ ጉባኤ ሳራ ፖሊንን በማስመረጥ ረገድ የኢትዮ አሜሪካዊያን ሚና ቀላል አልነበረም፡፡ በ2008 ባራክ ኦባማ ለፕሬዚዳንትነት እንዲመረጡ «ኢትዮጵያዊያን ለኦባማ» የሚል የበጎ ፍቃደኞች ስብስብ የማይናቅ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ በዋሽንግተን ዲሲ አማርኛ የስራ ቋንቋ እንዲሆን ማድረግ ችለዋል፡፡ የ2000 ዓ.ም ሚሊኒየም ሲከበር በፖለቲካ ልዩነት ምክንያት ወደ አገራቸው መግባት ያልቻሉ ኢትዮጵያዊያን ባሉበት ቦታ ሆነው በዓሉን ሲያከብሩ የዋሽንግተን ዲሲ ከንቲባ ዕለቱ የኢትዮጵያዊያን ቀን ተብሎ እንዲሰየም አድርጓል፡፡ ይህንን ሁሉ ተፅእኖ የመፍጠር አቅም ያላቸው ኢትዮጵያዊያን በአገራዊ ጉዳይ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ ቢቀርብላቸው ድህነት መለያችን ሆኖ ለዘለአለም እንዳይፈነጭብን በማድረግ ረገድ ጉልህ ድርሻ ይኖራቸው ነበር፡፡

በምንም መመዘኛ ማንኛውም ወገን (የተለየ የአጥፊነት አጀንዳ ከሌለው አልያም ደግሞ አእምሮው ካልተቃወሰ በስተቀር) እትብቱ ለተቀበረበት አገር ብልፅግናና ሁለንተናዊ ዕድገት ጠንቅ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም፡፡ የፖለቲካ ልዩነታችን በፈጠረው መራራቅ ምክንያት አንዱን የአገር ጸር ሌላውን ደግሞ የገዛ አገሩን የማተራመስ አጀንዳ እንዳነገበ አድርጎ ታርጋ ከመለጠፍ ይልቅ የፖለቲካ ልዩነትን እንደ አንድ አገርን የሚጠቅም እሴት በመውሰድ ለዳያስፖራው ከልብ የመነጨ ጥሪ እናቅርብለት፡፡

*ኢትዮጵያ*
*ለዘላለም ትኑር*

VERBATIM


## ማን ምን አለ ????



«ገለልተኛ አለመሆናችን የሚነሳው የምርጫው ውጤት ይፋ ከተደረገ በኋላ ነው ወይ?»

**ፕሮፌሰር መርጋ በቃና**
**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ**

የቦርዱን የ2002 ዓ.ም የሥራ ክንውን ሪፖርት ባለፈው ማክሰኞ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረቡበት ወቅት «ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም» ሲሉ የምክር ቤት አባላት የሆኑ ተቃዋሚዎች ለሰነዘሩት አስተያየት የሰጡት ምላሽ፡፡



«በኢትዮጵያ ውስጥ ጣራ የነካ ትዕግስት የታየበት ታሪካዊ ሂደትን እድል አግኝቼ አምስት ዓመት እዚህ በምክር ቤት ውስጥ ኪሎ ሳይሆን የሃሳብ ግራሞቼን እየጣልኩ ቆይቼ ዛሬ ብመረጥም ባልመረጥም የሕዝቤን ውሳኔ ልቀበል ያለውን ሁኔታ በመቻል ስሰናበት እንደተሰናበትኩ አልቆጥረውም»

**አቶ ወንድሙ ኢብሳ**
**የሕብረት ምክትል ተጠሪ እና የፓርላማ አባል**

«የምክር ቤት አባል ሆነው ቆይተዋል፡፡ አሁን በመጭው ፓርላማ ላይ እርስዎ እና መሰል የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሰዎች ቦታውን አላገኛችሁም፡፡ በዚህ ምንድነው ተሰማዎት?» ተብለው ከነጋድራስ ጋዜጣ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፡፡



«በ97ቱ ምርጫ የተወሰኑ ምርጫ አስፈፃሚዎች በተወሰነ ሁኔታም ቢሆን ፍትሐዊ አልነበሩም፣ ነገር ግን ኢህአዴግ የተወሰነ ፈሪሃ እግዚአብሔር ወይንም ፈሪሃ ፈረንጅ ነበረው፡፡ አሁን የተካሄደው ምርጫ ቅርጫም አልመስል አለኝ፡፡ ... ለትንተናም አስቸጋሪ ሆኖብኛል፡፡»


**ዶ/ር መረራ ጉዲና**
**የመድረክ ምክትል ሊቀመንበር**

«...የፖለቲካ ምህዳሩ ፍትሃዊ ባልሆነበር ሁኔታ በምርጫ ተወዳድሮ ማሸነፍ ይቻላል?» በሚል ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፡፡



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# የተቋማት የገለልተኝነት ጥያቄ



በሰለሞን ሞገስ
(ፋሲል)

«በዋናው ፖስታ ቤት የፖስታ መልዕክቶቻችን ተከፍተው ይደርሱናል»
**አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ**

«የመንግስትን ንብረቶች ገዥው ፓርቲ ለምርጫ ቅስቀሳው ተጠቅሟል::»
**የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን**

«የምርጫ ቦርዱ ወገንተኛ ነው::»
**ተቃዋሚ ፓርቲዎች**

«ገዥው ፓርቲ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥንን የብቻው መጠቀሚያ አድርጓቸዋል::»
**ተቃዋሚዎች**

«የግል ጋዜጦች ለተቃዋሚው የወገኑ ናቸው::»
**ኢህአዴግ**

በአንድ አገር የዴሞክራሲ ግንባታ ውስጥ ቁልፍ ሚና ከሚጫወቱ ባለድረሻዎች መካከል የአገሪቱ ተቋማት ሳይጠቀሱ አይታለፉም:: ተቋማት ድክመታቸውን በማረም፣ ጥንካሬያቸውን በማጎልበት ሕዝቦች የተሻለ ዋስትና፣ የተሸለ ሕይወትና ብልፅግና እንዲጐናፀፉ በማንም የማይተካ ሚና አላቸው:: የተቋማት ድክመት (ችግር) በአገር እድገትና በሕዝብ ሕይወት ላይ ከፍ ያለ ጉዳትን ያስከትላል::

ተቋማት አንድም የአገሪቱን ሥርዓት እንደምሰሶ ደግፈው የሚያቆሙ ናቸው:: በሌላ በኩል ደግሞ የሥርዓቱ ምንነት መገለጫዎች ሆነው ይታሰባሉ:: ይህም ማለት እነዚህ ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎት በቅርበትና በጥልቀት በማየት የሥርዓቱን ባህሪ፣ የሥርዓቱን የዕድገት ደረጃ እና በአጠቃላይም የአገሪቱን እርምጃ መፈተሽና መተንተን ያስችላሉ::

ሕዝባዊ ተቋማት በሌሉበት የዴሞክራሲ ሥርዓት ሊገነባ ቀርቶ ሊታሰብ አይችልም:: ተቋማት በመዋቅር ደረጃ እያሉ ሕጋዊ ኃላፊነታቸውን እና ሕዝባዊ አገልግሎታቸውን በአግባቡ መወጣት ካልቻሉም ልፋቱ ሁሉ ውሃ እንደ መውቀጥ ነው የሚሆነው:: እነዚህ ተቋማት እንደአያያዛቸው ሊያድጉና ሊጠነክሩ፣ አልያም በተቃራኒው ሊቀጭጩና ሊከስሙ የሚችሉ ናቸው::

ተቋማት ለተወሰነ ቡድን ወይም አካል ያልተገባ ጥቅም መስጠት አልያም ተገቢውን አገልግሎታቸውን ለተገቢው አካል አለመስጠት በስህተት ደረጃ ብቻ ታይቶ የሚታለፍ አይደለም:: እናም፣ እያንዳንዱን ተቋም በአዋጅና ደንብ ከተሰጠው ኃላፊነት አኳያ በሕግ ፊት የሚያስጠይቀው ተግባር ነው:: ይህን የምለው ከሕጉ ፅንሰ ሃሳብ አንፃር ሲሆን የሕጉ ሃሳብ ወደ መሬት ወርዶ ካለው ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥሟል ወይስ ሆድና ጀርባ ሆኗል ብለን መፈተሽ ደግሞ «ያለንበትን ልክ» ለማወቅ ያስችለናል::

ይህን ጽሑፍ ከማዘጋጀቴ አስቀድሞ፣ ሕብረተሰቡ በልዩ ልዩ ተቋማት ላይ ያለው መተማመንና የእኔነት ስሜት ምን ያህል ነው? የሚል መጠነኛ ጥናት (መጠይቅ ብጤ) ለማዘጋጀት አስቤ ነበር (በአንዳንድ ግላዊ ምክንያቶች አልተሳካልኝም እንጂ):: ይሁንና ይህንኑ ርዕስ ጉዳይ ሻይ ቡና ከምንባባል ወዳጆቼ ጋር ሆኜ በጠረጴዛ ዙሪያ አንስቼው ነበር:: በዚህ ግዜም ብዙዎቻችን በመንግስት እጅ ባሉ የሕዝብ ተቋማት ላይ አመኔታ እንደሌለን ለመታዘብ ችያለሁ::

አንዳንድ ተቋማት በአገራችን እንዲኖሩ የምንፈልገው ተቋማቱ በሌሎች ያደጉ አገራት ስላሉ ብቻ ይመስላል:: አገር ጐረቤት ሱቅ ስትከፍት ሱቅ፣ ጠላ ቤት ስትከፍት ጠላ ቤት እንደምትከፍት ሴት መሆን የለባትም:: የሕዝብ እንባ ጠባቂ ኮሚሽን እንዲኖር ያስፈለገው በሌላው አገር ስላለ ብቻ ከሆነ ተቋሙ ቢኖርም እንኳ የሌለ ያህል ነው:: ለዚህ የሚባክነው ጊዜ፣ ጉልበት፣ ገንዘብ እና የአገር ኃብት የሚያስቆጭ ይሆናል:: በመሆኑም እያንዳንዱን ተቋም ስንገነባ ለይስሙላና ለዝና (እወቁልን) ሳይሆን፣ ደጋግመን አስበንበት፤ ለተቋሙ ነፃ እቅስቃሴም እራሳችንን ዝግጁ አድርገን መሆን አለበት::

ማንኛውም ዜጋ በአገሩ ተቋት ላይ ሙሉ መተማመን ሊኖረው ይገባል:: ሕዝባዊና መንግስታዊ ተቋማት በአግባቡ ያገለግሉኛል፣ ለማንም ያልወገኑ ሁሉን በእኩልነት የሚያስተናግዱ፣ ከአድልዎ፣ ከሸፍጥና ከሕገ-ወጥ አሰራር የፀዱ የእራሱ ተቋማት ናቸው፤ ችግር ሲኖርም ላርማቸው፣ ላስተካክላቸው እችላለሁ የሚል እምነትን መፍጠር መቻል አለበት:: የተቋማቱ የአቅም ውስንነት እንዲቀረፍ፣ የብቁ አገልግሎት ደረጃቸው እንዲሻሻል ድጋፍና እገዛ፣ አድናቆትና ትችት ሊሰጣቸው ይገባል:: ቀደም ሲል እንዳልኩትም ተቋማት ወደተሻለ

**ማንኛውም ዜጋ በአገሩ ተቋት ላይ ሙሉ መተማመን ሊኖረው ይገባል:: ሕዝባዊና መንግስታዊ ተቋማት በአግባቡ ያገለግሉኛል፣ ለማንም ያልወገኑ ሁሉን በእኩልነት የሚያስተናግዱ፣ ከአድልዎ፣ ከሸፍጥና ከሕገ-ወጥ አሰራር የፀዱ የእራሱ ተቋማት ናቸው፤ ችግር ሲኖርም ላርማቸው፣ ላስተካክላቸው እችላለሁ የሚል እምነትን መፍጠር መቻል አለበት::**

ደረጃ ሊያድጉም ሆነ ወደከፋ ሁኔታ ሊያሽቆለቁሉ የሚችሉ ናቸው::

የዴሞክራሲ ሥርዓትን እንገነባለን ከተባለበት ከ1983 ዓ.ም ወዲህ አንስቶ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ፣ ልዩ ልዩ ተቋማት ተመስርተዋል:: ከዚያ ዓመት በፊትም ሆነ ከዚያ ወዲህ ሕዝባዊ አገልግሎት ያላቸው ተቋማት (ድርጅቶች) ተፈጥረዋል - እየተፈጠሩም ነው:: የመንግስት አሰራርና ተጠያቂነትን ያፀናው የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 12 ቁጥር 1፣ «የመንግስት አሰራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት» ሲል አስፍሯል:: በእነዚህ ተቋማትና ድርጅቶች አሰራር ላይ ሕዝብ ያለው እምነትና የልብ ኩራት ግን ከሸረሪት ድር የቀጠነ ሆኖ ይታያል:: ለዚህ ማሳያ የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን በምሳሌነት እናንሳ:: ኮሚሽኑ በመንግስት የሥልጣን ደረጃ በታችኛው እርከን (ተዋረድ) ላይ ለተቀመጡ ሹመኞች እንጂ ከፍ ላሉት ቱባ ባለሥልጣናት ጥርስ አልባ ነው የሚል ቅሬታ ይነሳበታል:: አንዳንዶችም ተቋሙን ያፌነገጡ ፖለቲከኞች የተባሉትን መምቻ አድርገው ያዩታል:: የሚባል፣ የሚወራው ሁሉ «ውሸት» ሊሆን ይችላል፤ «እውነትም» ሊሆን ይችላል:: የኔ ነጥብ በተቋሙ ላይ የዜጐች ጥያቄና ጥርጣሬ ጐልቶ መታየቱን ማስገንዘብ ነው:: ስለሆነም ተቋሙ ስሙን ሊያድስ የሚገባው ይመስለኛል:: ስሙን ሊያድስ ይገባል ስልም የፕሮሞሽን ስራ ያካሂድ ማለት ሳይሆን የሚወራበትን አለመሆኑን በተጨባጭ ተግባር ማረጋገጥ አለበት ነው:: ኮሚሽኑ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ፍርሀት ሳይሆን ኩራት ሊሆን ይገባል::

በአገራችን የፌዴራል ፖሊስ፣ የፍትህ አካላት፣ የምርጫ ቦርድ፣ የመንግስት የመገናኛ ብዙሀንና ሌሎችም መሰል ተቋማት ከተለያዩ አቅጣጫዎች የገለልተኝነት ጥያቄ ሲነሳባቸው ይታያል:: ቀደም ሲል እንዳልኩት የሚወራው ሁሉ እውነት ወይም ውሸት ነው የሚለው ጥያቄ አጀንዳ ውስጥ አልገባም:: እንዲያ ከሆነ ደግሞ መረጃ ቆጠራና የዳኝነት ሥራ ውስጥ ልንገባ ይሆናል:: በጥቅሉ ግን ተቋማት በዚህም ሆነ በዚያ ምክንያት በዜጐች ዘንድ መታመን የጐደላቸው መሆኑን መናገር ይቻላል:: አመኔታ በቅስቀሳና በማስታወቂያ ጋጋታ የሚፈጠር አይደለም ብለናል:: ተዓማኒነት የሚፈጠረው በብቁ ሙያዊ አገልግሎት ብቻ ነው:: ብዙ ጊዜ የምናየው ግን በቅስቀሳና በውትወታ እንዲህ ነን የሚለውን ምስል ለመፍጠር የሚደረግ አጉል መፍጨርጨር ነው:: አንድ ሰው «ጥሩ የዘፈን ድምጽ አለኝ» ብሎ ቀን ከሌት ቢወተውት «አዎ አለህ» ብለን ቆመን እንድናጨበጭብ ሊጠብቅ አይገባውም:: ሰውዬው ጥሩ ድምጽ ያለው መሆኑን እንድናውቅለት ከፈለገ አማራጩ አንድ ብቻ ነው - በጥሩ ሁኔታ ዘፍኖ ማሳየት::

ካልተሳሳትኩ ከዓመት በፊት የተላለፈ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የቴሌቪዥን ማስታወቂያ ነው:: ተገፋሁ፣ ተጠቃሁ ያለ ሰው በወንበር ቆሞ «ኡኡ ተበደልኩ!» ሲል አካባቢውን በጩኸት ያናጋዋል:: የማስታወቂያው መልዕክት፣ «ስትበደሉ፣ ስትገፉ፣ ስትጠቁ ዝም አትበሉ፤ ተከራከሩ፣ ተናገሩ፣ ጠይቁ፤ እኔም ከጐናችሁ ነኝ» የሚል ይመስለኛል:: ብዙዎቻችን ግን አንገታችንን ደፍተን፣ ሀዘናችንን አምቀን «ሆድ ይፍጀውን» እያንጐራጐርን «ንጉስ አይከሰስ፣ ሰማይ አይታረስ»ን እየተረትን ወደየጐጇችን እንዝለቃለን::

በበዕውቀቱ ስዩም

▷ ማስታወቂያ ◁

AWARD COMPUTER TECHNOLOGY PLC
አዋርድ ኮምፒውተር ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ማ

የኮምፒውተር ኮርሶችን ለክረምት
በልዩ ፕሮግራም ምዝገባ ጀምረናል!

| መሰረታዊ የኮምፒውተር ኮርስ | |
| --- | --- |
| የሐራት ወር | በወር 120 በሳምንት 3 ቀን |
| የሃምሌ ወር | በወር 160 በሳምንት 3 ቀን |
| የነሐሴ ወር | በወር 195 በሳምንት 4 ቀን |

በነጻ የሚጨመር ኮርሶች
- Ms Publisher
- Ms Power Point
- Internet Usage

ADVANCED COURSES

| Course Name | Fee |
| --- | --- |
| Peachtree | 250 Birr |
| Quick Book | 500 Birr |
| Sun systam | 2000 Birr |
| C++ | 490 Birr |
| VB.Net | 950 Birr |
| Photoshop | 550 Birr |
| Cisco CCNA | 1600 Birr |
| Web Design Basics | 700 Birr |
| Web Design Advanced | 1400 Birr |
| SPSS | 800 Birr |
| 3D-MAX Animation | 1600 Birr |

| Course Name | Fee |
| --- | --- |
| Auto Cad | 355 Birr |
| Archi Cad | 600 Birr |
| Eagle Point | 550 Birr |
| SAP | 550 Birr |
| ETAPS | 750 Birr |
| Ms-Project | 785 Birr |
| GIS | 980 Birr |
| Primavera | 690 Birr |
| MX- Road | 900 Birr |
| Inroad | 700 Birr |
| Terra Model | 700 Birr |

አድራሻ ፡ - የቅድስት ልደታ ማርያም ህንጻ ግራውንድ ፍሎር ሜክሲኮ ልደታ ቤተክርስቲያን ገን
Address :- St. Lideta Building Ground Floor, Mexico Near to St. Lideta Church
☎0115-151586 0911-876425 / 0912-119797 ✉42120, A/A

PHONiex TECHNOLOGY PLC
ፎኒክስ ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ማ

SUMMER COMPUTER CLASSES

| | | | |
| --- | --- | --- | --- |
| PEACH TREE | 500ETB | SUN SYSTEM | 2000ETB |
| QUICK BOOK | 550ETB | SAP, VISION EXCEL, SAGE AND MORE ACCOUNTING SOFT-WARES WILL BE COMING SOON | |
| ACK PACK | 2000ETB | | |

Computer Courses For Engineers

| | | | |
| --- | --- | --- | --- |
| AUTOCAD 2007 | 385ETB | EAGLE POINT | 515ETB |
| ARC GIS | 980ETB | SAP 580ETB /E-TABS | 855ETB |
| ARCICAD | 595ETB | TOTAL STATION | 1900ETB |
| PRIMAVERA | 755ETB | INROAD 750ETB CIVIL DESIGNER | 795ETB |

FOR IT EXPERTS AND OTHERS

| | | | |
| --- | --- | --- | --- |
| VB .NET | 850ETB | C++ | 495ETB |
| WEBSITE DESIGN I | 645ETB | ORACLE I | 1200ETB |
| CISCO CCNA | 1500ETB | SQL SERVER | 850ETB |
| JAVA | 505 ETB | ILLUSTRATOR | 555ETB |
| A+ MAINTENANCE | 525ETB | PHOTOSHOPE | 480ETB |
| MCSA PER MODULE | 1300ETB | VIDEO EDITING | 945ETB |
| NETWORK ADMINISTRATION | 1350ETB | SO MANY OTHERS .... | |

BIG NEWS
We are now giving away free courses for people coming in group for summer.

አድራሻ: - ከሜክሲኮ ወደልደታ በሚወስደው መንገድ ከተግባረዕድ ዝቅ ብሎ ከፌሲፕስ ፊት ለፊት ጨለለቅ አልሳም ህንጻ 1ኛ ፎቅ
ASK FOR MORE YOU GET MORE!
☎0115-526244/45 Mob 0911- 462706/ 0911-623383 ✉4858, A/A

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# ሕብር ስኳር አክሲዮን ማህበር
## Hiber Sugar Share Company

# ለመጨረሻ ጊዜ የተሰጠ መልካም አጋጣሚ

**ለተከበራችሁ የሕብር ስኳር አክሲዮን ማህበር አባላትና አክሲዮዮን ለመግዛት ላሰባችሁ ሁሉ::**

ሕብር ስኳር አክሲዮን ማህበር በእርሻ መሬቱ ላይ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በመጀመር አክሲዮኑን በፍጥነት እየሸጠ በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ይገኛል:: በአሁኑ ጊዜ አክሲዮን ማህበሩ ለፋብሪካው ግንባታ አስፈላጊ የሆነውን እና ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ባንኮች የብድር ጥያቄ የሚቀርብ ሰነድ (Bankable Document) የሚሰሩ ዓለም አቀፍ እወቅና ያላቸውን ኮንሰልታንት ኩባንያዎች ለመቅጠር የጨረታ ሰነድ ማስታወቂያ አውጥቷል::

በዚህ ሁኔታ ላይ የማህበራችን የዳይሬክተሮች ቦርድ የመስራችነት ልዩ ጥቅም የሚያስገኘው አክሲዮን ግንቦት 10/2002 ዓ.ም እንዲጠናቀቅ ከወሰነ በኃላ የተለያዩ የሕብረሰበብ ክፍሎች ማለትም:-

- § በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን
- § የሕብረት ስራ ማህበራትና እድሮች
- § የተለያዩ ኩባንያዎች እንዲሁም
- § እድሉ ያመለጣቸው ግለሰቦች የመስራችነት ልዩ ጥቅም የሚያስገኘው የምዝገባ ቀነ ገደብ ለመጨረሻ ጊዜ እንዲቀጥል ጠይቀዋል::

በዚህ መሠረት ቦርዱ የመስራችነት ልዩ ጥቅም የሚያስገኘው ምዝገባ ለመጨረሻ ጊዜ እስከ ሐምሌ 10/2002 ብቻ እንዲቀጥል ወስኗል::
ስለሆነም በዚህ እድል በመጠቀም የሕብር ስኳር አክሲዮን መሥራች በመሆን:-

- § ከሚገዙት የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ በተጨማሪ የ4% ትርፍ ልዩ ጥቅም ተጋሪና
- § ወደፊት ተጨማሪ አክሲዮኖች ሲሸጡ እስከ 4 ዓመት በተመሳሳይና አሁን ባለው መደበኛ የአክሲዮን ዋጋ የማሳደግ መብት በማግኘት የኩባንያው መስራችና ባለቤት እንዲሆኑ ተጋብዘዋል::

በዚሁ አጋጣሚ አክሲዮን ገዝታችሁ ቀሪ ክፍያ ያለባችሁ አባሎቻችን እስከ ሐምሌ 10/2002 በማጠናቀቅ ውልና ማስረጃ ለሚፈረመው ሰነድ እራሳችሁን እንድታዘጋጁ በአክብሮት እናሳስባለን::


**የመስራችነት ልዩ ጥቅም የሚያስገኘውን የህብር ስኳር አ.ማ. አክሲዮኖች**
**በህጋዊነት የሚሸጡ የአዲስ አበባና የክልል ወኪሎቻችን አድራሻዎች የሚከተሉት ናቸው::**

| | | |
|---|---|---|
| የሽያጭ ወኪሉ ስም | የሽያጭ ወኪሉ አድራሻ | |
| | አድራሻ | ስልክ ቁጥር |
| ኢ/ር አየለ ተጫኔ | አዲስ አበባ | 0911-22-95-93 |
| አቶ ክበበው ገ/የስ | አዲስ አበባ (ፒያሳ ሞዝቮልድ አጠገብ) | 0911-23-04-75 |
| አባይ ወንዝ የመኪና ክራይ | አዲስ አበባ (ራስ ሆቴል ፊትለፊት) | 0911-23-09-17 ወይም011-5527175 |
| አቶ. ጋሻው ለገሠ | አዲስ አበባ (ለም ሆቴል ሳላይሽ ሕንጻ) | 0911-21-19-95/0116622382 |
| ኮንቲኔታል የንግድ አማካሪ | አዲስ አበባ<br>ሀረር<br>ድሬዳዋ<br>ጅጅጋ<br>አሰበ ተፈሪ | 0911-93-42-07<br>0911-92-83-57/0256-66-56-62<br>0915-73-51-75/0251-11-21-71<br>0913-78-93-22<br>0912-95-96-01 |
| አቶ ሣህሉ ሰማ | አዲስ አበባ (መገናኛ የካ ቤ/ክርስቲያን አጠገብ ሜሪ የሕንፃ መደብር) | 0911-64-79-34 |
| አቶ ዋለልኝ መላክ ይርዳው | አዲስ አበባ | 0911-68-59-73 |
| ይግዛው አቢ | ባህር ዳር (ዝማምነሽ ሕንጻ) | 0913-71-47-02 |
| ማንያዘዋል ማንደፍሮ | ጎንደር (ጃን ተከል ንግድ ባንክ አጠገብ) | 0911-34-15-91/0918-04-27-29 |
| አቶ አእምሮ ተገኝ | ናዝሬት (አእምሮ መዝናኛ) | 0911-22-77-91 |
| አቶ ገናናው አሰፋ | ናዝሬት (ሕብረት ባንክ አጠገብ) | 0911-62-79-76 |
| አቶ ሽመልስ አባይነህ | ደብረ ማርቆስ (የኛ ሕንጻ) | 0911-99-31-65/0587-71-56-95 |
| አቶ ገበሩ (ገቤክ ፕሮሞሽን) | መቀሌ | 0913-27-92-70 |
| ጠሸት የንግድ | ደሴ (ዳሽን ባንክ ፊት ለፊት) | 0912-17-87-32/0914-71-18-17 |
| ኢ/ር አዳነ ቶለሬ | ሐዋሳ | 0916-82-33-45 |

**የሕብር ስኳር አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ**
**አድራሻ ሕብር ስኳር አክሲዮን ማህበር**
ዲ አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት በተገነባው አዲሱ የታደሰ ተፈራ ሕንፃ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 105
ስልክ 0118-50-13-57/ 0118-50-13-58 251-910-196886 / 251-913-437942/251-913-368965
Website: www.hibersugarethiopia.com, E-mail: info@hibersugarethiopia.com



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com



# አፍሪካ እና የልማት እርዳታ

## /ውጤት አልባነትና አዲስ የመፍትሄ ስትራቴጂን አስፈላጊነት/

በተስፋዬ ሀቢሶ
(አምባሳደር)

«ልክ ለቀዛፊዎች የወደብ አቅጣጫን እንደሚያመላክት የጉልላት የብርሃን ማማ፣ «ልማት»ም የታዳጊ አገራትን ድህረ ጦርነት ታሪክ የጉዞ አቅጣጫ ተቋሚ የሆነ ሀሳብ አይነት ሆኖ የሚያገለግል ሆኗል:: ዴሞክራሲያዊ ወይም አምባገነናዊ ሥርዓት ቢከተሉም ባይከተሉም፣ የደቡባዊ አፍሪካ አገራት ልማትን እንደ ተቀዳሚ ትልማቸው አውጀው ነበር:: ከአራት አስርት ዓመታት በኋላም፣ መንግስታትና ዜጎች በተመሳሳይ የብርሃኑ ርቀት ከመቸውም በበለጠ እጅግ በርቀት የብርሃን ፍንጣቂ በሚያመነጨው ላይ አሁንም አይናቸውን እንደተከሉበት ናቸው፤ እያንዳንዱ ጥረትና እያንዳንዱ መስዋዕትነት ምክንያታዊ የሚደረገው ግቡ ላይ በመድረስ ቢሆንም ብርሀኑ ያለው ጉልበት እየሚሸሸ እየሚሸሸ መሄዱን ቀጥሏል::» (ዎልፍጋንድ ሳቼዝ፣ «The Development Dictionary: A Guide to Knowledge and Power, 1992»፣ ገጽ 1)

ከአውሮፓውያን ቅኝ አገዛዝ የፖለቲካ ነፃነት ከታወጀበ በኋላ ባሉት በርካታ አስርት ዓመታት ውስጥ፣ በኢንዱስትሪ የበለፀጉ አገራት በማደግ ላይ ላሉ አገራት በመቶ ቢሊዮኖች ዶላር የሚቆጠር የገንዘብ መጠን በውጭ እርዳታ ወይም በልማት ድጋፍ መልኩ አቅርበውላቸዋል:: የልማት ድጋፉ መጠን በ1965 ስድስት ቢሊዮን 480 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን፣ በ1989 ወደ 46 ቢሊዮን 697 ሚሊዮን (የአሜሪካ ዶላር) እድገት አሳይቷል:: (ሀሪየት ባልድዊን፣ «The World Bank: 1993»)::

እንደ ዓለም ባንክ፣ ወደ ሰሃራ በታች የሚገባው የእርዳታ ፍሰት በ1980 ከነበረበት 3.4 በመቶ፣ በ1995 ወደ 16.3 በመቶ አድጓል:: እነዚህም መንግስታዊ ፍሰቶች በተለይ መሰረታዊ የመንግስት የልማት ወጪዎችን የሚደጉሙ ነበሩ (ሀሪየት):: ምንም እንኳን ይህን ያህል ግዙፍ የልማት ድጋፍ ያለ ቢሆንም እና ከላይ የተገለፀው ኮታ በግልጽ እንደሚገልፀው፣ የልማት ድጋፍ ለአፍሪካ ምንም ዓይነት ትርጉም ያለውና ዘላቂ ልማት ማምጣት አልተቻለውም፤ ለአብዛኞቹ የአፍሪካ አገራት ልማት ህልም ብቻ እንደሆነ የቀረ እና በ21ኛው ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ እንኳን እውን ሊሆን የማይችል ግብ እንደሆነ ያለ ነው::

አንድ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማሕበር ሪፖርት ቅልብጭ አድርጐ እንደሚያስቀምጠው «. . . እርዳታ ስንል በረዥም ጊዜ ውስጥ በሰዎች ሕይወት ላይ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ ማለታችን ከሆነ፣ ሰዎች አስቸኳይ እርዳታ አስፈላጊያቸው በማይሆንበት ሁኔታ ውስጥ እንዲኖሩ እነርሱን መርዳት ማለታችን ከሆነ፣ እርዳታ ግቡን ያልመታ መሆኑ ግልፅ ነው ምክንያቱም ባለፉት ዓመታት ውስጥ ለአስቸኳይ እርዳታ የተጋለጡ ሰዎች ቁጥር በእጅጉ ጨምሯልና ነው:: . . . እርዳ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕይወት ታድጎ ሊሆን ይችላል፣ ሆኖም በረዥም ጊዜ ውስጥ ግን ነገሮች እየተባባሳ የሄዱ ነው የሚመስለው . . . » [የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማሕበር - 2004]::

በሁሉም መመዘኛዎች የትኞችንም አይነቶች ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቋሚዎች ብንወስድ ዛሬ አፍሪካ ከመላው ዓለም በጣም ኋላ የቀረችና እጅግ ድሃዋ አሕጉር እንደሆነች መመልከት ይቻላል:- «ከግማሽ በላይ የሚሆነው ሕዝቧ በቀን ከአንድ የአሜሪካ ዶላር በታች ባነሰ ገቢ ነው የሚኖረው:: ከግማሽ በላይ የሚሆነው ሕዝብ በፍፁም ድህነት የሚኖርበት የሰሃራ በታች አፍሪካ፣ 291 ሚሊዮን የሚደርሱ ድሃዎች መኖሪያ ነው:: ከግማሽ በላይ የሚሆነው ሕዝብ የንፁህ ውሃ አቅርቦት አያገኝም:: በየዓመቱ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ጨቅላዎች የመጀመሪያውን የልደት ቀናቸውን ከማክበራቸው በፊት ይሞታሉ:: ከአንድ ሺህ ሕፃናት ውስጥ 140 ሕፃናት ከአምስት አመታቸው በፊት የሚሞቱ ሲሆን በሕይወት የሞቆያው የዕድሜ ጠገግ ደግሞ 54 ዓመት ነው:: በመቶኛ፣ ዕድሜያቸው ከ15 በላይ ሆነው ማንበብና መፃፍ የሚችሉ 41 በመቶ ናቸው:: በአፍሪካ ውስጥ ለእያንዳንዱ 1ሺህ ሰው 18 የስልክ መስመር ያለ ሲሆን በመላው ዓለም 146፣ በበለጸጉ አገራት ውስጥ ደግሞ 456 የመስመር ስልኮች ለእያንዳንዱ 1ሺህ ሰው ግልጋሎት ይሰጣል:: በ1989፣ የሰሃራ በታች አገራት የብድር ክምችት 236 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ይደርሳል ተብሎ ተገምቶ የነበረ ሲሆን የጠቅላላው አሕጉሩ ደግሞ ከ300 ቢሊዮን በላይ እንደሚሆን ተገምቶ ነበር:: የአፍሪካ የብድር ሸክም ከየትኛውም የዓለም ክፍል ሁለት እጥፍ ነው - በማደግ ላይ ያለው ዓለም 11 በመቶ የብድር መጠን የሚይዝ ሲሆን 5 በመቶ ገቢ ብቻ ነው ያለው:: [ Time for a NEPAD Reality Check, «ዘ ስታር»፣ ማክሰኞ መስከረም 9/ 2003 (እ.አ.አ.)፣ ገፅ 13]::

በቅርቡ «ኒው ዮርክ ታይምስ» መጽሔት በዋናነት ባወጣው ጽሑፍ ተመሳሳይ ደብዛዛ መጪ ጊዜን ገልፆ ነበር:- «በየዓመቱ በክልሉ ያሉ አብዛኞቹ አገራት (የሰሃራ በታች ያሉ አገራት) ድህነት፣ ርሃብ እና በሽታ እየባሰባቸው ነው የሄደው:: በዓለም ንግድና ኢንቨስትመንት ያላቸው ድርሻ እየወደቀ የሄደ ነው:: አማካዩ የእያንዳንዱ ሰው ገቢ በ1960ዎቹ ከነበረው ዝቅተኛ ሲሆን ግማሽ ያህሉ ሕዝብ የሚኖረው በቀን ከ65 ሳንቲም (የአሜሪካ ዶላር) ባነሰ ገቢ ነው:: . . . ባለፈው አስርት ዓመታት አካባቢ፣ በመላ ክልሉ ርሀብ አስከፊ ችግር የሆነ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜም የአየር ንብረቱ እንኳን በጣም ምቹ በሆነበት ወቅት ይከሰታል:: . . .» [«ዘ ኒው ዮርክ ታይምስ መጽሔት»፣ ሀምሌ 13 2003]::

የአገር ውስጥ ፍላጎትን የሚሟላት አቅጣጫ በያዘ መልኩ በግብርና እና በኢንዱስትሪ ዘርፍ ራሱን የቻለ እድገት እንዲመጣ ዓለም አቀፉ መንግስታዊ እርዳታ በተደጋጋሚ ለማበረታታት አለመቻሉ ብዙዎች የእርዳታን ትክክለኛት እንዲጠይቁ ያስገደዳቸው እውነታ ነው:: በአሁኑ ወቅት ያለውን የልማት እርዳታ ሥርዓት በተመለከተ በርካታ ችግሮች ተነቅሰው ወጥተዋል:: ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል:-

አንደኛ:-አብዛኛው እርዳታ ከልገሳ ይልቅ በብድር መልክ የሚሰጥ በመሆኑ በጣም ድሃ አገራትን ምናልባት በከባድ እዳ ውስጥ ሊዘፍቃቸው ይችላል::

ሁለተኛ:- የየትኛውም እርዳታ ፓኬጅ አብላጫ የሚዋጠው የቴክኒክ ድጋፍ በሚሰጡ ኤክስፐርቶች እና ለለጋሽ አገራት የመስክ ሰራተኞች በሚውለው ክፍያ ወይም ለእነርሱ በተቀባይ አገራት በሚደረገው የቤት፣ የትራንስፖርትና የምግብ ወጭዎች ዝግጅት ነው:: «እስከ 25 በመቶ የሚሆነው የምዕራቡ የእርዳታ በጀት በኤክስፐርቶች ወጭ የሚውል ነው:: . . . መካከለኛ ነው የሚባል የእንግሊዝ ኤክስፐርት በዓመት 150ሺህ የአሜሪካ ዶላር ያስወጣል::» «New Internationalist»፣ 1991)::

**የምግብ እርዳታ ለሶስተኛው ዓለም አገራት የሚሰጥ ዋነኛው የእርዳታ አይነት ነው:: በረዥም ጊዜ ውስጥ የምግብ እርዳታ አስከፊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ሲያመጣ የሚችል ነው:: ኢኮኖሚን በተመለከተ የአገር ውስጥ ገበያን በመጫን ምርታማነትን የማያበረታታ በመሆኑ የሶስተኛውን ዓለም የግርና ዘርፍነወ የማላሸቅ አዝማሚያ አለው::**

ሶስተኛ:- የምግብ እርዳታ ለሶስተኛው ዓለም አገራት የሚሰጥ ዋነኛው የእርዳታ አይነት ነው:: በረዥም ጊዜ ውስጥ የምግብ እርዳታ አስከፊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ሊያመጣ የሚችል ነው:: ኢኮኖሚን በተመለከተ የአገር ውስጥ ገበያን በመጫን ምርታማነትን የማያበረታታ በመሆኑ የሶስተኛውን ዓለም የግርና ዘርፍነወ የማላሸቅ አዝማሚያ አለው:: ምንም እንኳን ገበሬዎች ስኬታማ በሆነ መልኩ ለመስራትና ለማልማት ፍላጐቱ ቢኖራቸውም፣ የአገር ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች አመቺ አለመሆናቸው ከስራ በቂ የሆነ ትርፍ የማግኘት እድል የተገደበ ነው ማለት ነው:: በማህበራዊ ደረጃ ይህ ገበሬዎች ከስራ እንዲወጡ የሚያደርጋቸው ነው:: በፖለቲካው ረገድ፣ የሶስተኛው ዓለም መንግስታት ለለጋሽ አገራት የበታች ሊያደርጋቸው የሚችልና ያም የማይፈለጉ ሆነው ሳለም እንኳን የለጋሽ አገራትን ተረፈ ምርቶች እንዲሸምቱ አድሮጎ አስገዳጅ ሊያደርጋቸው የሚችል ነው፤ ለምሳሌ ፓኪስታን የራሷ በቂ ምርት እያላት የአሜሪካንን የጥጥ ምርት መግዛት ግድ ብሏት ነበር (አንድሪው ዌብስተር)::

አራተኛ:- ለአንዲት አገር የሚሰጥ እርዳ ያቺ አገር የለጋሹን አገር ምርቶች የምትሸምት እንደሆነ በሚል የሚሰጥ ከሆነ የዚያችን አገር በእርዳታ ላይ የሚኖራትን ጥገኝነት የሚያባብሰው ነው የሚሆነው፤ ይህም አይነት እርዳታ «አሳሪ እርዳታ» በመባል ይታወቃል:: በዚህ ቅድመ ሁኔታ መሰረት ነው 70 በመቶ የሚሆነው የእንግሊዝ እርዳታ የሚሰጠው፤ እናም እርዳታ ለእንግሊዝ አምራቾች አስፈላጊ የሆነ ገበያን ያቀርብላቸዋል ማለት ነው:: «እርዳታ የበለጠ ሥራ ይፈጥራልና በታዳጊ አገራት ውስጥ ይልቅ በይበልጥ ባደጉት አገራት ውስጥ በርካታ ኢንዱስትሪዎች እንዲቋቋሙ ምክንያት የሚሆን ነው:: ዋነኞቹ የእርዳታ ተጠቃሚዎች በማደግ ላይ ላሉ አገራት በርካታ ዓለም አቀፍ ኤክስፐርቶችን የሚያቀርቡ እና ለእነርሱ ከእርዳታ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ጋር ባላቸው ቀጥተኛ ግንኙት አማካኝነት መሳሪያዎችን የሚያቀርቡ አገራት ናቸው::»


በተለይ በምግብ እርዳታ ረገድ፣ በሶስተኛው ዓለም ያሉ የእርዳታ ተጠቃሚዎች በከተማ ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች - ፖለቲከኞች፣ የኢንዱስትሪ ሰራተኞች፣ ቢሮክራቶች፣ ነጋዴዎች - እንጂ ከእርዳታው አብዛኛውን መጠቀም አለባቸው ተብለው የሚታሰቡት በገጠራማ አካባቢዎች ያሉ በጣም ደሃዎች በአብዛኛው ጥቂት ብቻ ነው የሚደርሳቸው::

ታዋቂው የፓን-አፍሪካ አቀንቃኝና ግራ-ዘመም ምሁር ታጁዲን ራህማን አበክሮ እንደሚከራከረው፣ እርዳታ የትኛ ውንም ማህበረሰብ ማልማት አይችልም፣ አላለማምም:: መጀመሪያውኑን ይህን ዓላ እውን ለማድረግ አይደለም የታቀደው:: ሰዎች የራሳቸውን እጣ ራሳቸው ለመወሰን እንዲቻላቸው ልማት የህዝብ ቀጥተኛ የጥረት ውጤት መሆን አለበት ምክንያቱም ማንም አካል ለእኛ ኑሮ ግዴታ የለበትም፤ ራሳችን ነን ግዴታ ያለብን:: ክርክሩ አፍሪካ እርዳታ ያስፈልጋታል ወይስ አያስፈልጋትም ሳይሆን የትና መቼ እንደሚያስፈልጋት ለመወሰን በጣም ደካም፣ የተሰነጣጠቀች እና የተጋለጠች መሆና ነው:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ እርዳታ እውነተኛ ያልሆኑ የተወሰኑ ለራሳቸው ህዝብ ተጠያቂ ሳይሆኑ በለጋሾች የገንዘብ ድጋፍና በውጭ ድጋፍ በሥልጣን እንዲቆዩ የተደረጉ መንግስታትን ፈጥሯል::

በውጭ እርዳታ ምክንያት ዘላቂ ልማትን ያሳካ ማሕበረሰብ አለ ብሎ ማንም ሰው መጠቆም አይቻለውም:: ልማት ዘላቂ መሆን ካለበት ከውስጥ እንጂ ከውጭ መሆን የለበትም:: እርዳታ የእርዳታ ጥገኝነትን እና አፍሪካ

ወደ ገፅ 23 ዞሯል

# አሜሪካ አጥብቃ የምትደግፋቸው ሁለት አዳዲስ ሀሳቦች



በዶናልድ ቡዝ
(አምባሳደር)

አሜሪካውያን የልደት ቀናቸውን በየዓመቱ በልዩ ፍቅር ያከብሩታል:: የወርኃ ጁላይ አራተኛ ው ቀን፣ «መንግስት ከሕዝብ፣ በሕዝብ፣ ለሕዝብ ነው» የማለውን ሐሳብ ያቀነቀኑት መስራች አባቶቻችንን ጥበብ የምንዘክርበት ቀን የመሆኑን ያህል፣ ልዩ ክብረ በዓልም ነው::

ከዩናይትድ ስቴትስ የነፃነት ቀን አዋጅ 56 ፈራሚዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ የሕግ ባለሙያዎች፣ ነጋዴዎች፣ የእርሻ ባለቤቶች አልያም ሌሎች ሃብት ያላቸው ባለሙያዎች እና ታዋቂ ሰዎች ነበሩ:: መሥራች አባቶቻችን ሐሳባቸውን በወረቀት ላይ ብቻ አልነበረም ያሰፈሩት:: ሕይወታቸውን፣ ነፃነታቸውን፣ ክብርና ዝናቸውን እንዲሁም አንጡራ ሐብታቸውን ሰውተውለታል:: የተናጠል የመብት ማረጋገጫ የሆነውን የነፃነት አዋጅ በመፈረማቸው በንጉሥ ጆርጅ ሣልሳዊ ዐይን ከሐዲያን ተደርገው ተቆጥረዋል::

ከእነርሱም ውስጥ ዘጠኙ በአብዮታዊው ጦርነት ውስጥ ተሳትፈው ከቆሰሉ በኋላ አልያም በእንግልት ለህልፈት ተዳርገዋል:: አምስቱ ተይዘው በከሃዲነት ተወንጅለው ስቅላት ተፈርዶባቸዋል:: አያሌዎች ወንዶች ልጆቻቸውን በጦርነቱ አጥተዋል፤ ብዙዎችም ቤታቸውን፣ ጥሪታቸውን እና መላ ሐብታቸውን ሰውተዋል::

ስለ ዩናይትድ ስቴትስ መሥራች አባቶች ሲወሳ አስደናቂው ነገር፣ እጅግ መሠረታዊ የሆኑትን ሰብዓዊ ነፃነቶች - ሕይወት ፣ ነጻነት እና ደስታን - ለመጎናፀፍ እና ጠብቆ ለማቆየት ሲሉ ሐብታቸውን እና ክብራቸውንም ጭምር መስዋዕት ለማድረግ የነበራቸው ፈቃደኝነት ነው::

እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የነፃነት እና ደስታ የማግኘ ት መብት አለው የሚለው የፀና እምነታቸው ዛሬ አሜሪካውያን ለግለሰብ ነፃነት በሚሰጡት ትልቅ ትርጉም እና እያንዳንዱ ሰው የራሱን ወይም የራሷን የወደፊት ዕጣ ለመወሰን መብት እና ችሎታ አለው በሚለው እምነታቸው ላይ በጉልህ ይንፀባረቃል:: ይህ ጽኑ እምነት ከስግብግብነት አልያም ከራስ ወዳድነት የመነጨ አይደለም:: ይልቁንም በሰብዓዊ መንፈስ ላይ እምነት ከማሳደር እና የግለሰብ ነፃነት ለእያንዳንዱ ወንድ እና ሴት ሲረጋገጥ አብሮም የሌሎችን ግለሰባዊ መብቶች ማክበርን ያስከትላል ከሚል እምነት የመነጨ ነው::

ፕሬዚዳንት ኦባማ ከዛሬ አንድ አመት ገደማ በፊት በጋና ዋና ከተማ፣ አክራ፣ ባደረጉት ታሪካዊ ንግግር የአፍሪካ የወደፊት ዕጣ በአፍሪካውያን እጅ ውስጥ እንዳለ አስረግጠው ተናግረዋል::

(ፕሬዚዳንት ኦባማ በንግግራቸው) የወደፊቱን (የአፍሪካ) ዕጣ ለመወሰን ቁልፍ የሆኑ የተወሰኑ መስኮችን ዘርዝረዋል:: እነርሱም **መልካም አስተዳደር** -- የመንግስታት አስተዳዳር ምን ያህል ለዜጎቻቸው ጥቅም ቆሟል የሚለው ጉዳይ፣ **የኢኮኖሚ ዕድል** -- ማለትም የግለሰቦች ጥረት፣ ተነሳሽነትና ሥራ ፈጣሪነት ምን ያህል የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና ዕድገት ለማምጣት ውሏል የሚለው፤ እንዲሁም **ሰላምና ፀጥታ** -- ማለትም አዳዲስ ግጭቶች እንዳይከሰቱ የመከላከል እና የተከሰቱትን ማስወገድ ችሎታችን ምን ያህል ነው የሚሉት ናቸው::

ዩናይትድ ስቴትስን የመሠረቷት ነባር ግዛቶች ከነፃነት በፊትም ቢሆን ጠንካራ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ልማድ ነበራቸው:: እኔ ባደኩበት የማሳቹሴትስ ከተማ፣ ዜጎች፤ ቀደምት አባቶቻቸው ከመቶዎቹ አመታት በፊት ሲያደርጉት እንደነበረው ሁሉ የከተማይቱ በጀት የሚዘጋጅበት እና ክልላዊ ህጎች የሚፀድቁበት የመዘጋጃ ቤት ስብሰባ ላይ ዛሬም ይሳተፋሉ:: እንዲህ ያለው የታችኛው ማህበረሰብ ትርምስምስ የበዛበት ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ይሄው (የአስተዳደር ስልት) አሜሪካውያን ከሌሎች የሃገራቸው ህዝቦች ጋር በመተባበር ጠንካራ የበለፀገች፣ ከአህጉር የምትቆጠር እና በምድር ላይ እንዳለ ማንኛውም አገር ሰፊ የህዝቦች ስብጥር ያለባትን አገር ለመገንባት ከሚያደርጉት ጥረት ጉን ለጉን የራሳቸውን መፅዒ እድል ለመወሰን አስችሏቸዋል::

የኢትዮጵያ ታሪክ ከአሜሪካ እጅግ የተለየ ነው:: በኢትዮጵያ የረዥም ዘመናት ታሪክ ውስጥ ዲሞክራሲ በአንፃራዊ አዲስ ጽንስ ሃሳብ ነው:: ወደፊት እንደምን ሊጐለብት ይችላል የሚለውን የሚወስኑት ኢትዮጵያውያን ናቸው::

ዩናይትድ ስቴትስ የትንንሽ ገበሬዎች አገር ሆና ነው የእድገት ጉዞዋን የጀመረችው:: በአሜሪካ ምስረታ ቀደምት አመታት ይካሄዱ የነበሩ የፖለቲካ ክርክሮች አገሪቱ ልትከተለው በሚገባት ልማት አቅጣጫ ላይ ያተኮሩ ነበሩ:: አሌክሳንደር ሐሚልተን በጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት ድጋፍ (ጥበቃ) የሚደረግለት የፋይናንስ እና የማምረቻ ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ ስለመሆኑ ሲከራከር፣ በአንፃሩ ቶማስ ጀፈርሰን ስልጣኑ ሆን ተብሎ የተገደበ ማዕከላዊ መንግስት ምንም አይነት ገደብ የማያደርግበት የገጠር ግብርና ልማት አስፈላጊ ስለመሆኑ ተከራክሯል:: ዛሬም የአሜሪካን ፖለቲካ የሚከታተል ማንኛውም ታዛቢ ስለፌደራል መንግስታችን ሚና መጠነ ሰፊ የሆነ ክርክር ሲካሄድ ይሰማል:: ግን ያኔ የነበሩትም ሆነ የዛሬዎቹ የጀፈርሰንም ሆነ የሐሚልተን ሐሳብ ደጋፊ የአሜሪካውያን፣ ማንኛውንም ህዝብ የ«ደስታ መሻት» ህልሙን እውን ለማድረግ የሚያስችለውን እድል ሲያገኝ ሊበለጽግ እንደሚችል ያምናሉ::

ኢትዮጵያ የምትከተለውን የእድገት አቅጣጫ እየተለመች ትገኛ ለች:: ከአጋሮቿ በሚደረግላት ድጋፍ፤ ኢትዮጵያ ዘመናዊ ኢኮኖሚ ቀጣይ ለማድረግ እና በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስፈልገውን የተማረ የሰው ኃይል እና መሰረተ ልማት በመገንባት ላይ ነች:: እነዚህ ጥረቶች መጠነ ሰፊ እድገት ለማምጣት ምን ያህል ውጤታማ ይሆናሉ የሚለው የሚወሰነው / በራሳቸው/ በኢትዮጵየውያን ነው::

ፕሬዚዳንት ኦባማ አክራ ላይ ባደረጉት ንግግር አሜሪካን በውጭ እርዳታ ላይ መጠነ ሰፊ እርዳታ እንደምታደርግ የመናገራቸውን ያህል፣ የስኬታችን እውነተኛ ምልክት አሜሪካ ምን ያህል ለሕዝቦች የዕለት ጉርስ የሚሆን እርዳታ የማይነጥፍ ምንጭ ነች የሚለው ጉዳይ ሳይሆን፣ ወደ አዲስ /የእድገት/ ምዕራፍ የሚያሸጋገር ለውጥ ለልጆቻችን በሙሉ እውን ልናደርግ የምንችለውን መፃዒ ዘመን የሚያሳካ ለውጥ እውን ለማድረግ የሚያስችል አቅም በመገንባት ረገድ ምን ያህል በአጋርነት ሰርተናል የሚለው መሆኑን አበክረው አስገንዝበዋል::

አሜሪካ አጥብቃ የምትደግፋቸው ሁለት ሃሳቦች ማለትም በአለም አቀፍ ደረጃ ርሃብን ማስወገድ እና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንዲሁም በአለም ዙሪያ መሰረታዊ ጤናን የማስፈን ዓላማዎች መሰረታዊ መነሻ ይህ አመለካከት ነው:: ኢትዮጵያ በሁለቱም ረገድ ቅድሚያ የሚሰጣት አገር ነች:: ይህን በተመለከተ ኢትዮጵያ መልካም የሚባል እርምጃ የተራመደች ሲኾን፣ እኛም ይህንኑ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ድጋፋችንን አጠናክረን መቀጠል እንሻለን::

የመጀመሪያው ፕሬዚዳንታችን የነበሩት ጆርጅ ዋሽንግተን «ውርክብ በበዛባቸው የውጭ ጉዳዮች ውስጥ ገብታችሁ አትዘፈቁ» የሚል ታላቅ ምክር ትተውልን አልፈዋል:: እርግጥ ቀደም ባለው ዘመን አሜሪካንን የማያዋስኗት ታላላቅ ውቅያኖሶችን አቋርጦ የሚመጣ የውጭ ጥቃት ወይም ወረራ ይኖራል ተብሎ ስለማይታሰብ፣ የሰጡትን ታላቅ ምክር ለመተግበር ያን ያህል አዳጋች አልነበረም::

በአንጻሩ ኢትዮጵያ እንዲህ አይነቱ የተፈጥሮ ጠለላ መቼም አግኝታ አታውቅም:: ይልቁንም አስደናቂ በሆነው የረዥም ዘመን ታሪኳ ሁሌም ድንበሯን ከአጥቂዎች ለመከላከል ተጋድሎ ስታደርግ መኖሯ ነው:: ዛሬም ኢትዮጵያ የዜጎቿን ህይወት እና ነፃነት፣ ባለችበት አስቸጋሪ ቀጠና ካሉ ፀረ ሰላም ኃይሎች ለመታደግ እየታገለች ትገኛለች:: ሁላችንም እንደምንገነዘበው ያለንበት ወቅት እንደበሽታ፣ የአየር ንብረት ለውጥ እና ሽብርተኝነት ያሉ ድንበር ዘለል ችግሮች የተረጋገጡበት ነው:: እነዚህ የወቅቱ ፈተናዎች ቀደምት አባቶች ሊከሰቱ ይችላሉ ብለው ሊገምቷቸው የሚከብድ ናቸው:: /ዛሬ/ ዩናይትድ ስቴትስ እነዚህን የወቅቱ ፈተናዎች ኢትዮጵያን ከመሰሉ ሌሎች የአለም ህዝቦች ጋር አጋር በመሆን መፍትሄ ልታበጅላቸው ቁርጠኛ አቋም ይዛ እየታገለች ትገኛለች::

በመጨሻም፣ ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ፕሬዚዳንት እና ሕዝቦች፣ ለዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንት እና ሕዝቦች፣ እንዲሁም እንደ ነፃነት ያሉ የጋራ እሴቶችን እና መጭውን ጊዜ የበለፀገና ሰላማዊ ለማድረግ ያለንን ቁርጠኝነት ለሚጋሩን የአገራት መሪዎችና ሕዝቦቻቸው ክብር ፅዋችን እንድናነሳ እጠይቃችኋለሁ::

**/ዶናልድ ኢ. ቡዝ፣ በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ሲሆኑ የአሜሪካ 234ኛ የነፃነት ቀንን ምክንያት በማድረግ ባለፈው ሰኞ በሸራተን አዲስ ያደረጉት ንግግር ነው::/**

ወደ ገፅ 23 ዞሯል

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ምንጊዜም የኢትዮጵያ

TRULY ETHIOPIAN

# ሐበሻ ቢራ ፋብሪካ አ.ማ

## የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ጥሪ



የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ **ቅዳሜ ሐምሌ 10 ቀን 2002 ዓ.ም** **ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ሒልተን ሆቴል** ስለሚካሄድ ባለአክስዮኖች በአካል ወይም በወኪሎቻችሁ በኩል ስብሰባው ላይ እንድትካፈሉ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

የሐበሻ ቢራ ፋብሪካ አክስዮን ማህበር በደብረብርሃን ከተማ የሚገነባውን ፋብሪካ በአጭር ጊዜ ውስጥ እውን ለማድረግ እንዲቻል የፋብሪካ ግዥ ለመፈፀም አለምአቀፍ ጨረታ ማውጣቱን ሲገልጽ ደስታ ይሰማዋል፡፡

በዚሁ አጋጣሚ የሐበሻ ቢራ ፋብሪካ ባለአክስዮን ለመሆን ለምትሹ ሁሉ እስከ ሐምሌ 10 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ የአክስዮን ግዥ እንድታጠናቅቁ ለመጨረሻ ጊዜ ግብዣችንን እናቀርባለን፡፡



አሁኑኑ የመሥራችነት ጥቅም የሚያስገኘውን አክስዮን ይግዙ!
እንዳያመልጥዎ!

ሐበሻ ቢራ!
ወገን የሚያኮራ!!

የአክሲዮን ሺያጭ ቢሮዎች አድራሻ ፡-

22 ማዞሪያ አክሱም ሆቴል ጎን ርብቃ ህንፃ 6ኛ ፎቅ ቢ.ቁ. 603/604. - ሜክሲኮ ጨለለቅ አልሳም ታወር (block A).
ቦሌ መድሃኒዓለም ቤ/ክ ፊት ለፊት ኢድናሞል ህንፃ 2ኛ ፎቅ ቢ.ቁ.211 - ፒያሳ እቴጌ ጣይቱ ሆቴል ግቢ ውስጥ.

- የኮሜርሻል ኖሚኒስ ቅርንጫፎች በሙሉ እና በቡና ኢንተርናሽናል ባንክ ፣ በወጋገን ባንክ ፣ በሕብረት ባንክ ፣

ስልክ ፦ 011-662 21 76 , 011-662 21 77 , 0911 51 23 51 , 0912 05 32 17 , 0911 23 00 25 , 0911 21 27 23

**www.habeshabreweries.com**

## የአቤቶ ወግ

አቤ. ቶኪቻው· abeto2007@yahoo.com

# «ኦ! ያያያ
# መድረክ እና መኢአድ ወደ ሰበር አመሩ»

ወዳጄ እንዴት ሰነበቱ? ክረምቱ እንዴት ይዞዎታል? «ባዶ ቤት በክረምት...» እያሉ እየዘፈኑ ነው፣ ወይንስ ለሀገሪቱ መልካም ገፅታ ሲሉ የሆድዎን በሆድዎ ይዘው «አትክልት ፍራፍሬ የቅባት እህሎች ሞልቷል በሀገራችን የምግብ ዓይነቶች» የሚለውን የጋሽ መሐሙድ ዘፈን እያንጎራጎሩ ነው? (በቅንፍ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ የቅባት እህል ለመልካም ገጽታ ግንባታ ብቻም ሳይሆን በሀገራችን የሞላ የተረፈ እንደሆነ መዘንጋት የለበትም:: ነገር ግን በሀገራችን የሞሉት እኒህ ሰብላ-ሰብሎች በቤታችን ሞልተው የሚተርፉት መቼ ይሆን? የሚለውን ጥያቄ የሚጠይቁ አንዳንድ ወገኖች አሉ::) ከቅንፍ ውጪ እነርሱን ብሎ ወገኖች! ድንቄም ቴ ወገን... ለመሆኑ ምን ጐደለባችሁ? ብለን እንገስፃለን::

«በዛን ዘመን ...» አለ ወዳጃችን፤ «በዛን ዘመን ጋሽ ጥላሁን የሰባ ሰባቱር ርሃብ አስመልክቶ «ዋይ ዋይ ሲሉ የርሃብን ጉንፋን ሲስሉ...» የሚለውን ዘፈን ዘፈነ:: ታዲያ ያኔ እንደ ዛሬ ፀሐይ አልወጣም ነበርና ደመናው መንግስት (ደርግ) እንዴት የሀገሪቱን (ያኔ መልካም ገጽታ የሚባለውን ቃል ለመጥራት የሚያስችል ደረጃ ላይ አልደረስንም ነበር) እናም እንዴት የሀገሪቱን ስም ታጐድፋለህ (ስንጠረጥር ማንን ለማሳጣት ነው? የሚል ጥያቄም ጨምረውበታል) በል ይሄን ዘፈን አስተካክል ተባለ:: ታድያ ጋሽ ጥሌ ምኑ ሞኝ ነው «ምግብማ ሞልቷል...» የተሰኘውን ዘፈኑን ዘፈነ አሉ» ብሎ አወጋን:: ማሳሰቢያ እዚህ ጨዋታ ውስጥ ሃሰት ቢገኝበት ፀሐፊው ኃላፊነቱን አይወስድም::

የሆነ ሆኖ፣ እርስዎ ክረምቱ እንዴት ይዞታል? ሞቅ ሞቅ ያለ ነገር ይውሰዱበት:: ከየት ይመጣል? ብሎ የጠየቀ ... ሊጠይቅ ያሰበ ... ሲጠይቁ እየሰማ ዝም ያለ ... ውርድ ከራሴ::

ዘንድሮ ትንሽ ከበድ ያለ ይመስላል:: ችግሩ እየዘነበ ያለው አዲሳባ እና አካባቢው ብቻ ነው:: በተለያዩ ክፍለ ሀገር ያሉ ወዳጆቼ እንዳቀበሉኝ ወሬ ከሆነ ከአዲሳባ ውጪ እዚህ ግባ የሚባል ዝናብ እየዘነበ አይደለም:: እናም አዲሳቦች ብርዱን ለመከላከል ጃኬት ያለው ጃኬቱን፣ ትዳር ያለው ትዳሩን፣ ሁለቱም የሌለው ካቲካላውን ደርቦ አዋኪውን ቅዝቃዜ ወደ እንከን የለሽ ሙቀት ለመቀየር ጥረት እያደረጉ ነው:: እርስዎስ?

እኔ የምለው ወዳጄ፣ ኳሱ እንግዲህ ሊያልቅ ነው:: ምን ይውጠን ይሆን? በኳሱ ሰሞን ሕፃን አዋቂው ሁሉ ከኳስ ውጪ ወሬ ያለው አይመስልም ነበር:: ድሮ ድሮ ኳስ የጐረምሶች እና የጥቂት አራዳ አባቶች ነበር:: ዛሬ ግን ሁሉም የዕድሜ ክልል፣ በሁሉም የሥራ ደረጃ፣ ሁሉም ፆታ፣ በሁሉም ሥፍራ የሚወራውና የሚሰማው ኳስ ኳስ ኳስ ሆኗል::

ዕድላዊት የትንሿ እህቴ ትንሽዬ ልጅ ነች:: ከተወለደች ሁለት ዓመት ከምናምን ወር ሆኗታል:: ኑሮ እና እንጉርጉሮ በተደባለቁበት በዚህ ወቀት ባትወለድ ጥሩ ነበር:: ነገር ግን እድለኛ አልነበረችምና ተወለደች:: ስለዚህ ምንም እንኳ ዕድለኛ ባትሆንም ቢያንስ ስሟን እንኳ ዕድላዊት እንበለው የሚል ስምምነት ላይ ቤተሰቡ ደረሰና ዕድላዊት ተባለች:: የሁለት ዓመቷ ሚጢጢ ዕድላዊት «ዋካ ዋካ.... አፍሪካ» እያለች ስትዘፍን ቢሰሟት የዘንድሮ ኳስ መንፈስ ሕፃን አዋቂ ሳይለይ በሁሉም ውስጥ መስረፁን ልብ ይላሉ:: ካቲካላ ቤት፣ ጠጅ ቤት፣ የወንዶች እድር፣ የሴቶች እድር፣ ቀበሌ፣ ወረዳ እና ክፍለ ከተማ ሳይቀር በዋካ ዋካ ዜማ ታጅቦ የመሰለ መንግስቱን ዘገባ እየሰማና ኢቴቪን እያየ ስለ ኳስ ያወራል፤ ስለ ኳስ ያስባል፤ ስለ ኳስ ይጨነቃል፤ ስለ ኳስ ይጠበባል:: እሰይ ይህ ኳስ ባይኖር ኖሮ ምን እንሰማ፣ ምን እናወራ፣ ምን እንዘፍን ነበር?

ነገ ኳሱ ይጠናቀቃል:: እስፔን ከሆላንድ የፍፃሜ ጨዋታ ያደርጋሉ ሁለቱም ቡድኖች ከዚህ በፊት የዓለም ዋንጫን አንስተው አያውቁም እናም ዛሬ የትኛ ውም ቡድን ቢያሸንፍ በዓለም እግር ኳስ አዲስ ታሪክ ይመዘገባል ማለት ነው:: በነገራችን ላይ የዘንድሮ ዓለም ዋንጫ ከዚህ በፊት ከተዘጋጁት ዓለም ዋንጫዎች በሙሉ ትኩረት በመሳብ ሶስተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል የሚል ዘገባ ሰምቻለሁ:: ሌላ በነገራችን ላይ በዘንድሮ ዓለም ዋንጫ ብራዚል ከውድድር በመውጣቷ የተነሳ ወደ አስራ ምናምን የሚሆኑ ባንግላዲሻውያን ሆስፒታል መግባታቸውን ሰምቻለሁ:: (በቅንፍ ራሴን እተቻለሁ:- ብዬ ብዬ ወጋችንን በስፖርት ክፍል ወዳጃችን አቤል የተዘጋጀ የስፖርት ዘገባ አስመሰልኩት አይደል?) ከቅንፍ ውጪ ይቅርታ ጠይቄ እቀጥላለሁ::

ረስቼው ...

አፈር ስሆን ወዳጄ አንድ ጊዜ ስለ ሀገር ውስጥ ስፖርታችን ትንሽ አውግተን ወደ ዋናው መስመር እንመለሳለን::

በሚቀጥለው ዓለም ዋንጫ ኢትዮጵያን ተሳታፊ በማድረግ ራዕይ የሰነቁ የውጪ ሀገር አሰልጣኝ መቅጠራችንን ሰምተዋል? እንዲሳካላቸው እንፀልያለን:: እርሳቸው በቴክኒክ እኛ በፀሎት ታምር ለመስራት እየታገልን ይቺን ያኽል ከተንደረደርን፣ እረ ወዳጄ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተጫዋቾች ምን ነክቷቸው ነው እግር ኳስ ሜዳውን ወደ ጦር ሜዳ የቀየሩት? ከአዲሱ አሰልጣኝ ቀጥሎ አሉን ብለን የተመካንባቸው እግር ኳስ ተጫዋቾቻችን «ጭንቅላት ለምን ይጠቅማል?» ተብለው ሲጠየቁ «ለቴስታ!» ብለው የሚመልሱ ቀሽሞች ሆነው በመገኘታቸው በእውነቱ ተሸማቀናል:: ስንት እንደሆኑ እንጃ እንጂ የተወሰኑ የጊዮርጊስ ተጫዋቾች አመክሮ ከሌለው በስተቀር ሁለት ዓመት ከሜዳ እንዲገለሉ ተወስኖባቸዋል:: እነዚህ ተጨዋቾች ከዚህ በኋላ ተመልሰው እግር ኳስ ተጫዋች የሚሆኑ አይመስሉኝም:: እንኳንስ እግር ኳስ «ቴስታ» የሚባል አዲስ ስፖርት ካልተፈለሰፈላቸው በስተቀር በሌላ ስፖርትም መገኘታቸውን እንጃ:: አሁንም ከስፖርት ጋር በተያያዙ የቀረኝ ነበር:: ነገር ግን በመጨረሻ ላይ አነሳዋለሁ:: አሁን ወደ ሌሎች ጉዳዮቻችን እናሳልጥ::

አሁን እግር ኳስ ጨዋታው ይጠናቀቃል:: «ሁሉም ነገር ወደ ኳስ ግንበር!» ተብሎ የታወጀው አዋጅ ፍፃሜው ነገ ነው::

ስለዚህ ኮሜንታተሮቻችን ፊታቸውን ወደ ወቅታዊ እና አገራዊ ጉዳዮቻችን አዙረው «ኦ ያያያ መድረክ እና መኢአድ እየተቀባበሉ ነው ... ወደ ሰበር ሰሚ ሄዱ ... ኢንስትራክተር እንዴት ነው፤ ውጤት የሚያገኝ · ይመስልዎታል? ... ኦ ያያያ ያጠራጥራል አሉ ኢንስትራክተር:: አሁን ኳስ በኢህአዴግ እጅ ነች...» በማለት ለፖለቲካችን ጆሮ እንድንሰጥ ይረዱናል የሚል እምነት አለኝ::

ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች ከተነሳ አይቀር፣ ባፈው ሳምንት ውስጥ ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና ለአንድ ጋዜጣ የሰጡትን አስተያየት ሰምተዋል?

«ባለፈው ምርጫ 97 መንግስት ቢያንስ ፈሪሃ እግዜር እና ፈሪሃ ፈረንጅ ነበረው ዘንድሮ ግን ሁለቱም አልነበሩትም!» የሚል ንግግር ተናግረዋል:: ታዲያ እኔ ይህንን እንዳነበብኩ ምን እንዳልኩ ያውቃሉ? «እኛ ፍርሃት የሚባል አልፈጠረብንም:: ድሮም ቢሆን በዘጠና ሰባቱ ምርጫ እንፈራ የነበረው ፈረንጅን ሳይሆን ድህነትን ነበር:: ሰዎች እርዳታቸውን ካቋረጡ ድህነቱ ይጨክንብናል ብለን ነበር:: ዛሬ ግን ምቀኛን ደስ አይበለው ድህነትንም መፍራት ትተናል!» አልኩኛ:: እንዴት ነው ይቺ ንግግሬ በሚቀጥለው ዓመት የልማት አርበኛ ተሸላሚ የምታደርገኝ አይመስልዎትም? አንዳንድ የእኔን መልካም ሲያዩ ዓይናቸው የሚቀላ የህብረተሰብ ክፍሎች «በወሬ ከምባል የልማት አርበኛ፣ ይሻለኛል ቢቀር ሳልበላ ልተኛ» ሊሉ እንደሚችሉ እጠረጥራለሁ:: ጠርጥሬም እመልሳለሁ፣ እንደማንም ኪራይ ሰብሳቢ ከመሆን ወሬ በስንት ጣዕሙ!

ስለ ኪራይ ሰብሳቢ ካነሳን አይቀር፣ አዲሳባ አስተዳር ባለፈው ዓመት «የተማሩ» ብሎ የቆጠራቸው አዳዲስ ምሩቃን ላይ ባደረገው ግምገማ፣ ተቀጣሪዎቹ በመሉ ለማለት ይቻላል «ኪራይ ሰብሳቢ ሆነው ተገኝተዋል::» ስለዚህ እኒህን ሠራተኞች ከኪራይ ሰብሳቢ አስተሳሰባቸው ለማላቀቅ መፍትሔው ወይ ፀበል ማስጠመቅ አልያም ከስራ ማስለቀቅ ሆኖ ተገኝቷል እየተባለ በከተማው አስተዳደር አካባቢ እየተወራ ነው:: ይህንን የሰማ አንድ ጽንፈኛ ወዳጄ «ድሮውንም በዓመቱ መጀመሪያ ሥራ የቀጠራችኋቸው ለምርጫው ውጤት ነበር:: ዛሬ የምርጫ ውጤታችሁን ስታውቁ ልታባርሯቸው ነው?» ሲል ሲጠይቀኝ እሱን ራሱንም በኪራይ ሰብሳቢነት ለመፈረጅ ተገድጃለሁ::

ስለ ምርጫ ከተነሳ አይቀር፣ በቃ የምርጫው ነገር አለቀ ማለት ነው? ወይስ፣ እውነትም ወይስ በፓርላማው አንድ አንድ ወንበር ያገኙት መኢአድ እና መድረክ የፍርድ ቤት ክሳቸው ውጤት ያመጣ እና «ምርጫው ይደገም» ይባል ይሆን?

በነገራችን ላይ፣ በቤኒሻንጉል መኢአድን ወክለው የፓርላማ ወንበር ያገኙት ግለሰብ አሁንም «እናት ድርጅታቸው» መኢአድ አላውቆትም እንዳላቸው ነው ወይስ መቸስ ምን ይደረጋል ብሎ አመነላቸው? አንዳንዶች «ሰውየው የመኢአድ እውነተኛ ልጅ መሆናቸው በ«ዲ.ኤን.ኤ» ምርመራ መጣራት አለበት» በማለት እየተቹ ነው:: ትችቱን ትተን ቁም ነገር እናውራ፣ እውነት ግን ሰውየው መኢአድ እስከመጨረሻው አላውቅም ካላቸው ምን ሊሆኑ ነው? ይህን ጉዳይ ያማከርኩት አንድ ወዳጄ ምን እንዳለኝ ያውቃሉ? «ሌላማ ምን ይደረጋል ወላጆቻቸው ከከዷቸው እንደፈረደባቸው እናንተ በጉዲፈቻ ታሳድጋላችኋ!» አለኛ:: በማያገባኝ ጉዳይ ገብቼ ራሴን ለአሸሙር በማጋለጤ እየተፀፀትኩኝ ሌላ ወሬ እንዳይቀጥል ፊት ነሳሁት::

«ኦ ያያያ መድረክ እና መኢአድ እየተቀባበሉ ነው ... ወደ ሰበር ሰሚ ሄዱ ... ኢንስትራክተር እንዴት ነው፤ ውጤት የሚያገኙ ይመስልዎታል? ... ኦ ያያያ ያጠራጥራል አሉ ኢንስትራክተር:: አሁን ኳስ በኢህአዴግ እጅ ነች...»

### በመጨረሻም አስካሉካን

አስካሉካን የተባለ «ሰው ላኪ ድርጅት» ለደቡብ አፍሪካ ኳስ «በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የምስራቅ አፍሪካ ሁሉ ውክልና አለኝ» በማለት «የእግር ኳስ አፍቃሪው» የህብረተሰብ ክፍልን ወደ ደቡብ አፍሪካ በመላክ «የኳስ ጥማቸውን» እንዲቆርጡ አደርጋለሁ ብሎ የአገሬን ደሃ ገንዘብ ሰብስቦ ሲያበቃ ከፋዮቹ እንኳንስ ደቡብ አፍሪካ ይቅርና ሚሊኒየም አዳራሽ እንዳይገቡ ሲያጉላላቸው መክረሙ ሳያንስ ብራቸውን «እምጿ ቀሊጦ!» እንዳላቸው ሰምተናል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ወዳጄ የድርጅቱን «ሌብነት» ካደነቀ በኋላ «እግር ኳስ አፍቃሪዎቹንም» ተችቷል:: እንዲህም አለ፣ «እግር ኳስ አፍቃሪዎቹ የሚሄዱት ለኳስ አለመሆኑ አስታወቀባቸው» አለን:: እንዴት አልነው? «መንገደኞቹ የኳስ ፍቅር ያላቸው ለማስመሰል ቱታ የለበሱ ቢሆንም ቅልጥ ባለ የኳስ ጨዋታ ጨዋታውን ትተው «ብራችን ተበላ» የሚል አቤቱታ ላይ መገኘታቸው የኳስ ፍቅርም የአገር ፍቅርም እንደሌላቸው አስታውቆባቸዋል» አለን:: እንደ ወዳጃችን ሀሳብ ከሆነ መንገደኞቹ የኳስ ፍቅር እንዳላቸው ለማሳወቅ ቢያንስ እግር ኳሱን በቲቪ እየተመለከቱ አቤቱታቸውን በእረፍት ሰዓት ቢያሰሙ የተሻለ ነበር::

ወዳጄ የሰማነውን በልቦናችን ያሳድርልን! አሜን አማን ያሰንብተን!

ዲፌንደር ጋዜጣ
በአዲስ መልክ ዘወትር ማክሰኞ መውጣት የምትጀምር መሆኑን እንገልፃለን
የዲፌንደር ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# የቦሌ መድኃኒአለም ጉባኤና የሐውልት መተከል ውዝግብ



በ2001 ሐምሌ ወር መጀመሪያ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ውስጥ ከባድ ውዝግብ ተፈጥሮ ነበር:: የውዝግቡ መነሻ በፓትሪያርክ አቡነጳውሎስና የአዲስ አበባ አገረ ስብከት ስራ አስኪያጅ በነበሩት በአቡነ ሳሙኤል መካከል ነበር:: ዛሬ ልክ በአንድ አመቱ ደግሞ በሁለት ምክንያቶች ውዝግብ ተፈጥሮአል:: አንደኛው የፓትሪያርኩን 18ኛ ዓመት በዓለ ሲመትን ምክንያት በማድረግ በቦሌ መድሀኒአለም ይተከላል የተባለው ሐወልት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እነ ዲያቆን በጋሻውና 18 ባልደረቦቻቸው በአዲስ አበባና በተለያዩ የክልል ከተሞች ያዘጋጁቸው ጉባኤዎችና እነዚህ ጉባኤዎች ደግሞ ከቤተክርስቲያን ቅጥር ጊቢ ውጪ የተደረጉ በመሆናቸው መጋቢት 4 ቀን 2002 ዓ.ም ውሳኔና መመሪያ ተላልፎ ነበር:: ሚያዚያ 8 ቀን 2002 ዓ.ም ደግሞ የቤተክርስቲያኗ ሰባኪያንና ዘማሪያን በተገኙበት ቀጣይ ውይይት ተደርጎ «አጉራ ዘለል ሰባኪያንና ዘማሪያን ከቤተክርስቲያን ሕግ እና ስርዓት ውጪ የሌላውን መብት የሚፃረር ጉባኤ እንዳያደርጉና በቤተክርስቲያን ስብከት ወንጌል ሐዋሪያዊ ተልእኮ መምሪያ ቁጥጥር መስመር ውስጥ ሆነው ስብከት እንዲያካሂዱ ውሳኔ ተላለፈ:: ከዚህ በኋላ የስብከት ወንጌል ሐዋሪያዊ ተልእኮ መምሪያ ኃላፊ አባ ኃ/ማርያም መልአከ «..ከዚህ በኋላ የአዳራሽ ጉባኤ ሊኖር አይችልም» በማለት ጉዳዩ መፍትሄ እንዳገኘ አሳውቀው ነበር::

ከዚህ ውሳኔ በኋላ እነ ዲያቆን በጋሻው ደሳለኝ በድሬዳዋ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (ከጠቅላይ ቤተክህነት ፈቃድ ውጪ) ጉባኤ በማዘጋጀት ማህበረ ቅዱሳንን አወገዙ::

በተመሳሳይ መልኩ በአሰበ ተፈሪ ቅድስት ልደታ ማርያም ቤተክርስቲያን ጉባኤ ቢያዘጋጁም ቀደም ሲል በተላለፈው ውሳኔ መሠረት እንዲታገድባቸው ተደረገ:: የዛሬ ሦስት ሳምንት ደግሞ በአዋሳ ከተማ ከ«ተስፋ ኪዳነ ምህረት» ማህበር ጋር በመተባበር ለማድረግ ያቀዱት ፕሮግራም ተሰረዘባቸው::

ከዚህ በኋላ ነበር «እነ ዲያቆን በጋሻው አፈንግጠው ወጥተዋል» በማለት የስብከት ወንጌል መምሪያ ኃላፊ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ማርቆስ በሚዲያ መግለጫ የሰጡት::

ይህ መግለጫ በተሰጠ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ግን በቤተክርስቲያኗ የስብከት ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልእኮ መምሪያ የክብር ስፖንሰርነት እነዚህ «አጉራ ዘለልና አፈንጋጭ የተባሉ ሰባኪያንና ዘማሪያን ዛሬና ነገ በአዲስ አበባው ቦሌ መድኃኒአለም ቤተክርስቲያን ጉባኤ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ይገኛሉ::

ለመሆኑ ይህ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ 18ኛ ዓመት በዓለ ሲመት ምክንያት በማድረግ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን ዛሬና ነገ ይደረጋል የተባለው ጉባኤ እንዴት ሊፈቀድ ቻለ? ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መንበረ ፓትሪያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የተፃፈ ደብዳቤ እንደሚያሳየው የፓትሪያሪኩን 18ኛ ዓመት በዓለ ሲመት ምክንያት በማድረግ ብፁአን አባቶች፣ የመንግስት ባለስልጣናት፣ አምባሳደሮች የቤተ-ክህነት የመምሪያና የድርጅት ኃላፊዎች... በተገኙበት ዋዜማው በደመቀ ሁኔታ ከቀኑ 10:00 ሰአት ጀምሮ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኒአለም በደማቅ መንፈሳዊ ስነ-ስርዓት እንደሚከበር በመግለፅ ስማቸው የተገለፀው ዘማሪያን በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት እንዲገኙ ጥሪ ይደርጋል:: ሆኖም በዚህ ጉባኤ ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ ከተደረገላቸው ዘማሪያንና ሰባኪያን መካከል ቀደም ሲል እንዲታገዱ ውሳኔ የተላለፈባቸው ስለሚገኙበት የስብከት ወንጌል መምሪያ በማያውቀው መንገድ የተዘጋጀ ነው ሲሉ ተቃውሞ አስምተዋል::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ስብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልእኮ መምሪያ የክብር ስፖንሰርነት ይካሄዳል ስለተባለው ጉባኤ አስተያየት እንዲሰጡ አውራምባ ታይምስ ያነጋገራቸው የመምሪያው ኃላፊዎች ግን «ስለ ጉባኤው ምንም የምናውቀው ነገር የለም» ብለውናል:: የቦሌ መድኃኒአለም ካቴድራል ሰበካ ጉባኤ ም/ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ትዕዛዙ ኩሪ እንዲሁም የሰበካ ጉባኤው አባላት የሆኑት ወ/ሮ ሙሉአለም ጀምበሬ እና ወ/ሮ እታለም ናደው በበኩላቸው ለደብሩ አስተዳዳሪ ለመላከ ቆሞስ አባ ዘርአዳዊት ኃይለስላሴ በፃፉት ደብዳቤ ከሰበካ ጉባኤ አባላት ዕውቅና ውጪ የካቴድራሉ የስራ ባለደረባ ባልሆኑ ግለሰቦች ትዕዛዝ የሚደረገውን እንቅስቃሴ በፅኑ እንደሚቃወሙ ገልፀው «ብዚህ ሁኔታ አገልግሎታችንን ለመቀጠል የሚያዳግተን በመሆኑ የምንወደው የሰበካ ጉባኤ ስራችንን ከሐምሌ 2 ቀን 2002 ጀምሮ የምንለቅ መሆኑን ከመንፈሳዊ አክብሮት ጋር እንገልፃለን» ይላል::

ለኮሚሽነሩ ስንብት ዋናው ምክንያት «ከተመደቡበት ጊዜ ጀምሮ የፈፀሙትና የሚፈፅሙት አስተዳደራዊ ተግባር ለኮሚሽኑ ከተሰጠው መተዳደሪያ ደንብ ውጪ ሆኖ በመገኘቱ» እንዲሁም «ባደረብዎት የጤና መታወክ ምክንያት የኃላፊነቱን ስራ ሊወጡ ባለመቻልዎ» ይላል:: እኚህ ኮሚሽነር ከአንድ ወር በፊት ሀላፊነታቸውን በአግባቡ በመወጣት ተሞግሰው ከብፁዕ ፓትሪያርኩ እጅ ሽልማት መቀበላቸው ይታወሳል::

አያይዘውም የተባለው (የፓትሪያርኩ) ሐውልት በዚሁ ካቴድራል የሚቆም ከሆነ ከኦርቶዶክስ ኃይማኖታዊ እምነት ጋር እንደሚጋጭ በደብዳቤያቸው ላይ ጠቅሰዋል:: ስለ ጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጡ አውራምባ ታይምስ በስልክ ያነጋገራቸው የቦሌ መድኃኒአለም ካቴድራል አስተዳዳሪ አባ ዘርአዳዊት ኃይለስላሴ በበኩላቸው «ዝርዝር መረጃ በስልክ ለመስጠት ይቸግረኛል» ካሉ በኋላ በነገው ዕለት በቤተክርስቲያኑ በሚከናወን ስነ-ስርዓት ላይ ተገኝታችሁ መንፈሳዊውን ዝግጅት በመከታተል መረጃ ብታገኙ ይሻላል ሲሉ ገልፀውልናል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መረጃ እንዲሰጠን ያነጋገርነው ዲያቆን በጋሻው በበኩሉ «ስለ ምንም አይነት መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አይደለሁም» ብሏል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ በትናንትናው ዕለት የአዲስ አበባ አገረ ስብከት ስራ አስኪያጅ የሆኑት ሊቀ መምራን ፋንታሁን ሙጬ የአዲስ አበባ የደብር አለቆችና ፀሐፊዎች ጋር ባደረጉት ስብሰባ የቅዱስ ፓትሪያሪኩን 18ኛ ዓመት በዓለ ሲመት ምክንያት በማድረግ ለብጹዕ ፓትሪያርኩ በተለያዩ ወገኖች የተለያዩ ስጦታዎች እንደሚሰጡ በማስታወስ ዋጋው 3.5 ሚሊዮን ብር የሆነ መኪና ገዝቶ ፓትሪያሪኩን ለመሸለም ይረዳ ዘንድ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን (ከፍተኛ ገቢ ያለው 60 ሺህ ብር ዝቅተኛ ገቢ ያለው ደግሞ 45ሺህ ብር) በማዋጣት እስከ ሐምሌ 30 2002 ዓ.ም ገቢ እንዲያደርግ መመሪያ ሰጥተዋል::


በተያያዘ ዜና የዛሬ አመት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ውስጥ ከተፈጠረው ውዝግብ ጋር በተያያዘ ሲኖዶሱ ከኃላፊነት ያገዳቸውና በፓትሪያሪኩ ውሳኔ ኃላፊነታቸውን ይዘው እንዲቀጥሉ የተደረጉት የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ኮሚሽነር አራጋው ጥሩነህ ከትናንት በስቲያ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፊርማ በቁጥር ል/ጽ/551/106/2002 በተፃፈ በብዳቤ ከኃላፊነታቸው ተነስተዋል:: በደብዳቤው ላይ እንደተገለፀው ለኮሚሽነሩ ስንብት ዋናው ምክንያት «ከተመደቡበት ጊዜ ጀምሮ የፈፀሙትና የሚፈፅሙት አስተዳደራዊ ተግባር ለኮሚሽኑ ከተሰጠው መተዳደሪያ ደንብ ውጪ ሆኖ በመገኘቱ» እንዲሁም «ባደረብዎት የጤና መታወክ ምክንያት የኃላፊነቱን ስራ ሊወጡ ባለመቻልዎ» ይላል:: እኚህ ኮሚሽነር ከአንድ ወር በፊት ሀላፊነታቸውን በአግባቡ በመወጣት ተሞግሰው ከብፁዕ ፓትሪያርኩ እጅ ሽልማት መቀበላቸው ይታወሳል::

ከዚህ በተጨማሪ ከሦስት ሳምንት በፊት በሐዋሳ ሊደረግ ታቅዶ ከተሰረዘው የነ ዲያቆን በጋሻው ጉባኤ ጋር በተያያዘ የሐዋሳ ቅዱስ ገብርኤል ገዳም አስተዳዳሪ የሆኑት ቆሞስ መላከ ምህረት ወልደ ሳሙኤል ከኃላፊነታቸው ተነስተው በምትካቸው ሌላ ኃላፊ እንደተሾሙ ለማወቅ ተችሏል::

ከሦስት ሳምንት በፊት ፕሮግራም ተይዞለት እንዲሰረዝ የተደረገው የሐዋሳው ጉባኤ አዘጋጅ ተስፋ ኪዳነምህረት ማህበር ምክትል ሊቀመንበር አማኑኤል ሰጌሳ በትናንትናው ዕለት ለአውራምባ ታይምስ በስልክ እንደገለጸው «የሐዋሳው የሰኔ 12 እና 13 ጉባኤ ሊሰረዝ የቻለው የገዳሙ አስተዳዳሪ የሆኑት አባ ወልደ ሳሙኤል ፍቃደኛ ባለመሆናቸውና የተለየ የጥቅም ጥያቄ አቅርበው ፍቃደኛ ባለመሆናችን ነው:: አሁን ግን እሳቸው ተነስተው ሌላ አባት በቦታው ላይ ስለተተኩ ጉባኤውን ሐምሌ 19 በስኬት እንድናከናውን ተፈቅዶልናል» ብሏል::

**ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ**

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com




ዳሰሳ

በጆአፍም ጋስካር

# ማኅደረ ጠባቡ «የእውቀት ማኅደር»


***የመጽሐፉ ርዕስ:- የእውቀት ማኅደር (ቁጥር አንድ)***
***ደራሲ:- ዶ/ር ኬኬ***
***የገጽ ብዛት:- 200***
***የታተመበት ወቅት:- 2002***
***ይዘት:- (???)***
***ዋጋ:- 20 ብር***

አንድ ሰው በትምህርት ወይም በተሞክሮ ያገኘውን መረጃ፣ ግንዛቤ፣ ክህሎት ወዘተ ሌሎች ሰዎች እንዲጠቅሙ በሚል ሀሳብ እውቀቱን ያጋራል:: ተጋሪውም ሰው ተጠቃሚ ይሆናል፤ የአጋሪውን እውቀት ካመነበትና ያስፈልገኛል ብሎ ካመነ የራሱ ያደርገዋል:: በመሆኑም የአእምሮው የእውቀት ማኅደር መስፋቱ እርግጥ ነው:: ምናልባትም የእውቀት ክምችቱ የጥበብ መንገድን ሊጠቁመው ይችላል:: ያወቁትን ለሌሎች ማካፈል ሌላው ቢቀር ያስመሰግናል:: እናም መጽሐፉ ምንም ይሁን ምን ይህን ዳሰሳውን የምጀምረው በቅድሚያ ደራሲ ዶ/ር ኬኬን «አመሰግናለሁ!» በማለት ነው:: ወደዋናው ነጥቤ ልለፍ::

የአንዲት አገር ጠቅላላ ሥረ-መሰረት «በአለት ላይ የተመሰረተ ነው» እንድንል ከሚያስችሉን መመዘኛዎች መካከል በመላ አገሪቱ የሚሰራጩ የሕትመት ውጤቶች - ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ ልብ-ወለድና ኢ-ልብ-ወለድ መጽሐፍት ወዘተ - በዋናነት ይጠቀሳሉ:: ለማንኛውም አገር የትምህርት ሥርዓት ወይም ፖሊሲ ስከታማነት ብቁ መምህራን በጣም አስፈላጊ እንደመሆናቸው አይጠራጥርም:: እንዲሁም ደረጃቸውን የጠበቁ መጽሐፍትም ያላቸው አስተዋፅኦና አስፈላጊነት ከመምህራን እኩል ቢሆን እንጂ በጭራሽ የሚያንስ አይደለም:: ያ አስተዋፅኦቸውና አስፈላጊነታቸው በአገሪቱ ውስጥ ከታችኛው እስከ ላይኛው ባሉ የትምህርት እርከኖች ድረስ በመደበኛነት ለተቀመጠላቸው ዓላማ የሚውሉ መጽሐፍት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን እንድናረጋግጥ የሚያስገድዱን ናቸው:: በተመሳሳይ፣ መደበኛውን የማስተማር - መማር ሂደት በአጋዥነት ወይም በተጓዳኝነት ልንገለገልባቸው የሚችሉና የምንገለገልባቸው መጽሐፍትም እንደ መደበኛዎቹ መጽሐፍት አቻ የሆነ ደረጃ ሊኖራቸው የሚገባ ይመስለኛል:: እናም ያን ማረጋገጥ ከተቻለ በእርግጥም አገሪቱ በአለት ላይ የተመሰረተች ናት ለማለት ድፍረቱ ይኖረናል::

የላይኛውን ምልከታዬን እንድጽፍ መነሻ የሆነኝ ምክንያት ባለፈው ሳምንት በእጄ የገባው «የእውቀት ማኅደር» የሚል ርዕስ የተሰጠው መጽሐፍ ነው:: እናም ከመጽሐፉ የታዘብኳቸውን የተወሰኑ ነጥቦችን እያነሳሁ የታዘብኳቸውን ላካፍላችሁ::

የአንድ መጽሐፍ ይዘት በማንኛውም ተደራሲ ትኩረት የሚደረግበት ይመስለኛል:: የይዘት ምርጫ ከግለሰብ ግለሰብ ሊለያይ ይችላል:: «የእውቀት ማኅደር» በአንድ ይዘት ላይ ብቻ ያተኮረ አልመሰለኝም:: ስለይዘት




መጽሐፉ የሚነግረን ምንም ነገር የለም:: በየትኛውም መጽሐፍ ውስጥ ስለመጽሐፉ ጠቅለል ያለ መረጃ የሚሰጠን በመግቢያ ወይም መቅድም እንኳን የለውም:: ምናልባት ይህን በተመለከተ ለአንባቢ የተቀመጠ የይዘት ጠቋሚ መረጃ ቢኖር መጽሐፉ «እጅግ በጣም አስገራሚ እውነታዎች፣ አስደናቂ ክስተቶች፣ አስደማሚ ታሪኮች፣ ጠቃሚ መረጃዎች፣ ሌላም ሌላም» ያካተተ ስለመሆኑ በገጽ 1 ላይ የሰፈረው ነው::

ሁለት መቶ ገጾችና አስራ አራት ክፍሎች በያዘው በዚህ መጽሐፍ፣ በርካታ ከሳይንስ፣ ከታሪክ፣ ከፖለቲካና ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ መረጃዎች ተካተዋል:: በሕያወት ያሉና የሌሉ የፖለቲካ፣ የሃይማኖት ቋማት እና የአገራት መሪዎች ታሪክ፤ የተለያዩ እንስሳት እና እፅዋት ሥነ-ተፈጥሮ፤ ስለዓለም ቅርሶች፤ ስለሳይንሳዊ ምርምሮች፣ ውጤታቸው፣ ስለተመራማሪዎቹ የመጨረሻ እጣ፤ ስለሁለንተናው ዓለም፣ ስለማዕድናት ... ቅንጭብ ቅንጭ በሆነ መልኩ ተዘርዝረዋል:: «ምንም የቀረ የለም» ማለት ይቻላል::

በእንደ መጀመሪያ መረጃ ሰጭነት፣ መጽሐፉ ለአንባቢ የራሱ ጥቅም የሚያበረክት መሆኑ እርግጥ ነው:: «ጠቅላላ እውቀት» ልናገኝበት እንችላለን:: ግርምትን የሚፈጥሩና የሚያዝናኑ መረጃዎችም አሉት:: ለምሳሌ፣ ሰውና ጊንጥ ስቃይ ሲበዛባቸው ራሳቸውን በራሳቸው እንደሚገድሉ፤ ከድመት ሌላ አቦሸማኔ «ሚያው» የሚል ድምጽ ማውጣቱን፤ ከሰው ሌላ በክፍያ ወይም በስጦታ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ከሚፈጽሙ ጥቂት እንስሳ ውስጥ ፔንጉዊን አንዱ መሆኑን፤ በ1998 ዓ.ም በኢኳዶር አቪስ ደን ውስጥ የተገኘችው አንቲፓ አቪስ ካኒስ ረድግሌይ የሚል ሳይንሳዊ ስያሜ የተሰጣት ወፍ የምታሰማው ድምጽ የውሻ ድምጽ መሆኑን፤ የምድራችን ረጅሙ ተራራ በአትላንቲክ ውቂያኖስ ውስጥ የሚገኘው ማውናኪ (ነጩ ተራራ) መሆኑን ናእና ከመሰረቱ እስከ አናቱ ጫፍ ያለው ሽቅብ ቁመት 10ሺህ 25 ሜትር እንደሆነ፤ «Set» የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል 463 ትርጉሞች ያሉት መሆኑ፤ የጸጉር ቅማል ከቆሻሻ ይልቅ በንጹህ ፀጉር ላይ መኖርን መምረጡን፤ የአንጎላችን ክብደት ከጠቅላላ የሰውነታችን ክብደት ሁለት በመውን ብቻ ቢሆንም ከሰውነታችን ውስጥ ከሚመነጨው ሙቀት ሃያ በመቶውን የሚጠቀም መሆኑን፤ ከመኮሳተር ይልቅ መሳቅ እንደሚቀልና ምክንያቱ ደግሞ ለመኮሳተር 43 ጡንቻዎች፣ ለመሳቅ 17 ጡንቻዎች በእንቅስቃሴ ላይ መዋላቸው መሆኑን እና ሌሎች ያስገረሙኝ መረጃዎች ናቸው::

ሆኖም አንድ መጽሐፍ የፈለገ አዝናኛና አስተማሪ ነው ተብሎ ቢታሰብ፣ «እጅግ አስገራሚ፣ አስደናቂ» በሚሉ ገላጭ ቃላት ቢሞካሽና ቢደምቅ፣ በውስጡ ያለ አንድ መልዕክት እንኳን የሚታወቅን ተጨባጭ ፍሬ ነገር የሚክድ መረጃ በውስጡ ካካተተ ለስራው የሚገባውን ክብር እንዳንሰጥ ሊያደርገን ይችላል:: መጽሀፉንም ተዓማኒነት የሌለው ሊያደርግብንይችላል:: መጽሐፍ እንደመጽሐፍነቱ ሊኖረው የሚገባውን ድርሻ የሚያሳጣው ይሆናል:: ደራሲው ለአንባቢ ክብር የሌለው፣ ለገንዘብ ብቻ በሚል መጽሀፉን ያሳተመ ወዘተ የሚሉ ውጤቶችን ያስከትላል::

በ«የእውቀት ማኅደር» ውስጥ የተወሰኑ በዘፈቀደና ካለጥንቃቄ እንደ ትክክለኛ መረጃነት የተካተቱ ስህተቶችን ይመለከታሉ:: ለምሳሌ:-

-በገፅ 160፣ ስለዓለም አገራት ብሔራዊ አርማ በሚዘረዝረው ሰንጠረዥ ውስጥ ኢትዮጵያ ተጠቅሳለች:: ሆኖም የኢትዮጵያ ብሔራዊ አርማ ተብሎ የተጠቀሰው የይሁዳ አንበሳ ነው:: ደራሲው ኢትዮጵያ አርማውን ትጠቀምበትየነበረበትን ወቅት ቢጠቅሱ ኖሮ ምናልባት ትክክል ነው ብለን እንቀበላቸዋለን:: ሆኖም አልጠቀሱልንም፤ በክፍል አስራ ሶስት፣ «የዓለም መንግስታት እና አገራት መሪዎች» በሚል ርዕስ ስር ባለ አንድ ትልቅ ሰንጠረዥ ውስጥ (ከገጽ 187 - 197) «የአገራት መሪዎች» ዝርዝር ተቀምጧል:: መሪዎች ናቸው ተብለው የተጠቀሱት ሰዎች ያላቸው (የነበራቸው) ማዕረግ ተሰጥቷል:: በአመራርነት የቆዩበት ዘመን አልተጠቀሰም:: እዚህ ላይ ከምንም በላይ ያስገረመኝ፣ በሕይወት የሌሉ «የቀድሞ» ተብለው መገለፅ የነበረባቸው አሁንም በህይወት እንዳሉና በነበራቸው የመሪነት ማዕረግ ላይ አሁንም እንደሚገኙ ተደርገው መገለፃቸው ነው:: በሕይወት ያሉ ሆኖም ከአገር መሪነታቸው የተነሱም አሉ:: ሌላም አለ፤ በጭራሽ አገር መርተው የማያውቁ ሰዎች ስም የመሪነት ማዕረግ ተሰጥቷቸዋል:: ምሳሌ:-

- መጽሐፉ ክጋሌማ ሞትላንቴ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝደንት መሆናቸውን አስቀምጧል:: ክጋሌማ ሞትላንቴ ጃኮብ ዙማ አገሪቱን መምራ ከመጀመራቸው በፊት የነበሩና የታቦ ምቤኪ ተተኪ ፕሬዝዳንት ነበሩ:: ምናልባት አገሪቱን እስከአሁን ድረስ በፕሬዝዳንትነት የመሩ ሰዎች ስም ዝርዝር ቢካተት ኖሮ የተባልነውን እንቀበል ነበር (ተመሳሳይ አመክንዮ በሰንጠረዡ ለተካተቱ ሌሎች ሰዎችም መጠቀም እንችላለን):: የቀድሞው የብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ጎርደን ብራወን አሁንም ሥልጣናቸውን እንደያዙ ተደርገው አሉ፤ በአውሮፕላን አደጋ በቅርቡ የሞቱት የፖላንድ መሪ የነበሩት ሌች ካቺንስኪ በሕይወት እንዳሉ ተደርገው ተቀምጠዋል፤ የናይጄሪያም ተመሳሳይ ነው:: ኡማር ያራዱአ ከሞቱ ሰነባበቱ:: ሆኖም «አሉ፣ መሪ ናቸው» ተብለው ተጠቅሰዋል:: ወዘተ::

የተወሰኑ መረጃዎች ደግሞ የተላለፉበት መንገድ አምባቢን «ኤጭ» ሊያስብሉ የሚችሉ ናቸው:: በገጽ 47 ስለቺምፓንዚ እና ስለጦጣ ተጽፏል:: እንደሚመስለኝ ስለእንስሳቱ መረጃ ያገኙበት ምንጭ በስዕል የተደገፈ ሳይሆን አይቀርም:: እናም «ከላይ ያየናቸው ቺምፓንዚዎች» እና «በልዩ ልዩ ምስሎችና ቅርፆች ላይ የምናያቸው» የሚሉ «የምስል ማብራሪያዎች» ተጽፈዋል:: ሆኖም አንድም ምስል ወይም ቅርፅ አልቀረበም (በገፁ ላይ ምስል መፈለግ ባይኖርብኝም መፈለጌን ግን አልደብቅም!!!)::

ሌላው ስለኮካኮላ በገጽ 146-7 የተባለው ነው:: በኮካኮላ ሽያጭ ትርፍ ምክንያት ዓሣ ግሪግስ ካንድለር የተባሉ ግለሰብ ባለፀጋ ወይም ቱጃር ለመሆን መብቃታቸውን እና የእርሳቸውም «ካዝና በገንዘብ ብዛት ከመጨናነቁ የተነሳ» በበጎ አድራጎት ተግባር ተሰማርተው ስማቸውን እንዳስጠሩ ተነግሮናል:: ከአመክንዩ አንፃር ብቻ በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ ያለውን ብወስድ ሚዛን አልደፋ አለኝ:: አንድን ሰብዓዊ ተግባር እንዲሁ ከገንዘብ ጋር ብቻ አያይዞ ቦጎ አድራጊው በበጎ አድራጎት ተግባር የተሰማራው በገንዘብ «ስለተጨናነቀ» ነው ብሎ መደምደም ትክክል አልመሰለኝም:: ከሞራል አንፃርም የሚሄድ አይደለም:: ከገንዘብ በፊት የሰብዓዊነት ስሜት ይቀድማል:: ለሰብዓዊ ተግባራቸው ከገንዘቡ ይልቅ (ገንዘብ ስላላቸው ነው በዚያ ዓይነት ተግባር የተሰማሩት የሚለውንም ለመግባባት ያህል ብንወስደው እንኳን) ሰውዬው ሰውን ለመርዳት ያላቸው ከፍተኛ የሞራል መሰረት እና ፍላጎት (ምርጫ) ቢጠቀስ አግባቢ ሊሆን ይችላል::

በመጨረሻ ማለት የምፈልገው መጽሐፉን ትክክለኛ አስተማሪ እና የእውቀት ማኅደር ማድረግ ይቻላል:: ትኩረት፣ ጥንቃቄ እና ጥረት ከታከለበት፣ በአሁኑ እትም ያሉ ስህተቶች ተለቅመው ከወጡና በቀጣይ እትሞች ከተስተካከሉ በእርግጥ መጽሐፉ እንደ መጽሐፍነቱ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ መመልከት እንችላለን:: ስጀምር እንዳልኩትም ለአንዲት አገር ሁለንተናዊ መሰረት መጽሐፍት የሚኖራቸው ድርሻ እጅግ ላቅ ያለ ነውና በዘፈቀደ ለሕዝብ አናቅርባቸው::

## በአማርኛ ዩ ተዳፊ ጽሁፍ

ደሳለኝ ስዩም
desalegnseyoum@yahoo.com

# በለው ጉባው ዘ እርሻ

ሰሞኑን ኢ-ሜይሌን ስከፍት የአንባቢ አስተያየት አገኘሁ:: እንዲህም ይነበብ ነበር::

*ደሳለኝ፣ አውራምባ ታይምስ ላይ የምትፅፋቸውን እያነበብኩ ነው:: ለማዝናናት መሞከርህ ጥሩ ነው:: በተለይ አንዴ የፃፍከው የተማሪ ወግ ምንኛ እንዳሳቀኝ እኔ ነኝ የማውቀው:: ለነገሩ አሁንም እንደዚያ ዓይነት ነገር ብትፅፍ ይሻልሃል::*

ወደ ዛሬ ዲስኩሮቼ ልለፍና፣ በመጀመሪያ ላይ ያሰፈርኩት አስተያየት ሰጭ እንደጠየቀው ወደ ትምህርት ቤት እንመለስ:: ለመሣቅ አይደለም:: በትምህርት ስቆ የሰለጠነ የለም:: ለማሾፍ አይደለም በአገሪቱ ፖሊሲ ማሾፍ ነውር ነው:: ለመሣለቅም አይደለም:: ከኛ መሣለቅ ትምህርታችን ምን ይጠቀማል?

አንባቢ ሆይ «እንግዲያ ስለምን ትለናለህ?» ያላችሁኝ እንደሆነ ለትምህርት ጥራት መጠበቅ የግሌን አስተዋጽኦ ለማበርከት ነው ብዬ እመልሳለሁ::

እነሆም ስለ ትምህርት ቤት፣ ስለ ተማሪና መምህራን ሳስብ እውነቶችንና ቅጥፈቶችን፣ እንዲሁም አፈ-ታሪኮችን በማቀናጀት የሚከተለውን ታሪክ ማዋቀር እችላለሁ::

በለው ጉባው የተባሉ የእርሻ መምህር /እርሻ በአካባቢ ሳይንስ ተለውጧል/ የሠሯቸውን ታሪኮች እንመልከት:: በለው የመምህሩ ስም ነው:: ጉባው የአባት ስም::

### 1. የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም

መምህር በለው ከፍ ሲል እንደተገለጠው የእርሻ መምህር ናቸው:: ሲያስተምሩ ብርቱ ናቸው:: ለሙያቸው ሟች ናቸው ብሎ የሚላቸው አንድም ዘመድ የላቸው::

ይሁንና ብርቱ መ/ር ለመሆን ብዙ ጥረቶችን ያደርጋሉ:: የአንድ ብርቱ መ/ር መለያ ከሆኑት ነገሮች ደግሞ አንደኛው የትምህርት መርጃ መሣሪያ /teaching aid/ መጠቀም ነው::

መምህር በለው እውነተኛ ቁስ /Real object/ በመጠቀም የመጀመሪያው ሰው ሆኑ:: ስለ ባህላዊ የኢትዮጵያ እርሻ ለማስረዳት ያስችላቸው ዘንድ ሁለት በሬዎች እየነዱ ክፍል ውስጥ ገቡ::

የክፍሉ ሕፃናት ተራወጡ፤ የቻሉ በመስኮት አመለጡ:: ያልቻሉ ወድቀው ተላላጡ:: አንዳንዶች በበሬ ቀንድ ተወግተው ዓይናቸውን አጡ:: ብዙዎች ግን ደነገጡ::

ከዚህ በኋላ መምህር በለው በበላጭነት መዝገብ ላይ ሠፈሩ:: በነገራችን ላይ በላጭ የሆኑት በዚህ ሥራቸው አይደለም:: ርዕሰ መምህሩ ጠርተው በወቀሷቸው ጊዜ እንዲህ በማለት መልስ በመስጠታቸው ነው:: «እስከሚገባኝ ድረስ በሬ ወደ ሰው ይመጣል እንጂ ሰው ወደ በሬ አይሄድም::»

### 2. የፈተና ጥያቄዎችና የተማሪዎቹ ውጤት

መምህር በለው ጉባው በተለመደ መንገድ መሄድ እንደማይወዱ ደጋግመው ገልጠዋል:: እነሆም ለተማሪዎች የማጠቃለያ ፈተና ሲፈትኑ የሚከተሉት ሁለት ጥያቄዎች አብረው ተካተው ነበረ::

ሀ) የእርሻ መምህራችሁ ስም ማን ይባላል?
ሀ) በለው ጉብነት ለ) በላቸው ጉባቸው
ሐ) በለው ጉብዋ መ) በልነት ጉብነት

ለ) የእርሻ መምህራችሁ የአቶ በለው ጉባው መኖሪያ ቤት የት ይገኛል?
ሀ) ከበሬሳ ማዶ /በሬሳ የወንዝ ስም ነው/ ለ) ከበሬሳ ወዲህ
ሐ) በሬሳ ውስጥ መ) ሁሉም መልስ ነው

በነገራችን ላይ የመጀመሪያውን ጥያቄ ሁሉም ተማሪ በትክክል መልሶታል:: ምክንያቱም እያንዳንዱ ተማሪ መ/ሩን እንደፈለገ አቆላምጦ የመጥራት መብቱ በመምህር በለው ዘንድ የተከበረ ስለሆነ::

### 3. የትምህርት ቤት የልማት ተሳትፎ

በጊዜው በርዕሰ መምህሩ አነሳሽነት በት/ቤቱ ግቢ ውስጥ የተለያዩ የልማት ሥራዎች እንዲሠሩ በጉባኤ ተወሰነ:: የልማት ሥራው በአብዛኛው ችግኝ መትከል፣ አበባ መኮትኮት፣ የስፖርት ሜዳ መገንባት፣ አጥር ማጠር፣ ወዘተ... ነበር::

እንዲህ ዓይነት ግብርናዊ ተግባራት ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መምህር በለውን ይመለከቱ ነበር::- ቢያንስ ሠርተው እንዲያሠሩ::

መምህር በለው ግን ልማታዊ ተሣትፎ እንዳያደርጉ አንድ እክል እንደገጠማቸው ተናገሩ:: ይኸውም የቀኝ እጃቸው አምስቱም ጣቶቻቸው ታጥፈው /እንደቦክስ ተጨብጠው/ አልዘረጋ እንዳሏቸው ተናገሩ::

ብዙ መ/ራን በክስተቱ አዘኑ:: እንዳይደርስባቸውም በስመ አብ ማለት አበዙ:: ርዕሰ መምህሩ ግን ተጠራጠሩ:: እንዲህ ያለ ክስተት በእንደምን አኳኋን ሊከሠት ይችላል ብለው አብዝተው አሰቡ:: ከቆይታ በኋላ ለመምህር በለው ጥያቄ አቀረቡ::

«መምህር በለው መቼ ጀመረህ?»
«ዛሬ አሁን!»
«ስብሰባ ስትገባ እንዴት ነበር?»

በለው እጃቸውን ለሠላምታ ዓይነት ዘረጉና፣

«ስብሰባ ሳልገባማ እንዲህ ነበር!»

### 4. ቅኔ ዘረፍ

የት/ቤቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ት/ቤቱን ሲለቁ ለመለያያ ያክል ይደግሳሉ:: ጠላ ከየቤታቸው ያመጣሉ:: ፍየል ይጠብሳሉ:: መጀመሪያ መምህሮቻቸውን ቀጥሎ ራሳቸውን ይጋብዛሉ:: እንዲህ ባለ ግብዣ ላይ የእርሻ መምህሩ ጠላ አብዝተው ኖሮ ለአንዲት ተማሪያቸው እንደሚከተለው ተቀኙላት::

«አንገቷን ብለካው ሆነ ስንዝር ከጋት፣
አሁንኮ ውሸት ይመስላል ላላየ ሰው ማውጋት::»

ቅኔውን የሰሙ ሁሉ በሳቅ አሽካኩ:: የእርሻ መምሩ አልተረበሹም፤ ይልቁንም ለሳቁባቸው ሁሉ እንደሚከተለው ተቀኙ::

«አላበቅል አለ ማሽላ ብዘራው፣
አላበቅል አለ ጤፉንም ብዘራው፣
ተልባ ነው ምዘራው ግዜው መላጋ ነው::»

*ቅዱሱ እሱ ያሰንብተን::*

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# መ ዝ ና ኛ

## እኔ የምለው *ከሊዮ*

## በብራዚል መናደድ ቅንጦት አይሆንም?

እናንተዬ ታክሲውም (በተለይ ውይይት ታክሲ) እንደ መኖሪያ ቤት በመወርወሪያ ቁልፍ መቀርቀሩን እንዴት አያችሁት? እንዴ አንዳንዱ ውይይት ታክሲማ ከመሳሳቱ የተነሳ እግር ሊያሾልክ ምንም አይቀረውም እኮ:: ኧረ በስንቱ እንሹለክ? የኑሮቀ ቀዳዳ ያሾለከን አንሶ ኧረ *fair* አይደለም? እኔ የምለው ግን እነዚህ ታክሲዎች የቦሎ ምርመራ ሲያደርጉ ክርቻቸው [ማለቴ መርገጫቸው] አይታይም ይሆን? ወይስ እሱንም ተበድረው ይገጣጥሙታል? [አናጢ የጠጋገናቸው እንጂ ጋራዥ የሚያውቃቸውማ አይመስሉም::]

ዓለም ዋንጫ ነገ ሊፈፀም ነው:: እኔማ ግልግል ብያለሁ:: እንዴ ለቫራይቲ እንኳን ሌላ ወሬ አታውሩ የተባለ ይመስል ፒፓል በሀሳብ ወደ ደ/አፍሪካ ተሰዶ ነበር:: በአርጀንቲና፣ በብራዚል፣ በጋና መውደቅ ስንቱ ትንሹ አንጀቱ፣ ትርፍ አንጀቱ፣ ወተት አንጀቱ፣ ትልቁ አንጀቱ ተላጠ እኮ:: በኑሮ ለተቆራመደ ህዝብ በላቲኑ፣ በአውሮፓው ከዓለም ዋንጫው መባረር ምክንያት መናደድ ቅንጦት የሚሆን አይመስላችሁም? እኔማ ንዴትን የሚቆጣጠረው የሰውነት ክፍል በኳስ የተናደደ የአገሬን ሰው ሲያገኘው ኮምፒውተር ያልተጫነበትን ሶፍትዌር ፋይል አላነብ እንደሚለው ሁሉ «በኳስ ለመናደድ ገና አልደረሱም» የሚል የምርጫ ሳጥን የሚያመጣ ይመስለኛል:: ይህም እኮ ፋይሉን ካነበበው ነው::

እነ ቤቢ እና እነ ሚሚ እንደ ፓርላማ ሁሉ የእነሱም ት/ቤት ስለተዘጋ እረፍት ላይ ናቸው:: የታደሉ ህፃናት ደግሞ ለመዝናናት ከአገር ይወጣሉ:: አንዱ ህፃን ግን የገጠመው ነገር ለየት ያለ ነው:: በትምህርት ጊዜ ከሚመከረው ነገር አንዱ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን እንዳያይ ነው:: በተለይ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሆኖ ዜና ሲነበብ እንዲተኛ ይታዘዛል:: አሁን ትምህርት ስለተዘጋ በሁለተኛ ሴሚስተር ከተወሩ ዜናዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹን አባቱ ይከልሱለታል:: ግንቦት 15 የተደረገው አገራዊ ምርጫ ላይ ደረሱ:: «ይኼውልህ ቲቪውን ባታየውም መንገድ እየዘጉ አይተሀቸው የለ?» ልጁ ለአዎንታ ራሱን ወደ ላይ ነቀነቀ:: «እና እልህለሁ...ምርጫ የሚባል ነገር ነበረ:: ምርጫውን ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ ኢህአዴግ ማሸነፉን ምርጫ ቦርድ የሚባለው... አሳውቋል:: በሚቀጥለው ዓመት ፓርላማ ውስጥ የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካዮች የሉም ማለት ይቻላል::» ልጅ መለሰ «በቃ ህዝቤ ጠርቶኛል ብለው ሄደው የነበሩት እነ ልደቱ ብቻ ናቸው የሚኖሩት ማለት ነው?» «አይ እሳቸው እኮ... ተቃዋሚ...» አባት ለማስረዳት ሞከሩ:: ልጅ ጥያቄውን ቀጥሏል:: «ታሪካዊው የፓርላማ ቡድንም አይኖርም?» «አዎ» «ታዲያ በሚቀጥለው ዓመት ተረትና ምሳሌ ማን ሊያስተምር ነው? ራሳቸው አማርኛ አስተማሪ ይዘው ሊገቡ...? ወይስ ይሄም ኃላፊነት በአፈ ጉባዔው አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ላይ ሊወድቅ ነው?» ብሎ ጠየቀ እላችኋለሁ:: እነ ቤቢ እና እነ ሚሚ አስተሳሰባቸው ጨምሯል:: [ከማዳበሪያው ነው የሚሉ አሉ::] አንዳንዱ ግን የልጅነት ስሙን ሳይለቅ ስሙ «ቤቢ» እና «ሚሚ» እንደተባለው ስራውም፣ ስልቱም፣ አስተሳሰቡም ትንሽ ሆኖ ይቀራል፤ እንደተነገረው ብቻ:: [«ሚሚ» ስል ከማንንም ጋዜጠኛ ጋር ለመነካካት አስቤ አለመሆኑ ይታወቅልኝ::] የምለው ካላጣሁ የሳምንት ሰው ይበለን::

## ቅንጭብጭብ

## የወርቅ ቅንጣቶች ለማግኘት ቁርጠኛ ውሳኔ

«የሃብት የመጀመሪያው ምዕራፍ ጥልቅ ፍላጐት ውስጥ መኖር ነው:: የእናንተም ፍላጐት ጠንካራና ግልጽ መስመር የያዘ መሆን ይኖርበታል:: ዝም ብሎ ጭፍን ፍላጐት ደካማ ኑሮን ይወልዳል:: አንድ ሰው ሃብታም ለመሆን መመኘትን ብቻ በቂ ነው ብሎ ካሰበ ይህ የድክመት ምልክት ነው:: ነገር ግን አምስት የወርቅ ቅንጣቶች ማግኘት አለብኝ ብሎ ቁርጠኛ ውሳኔ ላይ ከደረሰ ይህ ሰው ተጨባጭ የሆነ ስኬት ሊያስጨብጠው የሚችል ውሳኔ ላይ ደረሷል ማለት ነው:: በቃ ለውጤታማነቱ ወደፊት ይገፋል:: ይህ የአምስት ቅንጣት ወርቅ ዓላማወውን ሰንቆ ተንቀሳቅሶ ካሳካ በኋላ ያንን ወርቅ በጥሩ ሁኔታ ቦርሣው ውስጥ ይከትና ለቀጣዩ ወርቅ በተመሳሳይ ጥንካሬና ወኔ ለማሳካት ይንቀሳቀሳል:: ማን ያውቃል? ለአምስት ቅንጣት ወርቅ ሲንቀሳቀስ አስር ቀንጣት ወርቅ ሊያገኝ ይችላል:: ሃያም፣ ሰላሳም ከዚያም በላይ ወርቆች ሊሰበስብ ይችል ይሆናል:: እያለ እያለ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የወርቅ ቅንጣቶችን ያከማቻል:: በቃ ሃብታም ሰው ሆነ ማለት ነው::

«ሌላው ማከማቸት መቻልን መማር ነው:: ያቺን ያገኛትን አምስት ቅንጣት ወርቅ በወኔና በጠንካራ ፍላጎት፣ በጥንቃቄ ባይዛት ኖሮ ቀጣዮቹን ወርቆች አያገኛቸውም ነበር:: በትንሹ በጥቃቅን ወርቆች አያያዙን በአግባቡ ተማረና በደንብ ተገርቶ ከፍ ያለውን ወርቅ ለማስተናገድ ራሱን አዘጋጀ:: ሃብት በዚህ መንገድ ነው የሚካብተው:: መጀመሪያ በጥቂቱ ትንንሾቹን በአግባቡ ትይዛላችሁ:: እውቀትና ችሎታችሁን እያዳበራችሁ ስትሄዱ ከፍ ያለውን ሃብት ማስተዳደር ትችላላችሁ::

/ባቢሎናዊው የሐብት ልዑል- ደራሲ:- ጆርጅ ሳሙኤል ክላሰን፤ ተርጓሚ:- አካሉ ቢረዳ - 2002/

## ቋጠሮ

### ውሾቹ የማን ናቸው?

ለአደን  
ለምግብ  
ለቤት  
ለህክምና  
ለስፖርት  
ለጥበቃ  
ውሾች ይረባሉ፤  
ግና:-  
በየመውጫ መግቢያው  
መናከስ ስራቸው  
ዜብራ የሌላቸው  
«ጃስ» ባዺቸው ቁጥር  
«አ» የሚሉ በገቢር  
ባለቤት አላቸው?  
ለምን የረቡ ናቸው?

*በአበባየሁ ለገሠ*

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

## ጎንዮ ፍታ

***በፊልሞች እና በቲያትሮች ላይ መታየት የጀመረው በ1991 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ነው:: ከሃያ የማያንሱ ፊልሞች እና ከአስር በላይ ቲያትሮችን ሰርቷል:: «በአማተርነት ሳልሰራ ወደ ትልልቅ መድረኮች መምጣቴ እድለኛ ሊያስብለኝ ይችላል::» የሚለው አርቲስት ሳምሶን ታደሰ (ቤቢ) «ቢዚ» ነኝ በማለት ደስታን ከሚያገኙ በርካታ አርቲስቶች አንዱ መሆኑን ለመገመት ቀጠሮ እየያዝን በተደጋጋሚ መሰረዙ ማስረጃ ይሆናል:: ሰናይት ግርማ አንድ አፍታ አዋርታዋለች::***

# «ኃይማኖትም ይሁን ፖለቲካ አክራሪነት ያለበት ነገር ደስ አይለኝም»

***ብዙ አርቲስቶች አንተን ጨምሮ «ጊዜ የለንም «ቢዚ» ነን» ትላላችሁ:: የራሳችሁን ደረጃ ከፍ እንደ ማድረግ ትቆጥሩት ይሆን?***

ራስን ከፍ ማድረግ አይደለም:: ሰውየው «ቢዚ ነኝ» ሲልሽ ምናልባትም ውጥረት ውስጥ ሆኖ ሊሆን ይችላል:: ሁለትና ሶስት ስራ ይሰራ ይሆናል:: እዚህ አገር ያለው የአርቲስት ቁጥር ከህዝብ ጋር የሚመጣጠን አይደለም:: አርቲስቱ በእረፍቱ ሰዓት ደግሞ ነፃነትን ሊፈልግ ይችላል:: ብቻውን መቆየት ሊፈልግ ይችላል:: ካልሆነም ከለመድናቸው ሰዎች ጋር በአካባቢያችን መሆን ሊያስደስተን ይችላል:: ከዚያ አንፃር ነው እንጂ ራስን ከፍ አድርጎ የሚያስብ አርቲስት ኖሮ አይደለም:: አርቲስቱ በባስ እና በታክሲ እየሄደ ራሱን እንዴት ከፍ አድርጐ ሊያይ ይችላል?

***አዲስ ስራ እየሰራህ ነው?***

በብሔራዊ ቲያትር እየሰራን ያለነው አንድ ስራ አለ:: የሚያዘጋጀው ጌትነት እንየው ሲሆን ደራሲው ደግሞ መልካሙ ነው:: እየተለማመድን ነው::

***ራስህን በጥበብ ብቁ ለማድረግ ምን ያህል ትጥራለህ? የምትጠቀማቸውስ ቴክኒኮች አሉህ?***

የለመድነው የአጠናን ዘይቤ አለ:: ግን ሌሎች ትልልቅ ባለሙያዎችን እያየሁ ተሞክሯቸውን እወስዳለሁ:: ለምሳሌ ፊልሞችና ቲያትሮችን አያለው:: መፃህፍቶችንም አነባለው:: ለሙያው የሚያስፈልገውን ክህሎት እንዳዳብር ያደርገኛል::

***እንደ አገራዊ ምርጫ በአምስት አመት ቢሆን የምትለው ነገር አለ?***

ኳስ መዝናኛ ነው:: የዓለም አገራት የሚፎካከሩበት መድረክ ነው:: በአንድ በኩል ደግሞ ቁማር ነው:: ግን የዓለም ህዝብ የሚከታተለው እና የሚዝናናበት ነው:: ፖለቲካም ሲሆን ሰዎች አድገው የሆነ ደረጃ ሲደርሱ እምነት ተጥሎባቸው ነው ስልጣን ላይ የሚወጡት:: ይህንን በሌሎች ሙያዎች ላይ እናድርግ ብንል በጣም ይከብዳል:: ተምሮ፣ አድጎ፣ በስሎ ብቁ ሰው ሲሆን የአምስት ዓመት የስራ ልምድ ያለው ሰው እያለ በአዲስ ሰው መተካት ጥሩ አይደለም::

***በአርቲስቶች በኩልስ?***

እንኳንስ ለውጠናቸው ያሉትም በጣም ጥቂት ናቸው:: በንጉሱ ጊዜ ለጥበብ ብዙ ትኩረት ይሰጥ ነበር:: ብሔራዊ፣ ሃገር ፍቅር፣ አዲስ አበባ ባህልና ቴያትር አዳራሽ ተቋቁመው የነበረው የአዲስ አበባ ህዝብ ቁጥር ትንሽ በሆነበት ሰዓት ነበር:: በአሁን ሰዓት የህዝብ ቁጥሩ እጥፍ ባደገበት ወቅትም ያሉት ቲያትር ቤቶች እነዚሁ ናቸው::

***ሽንፈት ላንተ ምንድነው?***

አደርገዋለሁ ብለን ያልነውን ሳናደርገው ስንቀር፤ ወይንም ማድረግ እየቻልንና እድሉ ኖሮን ሳናደርገው ስንቀር፤ ያ ሽንፈት ነው::

***በእድል የተነሳ የማይሳኩ ነገሮች የሉም?***

እድል ከሆነ ሽንፈት አይደለም ለምን? ስለሞከርን:: ሳንሞክር ስንቀር ነው እድል የሚያመልጠን:: እድሉ መጥቶ ሳንጠቀምበት ስንቀር እድሉን አሳለፍነው ማለት ነው:: ይህ ሽንፈት ነው:: እኛ የቻልነውን እንጥራለን:: እድልም ያግዘናል:: ግን የእኛ ጥረት ነው ዋናው::

***ሌባ ዘርፎህ ያውቃል?***

አያውቅም:: የሚገርመው ነገር አጋጥሞኝ እንኳን አያውቅም:: መጥፎ መጥፎ (ኃይለኛ) ሌቦች አሉበት በሚባል ሰፈር ሁሉ ኖሬያለሁ:: ሌባ ግን ገጥሞኝ አያውቅም::

***ስለምትቀርባቸው ይሆን?***

የእግዚአብሔር ጥበቃ ይመስለኛል:: ምናልባትም ፍቅር ለእኔ ሊኖራቸው ይችላል::

***ፀጉርህን የምታሳድገው ለምንድን ነው?***

ፀጉሬን ማሳደግ የጀመርኩት በስራ ምክንያት ነበር:: የሚገርመው ስራውን ካሰብነው ከስድስት ዓመት በላይ ቢሆነውም እስካሁን አልተሳካም:: ጊዜውን የሚጠብቅ ስራ ነው:: ሙሉ የእኛ ግሩፖች (ጓደኞቼ) ፀጉራችንን የምናሳድገው ለዚያ ነበር:: በኋላም እንደ ስታይል ሆነ:: ፀጉር ማሳደግ ለስራችን በጣም ያግዘናል:: ኩል የሆነን ገፀ ባህሪ ለመስራት በቀላሉ መቆረጥ ይቻላል:: «ዱርዬ» ገፀ ባህሪ ቢፈለግ እንደዚያው:: ከአክቲንግ አኳያ እንዲህ አይነቱ ጥቅም አለው:: ለእኔ እንደ ግርማ ሞገሴ እቆጥረዋለው:: ምናልባት ስሜ ሳምሶን ስለሆነ ይሆናል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለው ሳምሶን ኃይሉ ፀጉሩ ላይ ስለሆነም ሊሆን ይችላል::

***ፀጉርህን የግድ መላጨት አለብህ ብትባል ምን ታደርጋለህ?፣ ማን እንዲላጭህስ ትፈቅዳለህ?***

እርግጠኛ አይደለሁም:: ምናልባት ፀጉሬን ማስላጨት አስገዳጅ ነገር እስር ቤት መግባት ሊሆን ይችላል:: መላጨት በፍፁም የማልወደው ነገር ነው:: የግድ ከሆነ ግን ፀጉር ቤት ሄጄ የምላጭ ይመስለኛል::

***ስትታይ አጫሽ፣ ቃሚ፣ ጠጪ የሆነ «አጭቤ» ነገር ትመስላለህ:: የሰካራም ገፀ ባህሪዎችን በተደጋጋሚ የምትጫወተውስ ለምንድን ነው?***

በመጠኑም እኔን አርአያ የሚያደርጉ ሰዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ስለ ሱስ ማውራት ጠቃሚ አይደለም:: የዳይሬክተሮች ምርጫ ነው የሰካራም ገፀ ባህሪያት በተደጋጋሚ እንድጫወት የሚያደርገኝ:: ዳይሬክተሩ ተጽእኖ የሚያደርግበት አርቲስቱ ከዚህ በፊት የሰራውን ስራ በማየት ሊሆን ይችላል:: መጀመሪያ «ሹፌሩ» የሚል የቴሌቪዥን ድራማ ነበር የሰራሁት:: በጣም ብዙ የለፋንበት ስራዎች ቢኖሩም እንደቀልድ የሰራናት ያቺ ድራማ ተመልካች እና ዳይሬክተሮች ጋር እንድገባ አድርጎኛል:: እያጨስኩኝ የሰራሁት ካራክተር እንዳለ ሁሉ ሌሎችም ካራክተሮችን ተላብሼ የሰራኋቸው አሉ::

***ትወናን ትተህ በሽክላ፣ በሽመና አልያም ደግሞ በቆዳ ስራ ላይ እንድትሰማራ እድሉ ቢሰጥህ የቱን ትመርጣለህ? ለምን?***

ከቢዝነስ አኳያ የቆዳ ስራ ሳይሻል አይቀርም:: ግን ለነብሴ ደስ የሚለኝ ነገር የሽክላ ስራ ነው:: የሽክላ ስራ ሲባል ድስት እና ጀበና ብቻ አይደለም:: እነ ሲኒ፣ እጣን ማጨሻ አንዳንዴም በኛው ህብረተሰብ የተሰሩ የሚያማምሩ ፈጠራ ያለባቸው የሽክላ ቅርጻቅርጾች አሉ:: ግን ያው የቆዳ ውጤቶች ወደ ውጪ ሲላኩ የሚያስገኙት ጠቀም ያለ ገንዘብ ስለሆነ ይህ ዘርፍ ይሻለኛል::

***ብዙ ጊዜ አርቲስቶች ለጋዜጦች ያላቸው ቅርበት ያን ያህል ነው?***



***በተለይ ለፖለቲካ ጋዜጦች? አንተስ?***

በጣም ብዙ አርቲስቶች ሁሉንም ጋዜጦች እንደሚያነቡ አውቃለሁ:: የሚይዙት ቦርሳ ቢከፈት በርካታ ጋዜጣ ይዘው የሚሄዱ አሉ:: ጋዜጦችን የማነብበት ወቅት ነበር:: ኃይማኖትም ይሁን ፖለቲካ አክራሪነት ያለበት ነገር ደስ አይለኝም:: የራሴ የሆነ የፖለቲካ አመለካከት አለኝ:: አክሮ አንዱን መውደድ እና መጥላት እነዚህ ነገሮች ደስ አይሉኝም:: እነዚህ ነገሮች ደግሞ ጋዜጦች ላይ የሚንፀባረቅበት ወቅት ስለ ነበር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጋዜጦችን ማንበብ እየቀነስኩኝ መጣሁ::

***እንቅስቃሴህ ኪስህ ውስጥ ባለው የገንዘብ አቅም ልክ ነው?***

አዎ! እግዚአብሔር ይመስገን እንኖራለን:: ያለነው ደሃ ከሚባሉት ሃገሮች አንዷ ውስጥ ነው:: ብዙ የሚያሳዝኑ ሰዎችን እናያለን:: ባለሞያዎች ሆነው የጥረታቸውን ያህል የማይከፍላቸውን ስናይ የእኛ ጥሩ ነው::

***ስትሰማው በጣም ያስደነገጠህ ዜና?***

እስካሁን የማልረሳው አስደንጋጭ ዜና የማይክል ጃክሰን ሞት ነው:: የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ስርጭት 24 ሰዓት የሆነበት ወቅት ነበር:: ቴሌቪዥኑን ሳልዘጋ ነበር ያደርኩት:: ነግቶ የ12 ሰዓቱን ዜና ሲያነብ «ዝነኛው የፖፕ ንጉስ ማይክል ጃክሰን አረፈ» ሲል ማመን አቃተኝ:: እንዲሁም የጥላሁንን ሞት ስሰማ በጣም ነበር የደነገጥኩት::

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

## ልብ-ወለድ

በታሪኩ ሽመልሽ

# ሑ ረ ት

በዚህ ትዕንግርታዊ ቅፅበት እኔና አዕምሮዬ በካዛንቼሱ የሕልቀት አደባባይ ላይ ተገናኝተናል:: ካዛንቼስ ለመሆኔ ግን የማስረግጥበት አንዳችም ምክንያት የለኝም:: ነገር ግን ከፊት ለፊቴ ያለ አንድ ጠብደልና እውናዊ ሰው ይናገረኛል:: «አሁን በካዛንቼስ አደባባይ ትገኛለህ» ይለኛል:: *ማህልዬ ማህልዬ ዘ ካዛንቼስ* የሚል ፅሁፍ የተከተበበት ብራና በቀኝ እጁ፣ በግራው ደግሞ ቀለም የተነከረ የሚመስል የጭንቅላት ቅርጽ ይዟል:: የብራናውን ፅሁፍ ሳነብ በእጁ ከነበረው ጭንቅላትም የተለያዩ ጨረሮች ወደኔ ይለቀቁ ነበር:: የሚፈተለኩት ጨረሮች «ዘ ካሳንቼስ» ከሚለው ፅሁፍ ይፈራረቁ ነበር:: እኔም 'አሁን ያለነው በካዛንቼስ ነው' ስል ለእኔነቴ ነገርኩት:: ለምን ግን በዚያ እንዳለሁ፣ ምንም ደግሞ አደርግ እንደነበር የማወቅ አልነበርኩም:: የሚናገረኝ ድምጽ ግን ይለኛል፤ «አሁን በካሳንቼስ አደባባይ ወደ 22ም በሚወስደው የህልቀት ስብስብ ዳርቻ ትገኛለህ» ሲል ደገመው:: «ሕልቀት» የሚለውን ቃል «እልቂት» በሚል ሃሳብ አፍጥኖ ሰማው:: አእምሮዬም በተዛነፈው ትርጓሜ ማሰላሰሉን ቀጠለ:: እኔና አእምሮዬም በቃል ተከራከርን እኔም አስረዳው ጀመር:: «ሕልቀት» የሚለውን ቃልም «ፍጥረት» ወደሚል ሃሳብ ከአረበኛ ወደ አማርኛ ይዘት በማስታከክ መለፈፌን ቀጠልኩ:: ለደቂቃዎችም ያህል በኔ ውስጥ ሁለታችንም እናወራ ነበር::

በዚሁ የክረክራችን እለት ለጉዞ የማይታክቱ ሁለት ቅንጣት እግሮቼ በአንድ ያማረና የአፈጣጠርም ዘመነኛ በሚባል ዓይነት፣ የወንበር ስብስቦችም ባሉበት የመጠጥና ጨኸት ማሣረጊያ ዳስ ውስጥ ጥለውኛል:: እኔም በዝምታ ተጠቅልዬ የሄድኩበትን አይ ዘንድ ዓይኖቼን ገለጥኩ:: በዳሱ የሥርገኛው ጨኸት፣ በአዳራሹ ምህዋር እየነጠረ የተከፈቱ የጆሮ ታምቡሮችን ማናወጥ ጀመረ:: በአዳራሹ ውስጥ የሚርመሰመሱ የሰው ልጆች፣ ሴቶች ልጆችም አየሁ:: አቋቋማቸው በውል ያማረ፣ ቡቲክ ውስጥ ከተተከሉ አርቴፊሻል ሰዎችም በእጅጉ የሚልቁ ነበሩ:: በአደባባዩ የውስጥ አዳራሽ ግድግዳ ላይ የሚብለጨለጩ፣ የሮምንም ጣኦት የሚመስሉ በመብራትና በእንቁ የተዥጉረጉሩ ስዕሎች ተሰቅለዋል:: በስዕሎቹና በእኔ መካከል፣ በወለሉም ስፋት እንቅስቃሴ ይታይ ነበረ:: ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝም ወደግራ እንደውዝዋዜም፣ ዳሌአቸውን አጉብጠው፣ ወገባቸውን የሚሰብቁ የሚንቀሳቀሱና እርቃን ገላም ነበሩ::

እኔና እኔነቴ አንደመጀመሪያው ክርክር ጀመርን፤ እኔም የማየውን እኔነቴ እንዳላየ ያስተባብል ነበር:: ወዲያውም የነፍሳቱ ምንነት ከነበረበት ተለወጠ:: እኔም በፊት እንኳ ያላየሁትን አየሁ:: ልብሳቸውም ጭን በሚመስለው የላይ ገላቸውና እምብርት በሚመስለው አካላቸው መካከል ነበር:: አለባበሳቸውም አንደመታረዝ፣ አቀማመጣቸው ደግሞ ወንበር እንደማጣት ነበር:: በአንድ ወንበር ላይም አንድ ጭን ከሌላ ጭን ርቀው በአንድ ዳሌ ይቀመጡ ነበር:: በአዳራሹ ካሉት ክፍሎችም የሰማይ መውጅ የሚመስል፣ ከነጐድጓድም የላቀ፣ የሙዚቃ ጨኸት ሞልቶ ይስተጋባ ነበር:: በዚህ ዕለትና ቦታ ይመራኝ የነበረውም በጥቁርና ዳልቻ የሚቀያየር፣ የመሠለ፣ በድምፅም የሚናገረኝ እውናዊ ሰው መጣ:: ከጐኔ እንዲቀመጥም መልስ ሰጠሁት:: እኔነቴ ግን ፈራ:: ሊያናግረውም አልደፈረም፤ ያኔም እኔና እኔነቴ ተጣላን:: በዚህን ጊዜ ከውጪው አእምሮዬ የሰማሁትን ሁሉ እቀበል ዘንድ ነበርኩና ውሳኔዬን በቀጥታ ለእኔነቴ ሰጠሁ:: ሃሳቤንም እያመነታ ተቀበለ::

እወናዊው ሰው መሰል አካል ከጐኔ ተቀምጦ ያናግረኝ ጀመር:: በዙሪያዬ ከነበረው ሁሉ ጨኸት ናላዬን ነጥዬ ጆሮዬንም ወደ ምላሱ ለኮስኩ:: በለሆሳስ ሲናገርም ቃሉ ከመዙቃው ይልቅ ኸረት ነበረው:: በመጀመሪያ የት እንደነበርኩ ነገረኝ:: «አሁን በካዛንቼስ ደግሞ በሕልቀትም መዶለቻ ትገኛለህ» አለኝ:: እኔም «ለመሆኑ አንተ ማነህ?» አልኩት:: እርሱም «እኔ በሮማ ያማልክትን ቅርጾች የሰራሁ ያማልክት አምላክ ነኝ» አለኝ:: እሰማውም ጀመር:: «እዚህ ቦታ ብዙ ታያለህ፤ የሮም አምላኮችንም አሁን እጠራለሁ የአንተነትህንም ቀልብ ይስቡ ዘንድ በፊትህ ይወዛወዛሉ ውዝዋዜውም ከመብራቱና ዕንቁው በላያቸውም ካለው አሸንክታብ ጋር ያማረ ይሆናል:: ነፍሳቸውም ከስጋቸው ሲነጠል ታያለህ» አለኝ:: ከዚያስ አልኩት «ነገስታቱንም እጠራለሁ:: የሮማ ቄሳርም በድግሱ ይሆናሉ:: በአማልክቱ ስጋም ነገስታቱ ይናወጣሉ:: ከወይን ጠጅም ጋር ደስ ይላቸዋል:: ነፍሳቸውም ከስጋቸው ፈጽሞ ይመሳሰላል:: በነፍሳቸውም ደም አለ:: ቄሳሮችም ይህንን መለያዬት ይሳናቸዋል:: ከነገስታቱም ጉራ ይሆናሉ» አለኝ:: የሚለው ሁሉ ግራ የሚያጋባ ነበር:: እኔ በወንበሩ ላይ በተሸለመው ግድግዳ ጫፍም በግራ በኩል፣ እኔነቴ ደግሞ በእኔ ውስጥ ገብቶ ነበርን::

ያማልክቱ አለቃም ነፍሳቱን ጠራቸው:: እኔም አልኩት፣ «ጌታዬ ያማልክት አለቃ ሆይ፣ ለመሆኑ የሮም አምላኮች እነዚህ ነበሩን? ሮም ዛሬ እንደነዚህ ዓይነት አምላክ አላትን?»:: «ለምን አታምንም?» አለኝ «አንተ አሁን እኔን መጨበጥ ትችላለህን፣ የማሳይህስ፣ ከሰው ልጆች የረቀቁ አይደሉምን?» አለኝ:: እኔም መጠየቄን ቀጠልኩ፤ «ጌታዬ ያማልክት አለቃ፣ ነፍሳቱንስ ከዬት አመጣህ:: ቅርፃቸውስ ለምን ሆነ?» አልኩት:: እንዲህም አለኝ::

«ነፍሳቱ ከማርስ መጡ፣ ቅርፃቸውም በማርስ የተለዩ ነበር:: እንዲህም አልነበረም:: የማርስ ሰዎችም ሀብታሞች ነበሩ:: አለባበሳቸውም ሙሉ አካል ነበረ:: ምግብና መጠጥም በማርስ ነበር:: በተድላና በደስታ ብዛትም ህይወታቸው ያማረ ነበር:: ከዘመናት በኋላ የማርስ ሰዎች ከአምላካቸው ጋር ተጣሉ ድርቅና ቸነፈርም ማርስን መታ:: ችግርም በዚያ ሆነ:: ውንዞችም ደረቁ:: በዚህን ጊዜ የማርስ ሰዎች ለመሰደድ ተገደዱ:: ወደምድርም ተመለከቱ፤ የተወሰኑት ሰዎች ከአምላካቸው ጋር ለመታረቅ ቢወስኑ ከፊሎቹ ረሃብና ቸነፈሩን መቋቋም ተሳናቸው:: በምድርም መጥተው ቃርሚያ ያሰባስቡ ዘንድ አሰቡ:: በሮም አደባባይም ለነገስታቱ እጅ መንሻን አቀረቡ:: በምድር ዳርቻ ካገኙት በሮምም ከሰበሰቡት ቃርሚያ ለወገኖቻቸው የሚሆን መክሊት ይዘው ወደ ማርስ እንደሚመለሱም፣ ከዚያም ከአምላካቸው ጋር እንደሚታረቁ ለውስጣቸው ቃል ገቡ:: ለነፍሳቱም ምልክት የሚሆን ያማልክት ቅርጽ እኔ ሰራሁ:: ይህም በካዛንቼስ ሆነ፤ ለአምልኮውም በዚህ አደባባይ ይሰባሰባሉ:: ይህም በጥቁር አምሳያ ስገለጥልህ ይሆናል:: ወደዳልቻ ስቀየርም በሮም እንዳለሁ ምልክት ነው::»

ንግገሩም በከፊል ግራ የሚያጋባ በከፊልም ግልጽ ይመስል ነበር:: ጥያቄ ሰጠሁት፣ «ነፍሳቱ በማርስ የራሳቸው አምላክ አላቸው፤ ታዲያ ያንተን ለምን ያመልካሉ?»

«ወደማርስ እስኪመለሱ የኔን አምላክ ያመልካሉ:: ስለዚህም አለባበሳቸውን ወደኔ አምላኮች ቀየሩ፤ በውዝዋዜና ሰልፍም ለነገስታት ደስታን ያቀርባሉ:: በዚህም ለማርስ ወገኖቻቸው የሚሆን እጅ መንሻን ከነገስታት እጅ ያገኛሉ::» አለኝ::

ወዲያውም ጥቁር በሚመስልና ጨለማ በከበበው የሸለቆ ዳርቻ ወሰደኝ:: በዚያም እንዲህ ሆነ:: ከፊት ለፊቴ የቆመ በመወጠሪያም በአየር ላይ የሆነ ፅሁፍ አየሁ፤ «ትነካና ዋ!» ይላል:: ያማልክት ጌታ ነኝ ያለኝም ከፊቴ ጠፋ:: ከነገረኝ መልኮችስ እንኳ ባንዱም አልሆነም፤ ጥቁርና ዳልቻ መልኩን ቀየረው:: የከርከሮ የሚመስል ጥርስ፣ የአጋዘን የሚመስል ቀንድ እንደ አንበሳ ሚያገሳ ድምጽም አወጣ:: አማልክቱም ቀረፃቸውን በላያቸው ለበሱ:: ለእያንዳንዳቸውም የልጃገረድ የሚመስል አጐጤ ተተከለላቸው:: ባዲሱ ክፍል ውስጥ የነበረው የጨኸት የአምልኮ ሥርዓት በዳሱ ከነበረው በእጅጉም የተለዩ ነበር::

በእኔ ውስጥ የነበረው እኔነቴ ከውስጤ ሾልኮ ጠፍቷል:: ምናልባትም በመጀመያው አዳራሽ ይሆን ብዬ ማሰላሰል ጀመርኩኝ:: ያወቀም ያክል በመልስ ይናግረኝ ዘንድ ያማልክቱ ጌታ ከወደላይ ጨኸቱን ሰማሁ:: አሁን አይታየኝም:: እንዲህ ግን ይላል «አንተነትህ በሮም አለ:: አትፍራ ከኛም ጋር ትተባበራለህ::» አለኝ:: «እኔ የትነኝ?» አልኩት «አሁንም አላመንከኝምን? አሁን በካዛንቼስ አደባባይ ወደ 22ም በሚወስደው የሕልቀት መሰብሰበያ ትገኛለህ» አለኝ:: እኔም መልሼ ተናገርኩት፣ «አንተ በካዛንቼስ አደባባይ ካለህ፣ ጥቁር ሆነህ ለምን አልተገለጥክም?» መልሱ፣ «ለምን አታስተውልም፣ የምናገርህንም አትሰማም? ለመሆኑ በካዛንቼስ አደባባይ ትገኛለህ ያልኩት አንተን እንጂ እኔን ነውን?» አለኝ:: «ታዲያ አንተስ የት ነህ» አልኩት:: «እርሱን እንድነግርህ ጊዜው ገና ነው፤ በካዛንቼስ ሰማይ ግን አሁን አለሁ::» አለኝ:: ግልጽ ስላልሆነልኝም ለመሆኑ አንተ ማነህ አልኩት:: እርሱም መልሶ «ከጉንህ ስሰወር ረሳኸኝ፤ ያማልክት አምላክ መሆኔን ትዘነጋለህ? አሁን ከኛ ጋ ትሆናለህ ከነፍሳቱ፣ የልጃገረድ አጐጤ ካለባትም አንዷን ላንተ ትወስዳለህ::» አለኝ:: «ወስጄስ?» አልኩት:: «ዛሬን ወደኛ ስለመጣህ ደስታ ይሆንልሃል በካዛንቼስ ሌሊቶችም የምሰጥህ ምስል ታረካሃለች::» አለኝ::


እኔም ጠየቅሁት፣ «ስለ እነርሱና ስላንተ ነገርከኝ፣ ዳሩ ግን እኔ ማነኝ?» አልኩት:: እርሱም መለስ «ስለራስህም አታውቅምን? አንተ ነፍሳቶችን በችግር ከመጡበት ከማርስ ወገን ነህ፤ የማርስ ሰዎችም የኛን አምላኮች ይንቃሉ፤ አንተም እንዲሁ እንደሆንክ አውቃለሁ፤ የማርስ ሰዎችም ስለሮም ቅርሶችና አማልክት ክፉ እንደምትናገሩ፣ እኔ ያማልክት አለቃ አውቃለሁ:: ዳሩ ግን እናንተ ትናገሩ ዘንድ የምትመርጡትን አታውቁም:: ነፍሳቶቻችንንም ትፈራላችሁ» አለኝ:: እኔም መልሼ «ታዲያ ነፍሳቶቹስ የኛ ወገን አይደሉ፤ ለምንስ እንፈራለን፤ የምንናገረውስ ስለነሱ መልካም አይደለምን?» አልኩት:: «በኛ አምልኮ ውስጥ ውሸትና እውነት በናንተ አምልኮ በተቃራኒ ናቸው» አለኝ፤ «ለምን አልክ?» አልኩት:: እርሱም መለሰልኝ «እናንተና እኛ አንደጣኦትና አምላክ፤ እንደሃጢያተኛ ና ፃዲቅ፣ መጥፎና ጥሩ እስከመቼ እንተያያለን፣ የምትናገረውን ትኖረዋለህን? ደግሞስ እዚህ ሳለህ ለኔ ጥሩ ትመልሳለህ፣ በማርስ ሳለህ ስለኛ መጥፎ ትናገራለህ፤ ይህን እኮ እኔ አውቃለሁ:: ለመሆኑ ይህ ውሸት በማርስ ዕውነት ነውን?» አለኝ:: እኔ ያሰብኩትን ሁሉ በድምጽ የሚባርቀው ያማልክቱ ጌታ አበጥሮ ተናገረው:: ያወቀብኝ ስለመሰለኝም ደነገጥኩ::

በዚህ ስሜት ውስጥ ሳለሁ በጨለማው ውስጥ የተተከለው ፅሁፍ ከፊቴ ተደቀነ፤ «ትነካና ዋ!» ይላል:: «ይህ ታዲያ ምንድነው?» አልኩት:: «አንተነትህ ይህን ፅሁፍ ከትቦ በዓይንህ ላይ ለጠፈው:: የውጭኛው አእምሮህም በፍርሃት ነውጥ ይህንን መልዕክት አስተላለፈ፤ ስለዚህም ዓይንህን በገለጥክ ጊዜ ሁሉ ይህንን ታያለህ::» አለኝ:: የሚለው ሁሉ ትክክል ይመስል ነበር::

በጥቁሩ ጨለማ ውስጥ ሳለሁ፣ በግዑዙ የሚላወሰው የነገስታቱ አጋፋሪ የወይን ጠጅ የሚመስለውን መጠጥ ቀዳልኝ:: በዚህም ሰዓት «ትነካና ዋ!» የሚለው የጨለማው ጽሁፍ እንደሸራ ባለ ሰሌዳ ላይ ባማልክቱ ጌታ በሆነው እውናዊ አካል የግራ እጅ የተያዘ የጭንቅላት ምስል እየወጣ ይፃፍ ነበር:: ፅሁፉ አሁን ከፊቴ በዓይኔም ላይ ነበር:: አጋፋሪው የቀዳልኝን የወይን ጠጅ የመሰለውንም ለመጉንጨት እጄን ከብርጭቆ ጋር ሳገናኝ «ት» የሚለው ሆሄ ጠፋ:: በመቀጠልም የመጠጫውን ብርጭቆ ሳነሳው «ነ የሚለው ሆሄ ጠፋ:: ከዚያም ከንፈሬ ከብርጭቆው ጋር ሲገናኝ «ካ» የሚለው ቃል ጠፋ:: አሁን የወይን ጠጅ የመሠለውን መጠጥ በአንድ ትንፋሽ ያለማጣጣም ስጉነጭ በዙሪያዬ «ና» የሚል ቃል ሲያስተጋባ ተሰማኝ:: ከተቀመጥኩበት የማዕዘን ወንበር ተነስቼ ቆምኩ:: ዙሪያዬ ጨለማ ነበር:: ከኋላዬም በሮም ከተነገረኝ የሚመስል ምስል እንስት በዳልቻ የፊትና ዳሌ ሽራ በብርሃን ወራወር አየሁ:: «ና!» የሚለው ድምጽም ከእሷ እንደሁ አሰብኩ:: ወደ ርሷም ተጠጋሁ፤ ከአሸንክታቧ መሃል ባብዛኛው ሰውነቷም የነበረው ዕንቁ በጨለማው ውስጥ እንደሚበራም ይመስል ነበር:: በሮም እንደሰማሁት እንጅ በማርስ እንደማውቃት ግን አልነበረችም:: እርቃን ጭኖቿም የተራራቁ ነበሩ:: ከምድርም ጋር በሹል የተረከዝ ጫማ፣ ከማርስ ደግሞ ሐር የመሰለ አርቴፊሻልና ቡናማ የፀጉር ነዶ ነበራት:: እነዚህን አይቼ ስጨርስ ወደ ኋላዬ የሚስተገባ ድምጽ ይባርቅ ነበር:: እንደመወጀም ኃይል ነበረው:: ከፊት ለፊቴ ማዶ በወናው ላይ በተወጠረው ሸራም ላይ፣ ያማልክቱ ጌታ በግራ ዕጁ ይዞት ከነበረው በቀለም የተነከረ ጭንቅላት የሚወጣ ብርሃናማ ፅሁፍ «ዋ» በሚል ነጐድጓዳማ ድምጽ በህዳጉ ላይ ሲያሳየኝ ምንም እንደሆነ ሳይገባኝ በድንገት ከነበርኩበት ቦታ ተፍገምግሜ በአደባባዩ ወለል ተዘረርኩ:: ከዚህ በኋላ ምን እንደተፈጠረ አላወኩም::

በአዳራሹ ውስጥ የሚርመሰመሱ የሰው ልጆች፣ ሴቶች ልጆችም አየሁ:: አቋቋማቸው በውል ያማረ፣ ቡቲክ ውስጥ ከተተከሉ አርቴፊሻል ሰዎችም በእጅጉ የሚልቁ ነበሩ:: በአደባባዩ የውስጥ አዳራሽ ግድግዳ ላይ የሚብለጨለጩ፣ የሮምንም ጣኦት የሚመስሉ በመብራትና በእንቁ የተዥጉረጉሩ ስዕሎች ተሰቅለዋል

# የዘጋንባ ትረካዎች በግሽን ማረያም



በተስፋዬ ገብረአብ

...ደሴ ላይ ምሳ እየተመገብን ሳለ የዘጋንባ ድምጽ ተሰማ::

«... መቼም እስካሁን በሰላም ተጉዘናል:: የግሽኑ ሚካኤል ታክሎበት ደግሞ ቀጣይ ጉዞአችን ሰላማዊ እንደሚሆን አምናለሁ» በሚል መንደርደሪያ ዲስኩሩን አራዘመ «... ዋናው በንፁህ ልብ መጉዋዝ ነው:: እንዲህ ባለ ጉዞ ጥብቅ እምነት ያስፈልጋል:: እውነቴን ነው የምላችሁ እንደቀድሞው ምግባሬ ቢሆን በኔ ሀጢአት ምክንያት በመንገዳችን ላይ እክል ይገጥመን ነበር:: ዛሬ ግን ያው እንዳልኩዋችሁ መንፈሳዊ ሰው ሆኛለሁ:: ሀጢአቴን በሙሉ ለየካ ሚካሄል ተናዝዤ ንሰሀ ገብቻለሁ::»

ገበታው ከፍ ብሎ ቡና እየጠበቅን ባለበት ደቂቃ ዘጋንባ ዳግም ከገጠመኞቹ መካከል አንድን መዝዞ ጀባ አለን፣

«...ኢህአዴግ የገባ ሰሞን የንግድ እንቅስቃሴው ቀዝቅዞ፣ የመኪና ስራ ተቋርጦ ስለነበር እንደ ድለላ ያለ ስራ ነበር የምሰራው:: በክረምቱ ወራት ታዲያ ለአንድ ፓይለት አንድ ስራ ሰርቼለት ከገመትሁት በታች ከፈለኝ:: አምስት መቶ ብር ጠብቄ አራት መቶ ብር ሰጠኝ:: ሆኖም ዝም ብዬ አልተስማማሁም:: ለፓይለቱ በግልፅ ነገርኩት:: «የሰራሁልህ ስራ የአምስት መቶ ብር ነው ቀሪውን ወዲህ በል» አልኩት:: ይገርማችሁዋል፤ የንቀቱ ብዛት በቁም ነገር እንኳዋ አላናገረኝም::

«ካልፈለግህ አራት መቶውን ወዲህ በል» አይለኝ መሰላችሁ? በጣም ተናደድኩ፤ እኔ ከተናደድኩ ሰይጣን ነኝ:: ፓይለቱ ይህን ባለማወቁ በጣም ተጎዳ:: ምክንያቱም ለዚያ የንቀት ንግግሩ ማካካሻ በእጥፍ ልቀጣው የወሰንኩት ወዲያው ነበር:: እንዳልኳችሁ ጊዜው ወያኔ የገባበት ሰሞን ነው:: ታዲያ በደንብ አጠናሁና አንድ ተንኮል ወጠንኩ:: ፓይለቱ የሚጠጣበት ካዛንቼስ አንድ ህቡእ ጉዋዳ አለች:: አንድ ቅደሜ ምሽት መኪናውን አቁሞ ከውስኪ ቤቷ ሲገባ የበቀል ውጥኔን በስራ ላይ አዋልኩት:: በቀጥታ በአካባቢው ወደነበሩ ታጋዮች አመራሁና፣

«ሐውዜንን በአይሮፕላን ከደበደቡት ፓይለቶች አንዱ እዚያ ቤት ተደብቆአል» አልኳቸው::

ጊዜው በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ስለሀውዜን ድብደባ የሚነገርበት ስለነበር ታጋዮቹ ባንድ አፍታ ስሜታዊ ሆኑ:: ጠመንጃቸውን ወዲያውኑ አቀባብለው «ምራን ወደ ጨፍጫፊው ሰው» አሉኝ::

«አይ፣ ፓይለቱ እኔን ካየኝ የደርግ ኢሰፓ አባላት የሆኑ ጉዋደኞቹ ስለሚበቀሉኝ እኔ አልመራችሁም» ብዬ ውስኪ ቤቱን በሩቅ አሳየሁዋቸው:: ፓይለቱ የለበሰውን የልብስ አይነት፤ ጉዋዳ ውስጥ እንደሚገኝም በዝርዝር ነገርኳቸው:: ታጋዮቹ በሞቀ ስሜት «የህዝብ ልጅ» መሆኔን ነግረውኝ፣ ደጋግመው አመስግነውኝ ሲያበቁ ወደ ጠቆምኳቸው ቤት ሰተት ብለው ገቡ:: እኔም ወዲያው ከአካባቢው ተሰወርኩ:: ሁዋላ እንደሰማሁት፣ ታጋዮቹ እንደገቡ፣

«እገሌ የምትባለው የአይሮፕላን ነጂ አንተ ነህ» ሲሉ ነበር የጠየቁት::

«ልክ ነው» ይላቸዋል::

«በል ተነስ፣ ቀጥል» ይሉታል:

«ምናጠፋሁ?» ይላቸዋል ደንግጦ

«ንግግር አታብዛ፣ ተነስ ቀጥል» ይሉታል::

«ምናጠፋሁ? መሄድ እሄዳለሁ...እኔ ግን » እያለ ከተቀመጠበት ሲነሳ፣

«ከሀውዘን ድብደባ ጋር በተያያዘ የሚጣራ ነገር ስላለ ነው» ሲሉ ፍንጭ ይሰጡታል::

ይህን ጊዜ ፓይለቱ፣


«ኧረ ሀሰት ነው፤ እኔ የጦር አይሮፕላን አይደለም የምነዳው» እያለ እሪታውን ቢያቀልጥም አላመኑትም:: ሊያታልል መስሎአቸው ከግሮሰሪው እየነዱ ፖሊስ ጣቢያ አደረሱት:: እለቱ ቅዳሜ ስለነበር በዚያን እለት ምሽት ጉዳዩን የሚያይለት አልተገኘም:: በነጋታው እሁድ ተሲያት አካባቢ ግን ጥቆማው ሀሰት መሆኑ ተረጋግጦ ተለቀቀ:: እኔ መቼም በወቅቱ አንጀቴ ነው ቅቤ የጠጣው:: አንድ ሌሊት እስር ቤት ማደር ከመቶ ብር በላይ እንደሚከብድ አውቃለሁ:: ስለዚህ መቶ ብሬ ከስራ አልቀረችም:: መቼም የተረገምኩ ነበርኩ:: ድርጊቴን አሁን ሳስበው ግን ይፀፅተኛል:: ጊዜው የግርግር ነበር:: የፖሊስና ሌላው ሌላው ስርዓት ሁሉ ገና መልክ ያልያዘበት ነበር:: ወያኔዎቹ ወንጀለኛ ፍለጋ ከተማውን ሲያስሱ ውለው የሚያድሩበት ጊዜ ነበር:: ፓይለቱ በወቅቱ ቢያንገራግርና ታጋዮቹም የሀውዜንን ነገር እያስታወሱ ስሜታዊ ሆነው ከፍ ያለ ችግር ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮስ? ያው እንዳልኳችሁ ግን ለየካ ሚካኤል ይሄን ሁሉ ነግሬው ይቅር ብሎኛል...»

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# ምድርን ለብክለት የዳረጉ የኤሌክትሮኒክስ ምርቶች

*በአብዱ መሐመድ*



ከጥቂት ወራት በፊት የዓለማችን የሕዝብ ብዛት ሰባት ቢሊዮን ደርሷል የሚለው የታይም መጽሔት እንደሚጠቁመው የምድርን የቆዳ ስፋት በመንተራስ አንድ ግለሰብ የ1.8 ሄክታር ወይም ሁለት ጎልፍ መጫወቻ ሜዳ ስፋት የሚያክል የመሬት ድርሻ ይኖረዋል::

አሁን ባለው ነባራዊ እውነታ፣ የሰው ልጅ ከተፈጥሮ የሚደርሰውን ይህን ድርሻ እያወራረደ የሚያልፈው በአማካይ 2.2 ሄክታር ላይ የጥፋት አሻራውን እያሳረፈ ነው:: ይህንን መረጃ ያቀረበው የተባለው የአካባቢ ጥበቃ ተቋም ዳይሬክተር ሮብ ሆልድ ዌይ እንደሚገምቱት አሁን በህይወት የሚገኝ የሰው ልጅ በሙሉ የአውሮፓውያንን የተንደላቀቀ ኑሮ የመኖር ዕድል ያግኝ ከተባለ የምድርን ስፋት ያላቸው ሶስት ፕላኔቶች ማዘጋጀት ይኖርብናል::

ሥያሜውን «የአውሮፓ ሕብረት የኤሌክትሪክና የኤሌክትሮኒክ ቁሳቁሶች ውዳቂ (Europian Union's Waste from Electrical and Electronic Equipment)» ወይም በምህፃረ ቃል «ደብሊው.ኢ.ኢ.ኢ. (WEEE)» ባደረገው ተቋም አማካኝነት የተተከለው ሐውልት ይህንን የሰው ልጅ ፍላጎትና ጥፋት የሚያሳይ ነው::

እግር ጥሎት እንግሊዝ፣ ለንደን ተገኝቶ ሳውዝ ባንክ አካባቢ ጎራ ያለ ግለሰብ ይህን በዲዛይነር ፖውል ቦኖ በሰው ቅርጽ ተነድፎ የተሰራውን ሰባት ሜትር ርዝመት ያለው ሐውልት የተመለከተ የቲም ብሮቶን ፊልም ላይ የሚታየውን ሮቦት ሊመስለው ይችላል::

ዲዛይነር ፓውል ቦኖ ከቀረፀው ይህ ሐውልት ከትናንሽ የኤሌክትሮኒክ ቁሶች ቫኪዩም ክሊነር፣ ካውያና የፂም መላጫ የመሳሰሉ 95 ቁሶችን የያዘ ነው:: ትላልቅ ከተባሉ የኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች ደግሞ እንደቴሌቪዥሮን፣ ዲቪዲ ማጫወቻ የመሳሰሉ 55 ቁሶች፤ እንዲሁም 35 ሞባይል፣ 10 ማቀዝቀዣና ስድስት ማይክሮ ዌቭ ማብሰያዎችን የያዘ ነው:: አርቲስቱ በሰው ምስል አድርጎ በአንድ ላይ ሶስት ቶን ክብደት ከሚመዝኑ 533 የተለየዩ የኤሌክትሪክ እና ኤሌክትሮኒክስ ውድቅዳቂዎች የቀረፀው ሐውልት የሰውን ልጅ ጥፋት ለማመልከት የታሰበ ነው:: እውነታውም በሰለጠነው ዓለም የሚኖር መካከለኛ ገቢ ያለው ግለሰብ በሰባ ስምንት ዓመት ዕድሜ ዘመኑ የሚጠቀምባቸውና በብልሽትና በለውጥ ወደ ምድር የሚወረውራቸውን ቁሶች በተመለከተ ለረጅም ዓመታት በተደረገ ጥናት መነሻ በማድረግ የሰው ልጅን ጥፋት ለማሳየት የተቀረፀ ነው::

አሁን ያለው መረጃ እንደሚያመለክተው ከአገልግሎት ውጪ ሆነው ከሚጣሉ የኤሌክትሪክና የኤሌክትሮኒክስ ቁሶች ውስጥ 90 በመቶ የሚሆኑት ጉድጓድ ውስጥ ይቀበራሉ፣ ወይም በየጥጉ ተወሽቀው ይቀመጣሉ:: ከነዚህ ውዳቂዎች አንዳንዶቹ ለመተንፈሻ አካልና ለተዛማች በሽታዎች የሚዳርጉ እንደ ሊድ ፎስፌት እና ባሪየም የተባሉ ኬሚካሎች ከያዙ ማዕድኖች የተዘጋጁ ናቸው::

በዓለም አቀፍ የዕቅድ ነደፋ ተቋም ተወካይዮች ማቲስ ዋክሮርገል እና ዊሊያም ሪስ በ1990ዎቹ መጨረሻ የቀረበው ሪፖርት እያንዳንዱ ሰው በህይወት ዘመኑ መጠለያና ምግብን ጨምሮ የሚያወራርደውን ፍጆታ የሚያመለክት ነው:: ቁሶችን ያከተተው ይህ ሪፖርት በጥቅሉ የሚያስረዳው፣ እያንዳንዱ ሰው በየቀኑ የገዛ ህይወቱን አደጋ ላይ የማጥልና ምድርን የሚበክል የጥፋት አሻራ እያሳረፈ በመጓዝ ላይ መሆኑን ነው::

የከባቢ አየርን በመበከል ቀዳሚ ከሆኑ በካይ ጋዞች ቀጥሎ በአሁኑ ወቅት ምድርን እየበከሉ የሚገኙት ቴክኖሎጂ ያፈራቸው የኤሌክትሮኒክስ ውዳቂዎች ለመሆናቸው እያንዳንዱ ጓዳውን በመፈተሽ ማረጋገጥ የሚችለው ሀቅ ነው:: ከሰለጠኑ ሀገራት በእንግሊዝ ብቻ በየዓመቱ 220 ሚሊዮን የኤሌክትሪክ ምርቶች ለገበያ ይቀርባሉ:: በዚችው ሀገር 90 ሚሊዮን የሚገመቱ የተበላሹ ወይም ቴክኖሎጂ የቀደማቸው የሞባይል ቀፎዎች በግለሰቦች መኖሪያ በየስርቻውና በየመደርደሪያው ተጥለው ወይም ተቀምጠው እንደሚገኙ በለንደን የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የቀረበው ጥናት ይጠቁማል:: በሞባይል ቀፎ የሚመጡ ጨረሮች የሚያስከትሉትን ጉዳት በተመለከተ ጥናት እንዲያደርግ የተሰየሙ የአውሮፓ ኤክስፐርቶች በብራሰልስ ካቀረቡት ሪፖርት ውስጥ በዓለማችን ሕዝብ በቻይና በሕንድ ብቻ 1.5 ቢሊዮን ሕዝብ በየጉዳና የሚጓዘው አሮጌ ሥራቶችን እየጣለና ዘመናዊ የተባሉትን የሞባይል ቀፎዎች በእጁ እየጨበጠ ነው::

ከዚህ በመነሳት የደብሊው.ኢ.ኢ.ኢ. ዳይሬክተር በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች መካከለኛ ገቢ ወዳላቸው ሀገሮች በተካተቱ ቁጥር እየተጨመረ የሚመጣወን የአሌክትሮኒክስ ውዳቂ መቆጣጠር የማይቻልበት ችግር መፈንዳቱ አይቀሬ ነው ይላሉ:: ለዚህ መፍትሔው ደግሞ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ቁሶቹን የማያመርቱ ድርጅቶች ከአገልገሎት ውጪ የሆኑ የኤሌክትሮኒክስ ምርቶችን ዳግም ወደ ሥራ የሚያውሉበትን፣ አልያም ጉዳት ሳያስከትሉ የሚወገዱበትን መላና ቴክኖሎጂ ካላዘጋጁ ከብድርና ከገበያ የሚያገል ዕገዳ መጣል ነው:: ይህንን ጥያቄ የተቀበሉ ግዙፍ ባንኮች አካባቢን የማይበክሉ ኢንዱስትሪዎችን ለማበረታታትና ለማገዝ የሚያስችል «ዘ ኢኩዌተር ፕሪንስፕል» የተባለ ሰነድ አዘጋጅተው መንቀሳቀስ ከጀመሩ ዓመታት እየተቆጠሩ ነው:: ከነዚህ ውስጥ ዩናይትድ ስቴትስ ሲቲ ግሩፕ፣ ጄፒ ሞርጋን ቼዝ፣ ባንክ ኦፍ አሜሪካ፣ ኤ.ቢ.ኤን አምሮ እና ኤች.ኤል.ቢ.ሲ የተበሉ ትላልቅ ባንኮች የሚጠቀሱ ናቸው::

እ.ኤ.አ ሰኔ 12/2005 የአንስተይን 100ኛ የልደት በዓልና የስፔሻል ቲዩሪ ኦፍ ሬላቲቪቲ 50ኛ ዓመት ሲከበር መሪ ቃል የነበረው «አካባቢያችንን ከኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ ብክለት እንጠብቅ» የሚል ነበር:: ደብሊው.ኢ.ኢ.ኢ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ይህ መሪ ቃል የተመረጠው፣ በጀርመን አልምወርት በርግ የተወለደው አልበርት አንስታይን «ፎቶ ኤሌክትሪክ ኢፌክት» የተሰኘው ግኝቱ ለኮምፒዩር፣ አይ-ፖድ፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ ለመሳሰሉ የኤሌክትሮኒክስ ቁሶች ያበረከተውን አስተዋጽኦ መነሻ በማድግ ነው:: ከዚሁ በተጨማሪ የህዋ ምርምር ባለሙያዎች መንኮራኩሮችን ወደ ህዋ ለመላክና ፕላኔቶች ከምድር ያላቸውን ርቀት ለመለካት የቻሉት «ስፔሻል ሬላቲቪቲ» የተባለውን የአንስታይን መላ ምት ወደ ተግባር በመለወጥ ነው::

ይህ የክብረ በዓሉ መሪ ቃል የተመረጠው ብዙ ውዝግቦችን ባስተናገደ ኮንፈረንስ ነበር:: በአካባቢ ጥበቃ ባለሙያዎች እ.ኤ.አ በ1999 ታይም መጽሔት የክፍለ ዘመኑ ምርጥ ሳይንቲስት ብሎ የሰየመውን አንስታይንን መዘከር ያለብን ከባቢ አየርን ከብክለት እንጠብቅ በሚል መፈክር መሆን አለበት የሚል አጀንዳ አቀረቡ:: ይህንን ሀሳባቸውን ለማጠናከርም ፈረንሳይያዊው የሂሳብ ሊቅ ጆን ፎየር እ.ኤ.አ በ1822 ያዘጋጀውን የህይወትና የከባቢ አየር ትስስር እየተነተኑ በከባቢ አየር ላይ የሚደርሰውን ጥፋት በዝርዝር አቀረቡ::

በሌላ በኩል የቀረቡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከተቃጠለ ነዳጅ፣ ከደን ቃጠሎ ወደ ከባቢ አየር የሚዘልቀው ካርቦን ዳይ ኦክሳይድ በከባቢ አየር ውስጥ አንድ መቶ ዓመት ይቆያል:: ከከብቶች ፍግና ከብስባሽ የሚተነው ሚቴን (methane) የተባለው ጋዝ ከካርበን ዳይ ኦክሳይድ ከ20-30 እጥፍ ሙቀት ማመቅ የሚችልና ለሙቀት መጨመር ከ15-20 በመቶ ድርሻ ያለው ነው:: ከ1930 ጀምሮ በመኖሪያ ቤት ለማቀዝቀዣነት ከምንጠቀምበት ፍሪጅ የሚወጣው «ክሎሮ-ፍሎሮ-ካርቦን» (cfc) በከባቢ አየር ላይ 400 ዓመት መቆየት የሚችልና ከካርበን ዳይ ኦክሳይድ አሥራስድስት ሺህ ጊዜ የሚበልጥ አደገኛ መርዝ ሲሆን አካባቢን በመበከል ያለው ድርሻ ከጠቅላላው 20 በመቶ ነው:: በተጨማሪም ከማዳበሪያ በምድር ኬሚካላዊ ውህደት ወደከባቢ አየር የሚዘልቀው «ናይትረስ ኦክሳይድ» ($N_2O$) ከካርበን ዳይ ኦክሳይድ 200 እጥፍ ለሙቀት መጨመር ምክንያት መሆኑን ይጠቁማል::

ከዚህ በመነሳት የኤሌክትሮኒክስ ውዳቂዎች ብዙም አያሳስቡም የሚለውን የመከራከሪያ እጀንዳ ያደረጉት በወቅቱ በታይም መጽሔት የቀረበውን ዜና በመጥቀስ ነው:: መጽሔቱ እ.ኤ.አ ግንቦት 9/2005 ገጽ 17 ላይ ያሰፈረው ዜና በእንግሊዝ፣ ለንደን ኦክስፎርድ ጎዳና ላይ ብቻ 300 ሺህ የታኘኩ ማስቲካዎችን ለማፅዳት በዓመት 290 ሚሊዮን ዶላር እንደሚወጣ የሚገልፅ ነው:: ስለዚህ ስለኤሌክትሮኒክስ ውዳቂዎች ከመጨነቃችሁ በፊት የምታኘኩትን ማስቲካ በአግባቡ አስወግዱ የሚል ነበር::

ይሁንና ግን በመጨረሻ በደብሊው.ኢ.ኢ.ኢ. የቀረበው ጥያቄ ሚዛን ደፍቶ «ምድርን ከኤሌክትሮኒክስ ቁሶች ብክለት እንጠብቅ» የማለው ነበር በክብረ በዓሉ ላይ ቀዳሚ መፈክር የሆነው:: በፊዚክስ የኖቤል ተሸላሚ የሆነው አልበርት አንስታይን በኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂ ያበረከተውን አስተዋጽኦ የሞነዘከረው ዓለማችንን ወደ ተራራ ቁልል የቀየሩና ምድርን እየበከሉ የሚገኙትን ውዳቂዎች ሥርዓት እንዲይዙ በመጠቆም ነው ተባለ:: ሀሳባችሁ ቀዳሚ ሆኖ ተመረጠላችሁ የሚል የእንኳን ደስ ያላችሁ ዜናም በድርጅቱ ድረ-ገጽ፣ «www.weeman.org» ላይ ተጥለቀለቀ:: የአውሮፓ ሕብረት በመደበው ከፍተኛ በጀት አማካኝነትም በ533 በኤሌክትሮኒክስ ውድቅዳቂዎች የታነፀው የሰው ምስል የያዘ ሐውልት በእንግሊዝ፣ ለንደን በሚገኘው ሳውዝ ባንክ ፊት ለፊት ተተከለ::

# መንገድ ላይ

* * *

ተሲያት ላይ ደሴን የሁዋሊት በመተው የሳር ስጋጃ የተነጠፈበትን የቦሩ ሜዳ አልፈን ወደ ግሸን ማርያም ጉዞ ሆነ:: የቦሩ ሜዳን ያለበሰው አደይ አበባ አውቆ በቀል አይመስልም:: የዘሩን ያህል ከጫፍ እጫፍ ግጥግጥ ብሎ አይንን ይማርካል:: መንገዳችን ላይ አስደሳች ዜና ከመኪናችን ሬድዮ ሰማን:: ሚሊዮን ወልዴና ደራርቱ ቱሉ ሲድኒ ላይ የማሸነፋቸው ዜና:: ጉዞአችን በሀሴት የተሞላ ሆነ::

ኩታ በርን አልፈን የቁንዲን ወንዝ ተሻገርን:: በምንጉዋዝበት ያልሰለጠነ ጉዳና ግራና ቀኝ ሰማዩን የነኩ ተራሮች ተዘርግተዋል:: የወሎ ገበሬዎች ከ45 ዲግሪ በላይ የሆነ መሬት ላይ በአግድመት እያረሱ እህል ማምረታቸው ፈታኝ ነው:: ለጥ ባለ ምድር ላይ የሚከናወነው የአድአ ገበሬዎች የእርሻ ስራ አሁን ከማየው አንፃር በአድካሚነት ደረጃው ሲመዘን የሰማይና የመሬት ያህል ይራራቃል:: በዚህ አስቸጋሪ መሬት ላይ የዝናብ እጥረት ሲታከልበት የወሎ ገበሬዎች ህይወት ምን ያህል አስቸጋሪ ሆኖ እንደኖረ ታሰበኝ::

* * *

ዘጋንባ ዝም አላለም ...

«ሁዋላ ታዲያ ፓይለቱ ላይ ያን ጥቆማ ያደረኩት በፖለቲካ ዓላማ ምክንያት መስሎአቸው ወያኔዎቹ ሊይዙኝ ያፈላልጉኝ እንደነበር ሰማሁ:: «ፀረ ህዝብ» እያሉ ይሰድቡኝ እንደነበር ስሰማ ግን በሳቅ ነው የፈነዳሁት:: እኔ ምኔ ሞኝ ሆኜ ታዲያ፤ ከዚያ ወዲህ እስከዛሬ ካዛንቺስን ረግጬ አላውቅም:: ለነገሩ ፓይለቱ ገንዘቤን ስላስቀረብኝ ያን ፈፀምኩ እንጂ እኔ በፖለቲካ ምክንያት ከማንም ዳር ተጋጭቼ አላውቅም:: እኔ ፖለቲካ አልወድም፣ አላውቅምም:: ይገርማችሁዋል፤ የኤርትራን መገንል እንኳን በጣም ዘግይቼ ነው የሰማሁት::

«አሁን እዚህ የኤርትራ ስም ሲጠራ አምባገነኑ ኢሳያስ አፈወርቂ ስለሚባለው ሰውዬ.. ወይ ስለጦርነቱ ምናምን የማስታውስ ይመስላችሁዋል? በፍፁም» 'ስለ ኤርትራ ሲነሳ ማን ትዝ ይልሃል?' ብትሉኝ 'በርሄ አስመላሽ' ነው የምላችሁ..»

ዘጋንባ ይህን ብሎ ሲያበቃ ዲስኩሩን ገታ አደረገ:: ምን ያህል እየተደመጠ እንደሆነ ለማረጋገጥ የፈለገ ስለመሰለኝ፣

«በርሄ አስመላሽ ማነው?» ስል ጠየቅሁት::

«.. በርሄ ኤርትራዊ አይደለም» ሲል ቀጠለ «የአድዋ ሰው ነው:: ግን ያው በልጅነቱ ነው ከአድዋ ገጠር የወጣው:: አዲሳባ ገብቶ፣ ኬክ ቤት ተቀጥሮ ብዙ አመታት ካገለገለ በሁዋላ የራሱን ኬክ ቤት ከፈተ:: በቃ:: ከመጠሪያ ስም በቀር በርሄ ያው እንደኛው አዲሳበቤ ነው:: በዚህ ላይ ልክ እንደኔ ፖለቲካ የሚባል ነገር አያውቅም:: አይወድም:: የአመቱን ገብርኤል ካልሆነም ሌላ በአል አያከብርም:: መስከረም 2፤ ግንቦት 20 ሲባልም ተገኝቶ አያውቅም:: ፋሲካ የለ፣ እንቁጣጣሽ የለ፣ ሌትና ቀን ስራ ነው:: በርሄ ገንዘብ ማስገባት እንጂ ማውጣት አይወድም:: እና ታዲያ ኤርትራውያኖች በርሄ ትግራይ ነው ብለው ነበር የሚያስቡት:: የትግራይ ሰዎች በበኩላቸው ወደነርሱ ስለማይመጣ ኤርትራዊ ነው ብለው ደምድመው ነበር:: እሱ ግን ሁለቱም ዘንድ አይቀርብም ነበር:: ጦርነቱ ተከስቶ የኤርትራውያን አፈሳ ሲጀመር ታዲያ የበርሄ ነገር መዝገብ ላይም ምንም ቦታ መረጃ ባለመገኘቱ 'ሁኔታው ያልታወቀ' ተብሎ ነበር የተመዘገበው:: አንድ ቀን የቀበሌ ሰዎች የበርሄን ነገር ለማጣራት ፈልገው ኬክ ቤቱ ብቅ አሉና እንደዋዛ በርሄ 'ያንተ ነገር ታዲያ ከወደ የትኛው ነው?' ይሉታል:: በርሄ ለቀልድ የጠየቁት መስሎት 'በርሄ ፖለቲካ አያቅም፤ አዲስ አበቤና ነጋዴ ነው' ብሎ ይመልስላቸዋል:: ይህን ንግግር የቀበሌ ሰዎች እንደሚመቻቸው ተረጎሙት:: 'ኤርትራዊ መሆኑን ለማድበስበስ ብሎ ነው እንዲህ መናገሩ' ይሉና ቅዳሜ ማምሻውን ጋማውን ያዙት:: የምር ነገር ሲመጣ በርሄ 'እንዴ ምን ነካችሁ እኔኮ አድዋ ነኝ' ይላቸዋል:: ማን ይስማው? እሁድ ጉዞ ሆነ:: እውነቱን ነው ...የተፈፀመ ታሪክ ነው የምነግራችሁ... ከዚያማ በርሄ ሆዬ በግርግሩ የሚመሰክርለት ጠፍቶ በጥድፊያ ተላከ ወደ ኤርትራ:: ጉዞው በአድዋ በኩል ስለነበር ታዲያ ልክ አድዋ ከተማ እንደገባ አንገቱን በመስኮት ብቅ አድርጐ 'እኔ በርሄ ነኝ፤ የአስመላሽ ልጅ ነኝ' እያለ እሪታውን እንደ አምቡላንስ አቀለጠው::

ሆኖም ያመነው አልነበረም:: እትብቱ የተቀበረው እዚሁ ነው እያለ ቢማፀንም «ወክልና ሂድ፣ ይላክልሀል» ሲሉ ቀለዱበት ፖሊሶቹ:: እና በቃ በርሄ ኤርትራ ገባ:: በሶስተኛው ወር ደግሞ ከኤርትራ ከተባረሩት ኢትዮጵየውያን ጋር ተመልሶ ተባርሮ መጣ:: እና በተረጋጋ ሁኔታ ምስክር ቆጥሮ ኢትዮጵያዊነቱን በማረጋገጡ አዲስ አበባ መጥቶ ስራውን ቀጠለ:: ጣጣውን ጨርሶ ከትግራይ የተመለሰ ሰሞንም አግኝቼው «እንዴት ነው በርሄ?» ስል ጠየቅሁት::

«ኧረ ተወኝ ወንድሜ» አለኝ ሁለት እጆቹን ወደ ሰማይ ሰቅሎ «... መለስና ኢሳያስ አንድ ዙር ግራውንድ ቴኒስ ተጫወቱብኝ ከማለት ውጭ ሌላ ምን ይባላል::»

*/እፎይታ መጽሄት ጥር 1993 ዓ.ም/*

# የፕሌቶ የመንግስት...

ከሁሉም የሚሻል መንግስት አብዛኛዎቻችን ያለንበትን በዓይን የሚታየውን ዓለም ተሻግረው ባለፉ፣ በዚህም መልካም ማለት ምን እንደሆነ በማወቃቸው መልካሙን በሚያደርጉ ሰዎች የሚመራ አሪስቶክራሲ ይሆናል:: ሕጎችን አያወጡም፤ በራሳቸው ግለሰባዊ የመወሰን ነፃነት ያስተዳድራሉ:: ከሶፊስቶች ግምት በተቃራኒው፣ የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስተዳድሩትን ሕዝብ አይበዘብዙም:: ድርጊቶቻቸው በእውቀት የሚመሩ የበራላቸው ፍጡራን ከመሆናቸው ባሻገር፣ የሀሳባዊው ከተማ ትምህርታዊ እና ማህበራዊ ሥርዓት የግላዊ ጥቅም እና ዝና ማንኛውንም ሀሳብ ከአእምሮአቸው አሽቀንጥረው በማውጣት እንዲኖሩ ይጠይቃቸዋል:: ምንም ዓይነት ቤተሰብ ወይም ንብረት አይኖራቸውም:: ፍላጋቸው ሁሉ የጋራ ጥቅምን ለማምጣት ብቻ ይሆናል፤ እንዲሁም ድረጊታቸው ሁሉ ሁሉም ሰው እንደተሰማራበትና እንደችሎታው የሞራል ልዕልና እና ደስታ የሚያገኝበትን መንገድ የተከተለ ይሆናል::

ፕሌቶ ወደኋላ ባፈለቃቸው፣ ፖለቲካስ እና ሎውስ የፖለቲካ ሥራዎቹ ላይ እንደተቀመጠው፣ የጠቢብ ሉዓላዊ አገዛዝን እምነት መቹም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ ባያስወግደውም በተወሰነ መልኩ አሻሽሎታል:: ይህ ወደኋላ የታየው መሻሻል ከሁለት ነገሮች ጋር የተያያዘ ተደርጐ ይታሰባል:: የመጀመሪያው፣ የእውቀትን አስተምህሮ በተመለከተ ያደረበት ጥርጣሬዎች ከዚህ ቀደም በድብቁ እውቀት እና በፖለቲካ ትግበራ መካከል ያለ ገልጽ ማያያዣ ስለመሆኑ በተናገረው ላይ ጥያቄ እንዲያጭርበት ሳያደርገው አልቀረም:: ከጊዜ በኋላ «ሀሳባዊ ዓለም» በማለት ስለተቀመጠው ግንዛቤ ሀሳቡን መቀየር መጀመሩ ግልጽ ነው:: በዚህ ላይ የተሻለ ምልከታ ማድረጉ ፓርሜኒደስ በተሰኘው ምልልስ ላይ ይታያል:: ይህ ፕሌቶ የአርስቶትልን ድምጽ በመጠቀም የተለያዩ የሚቃወሙ ሀሳቦችን ያሰፈረበት አስገራሚ የራስ ትችት ጽሁፍ ነው::

ሁለተኛው፣ ምናልባትም ይበልጥ ወሳኙ የሆነው፣ ፕሌቶ በ367 ዓ.ዓ የሲራኩስ ወጣት አምባገነን ገዥ ለነበረው ዲዮናይሲስ 2ኛ የፖለቲካ አማካሪው ሆኖ ነበር:: ይህ ሁኔታ በጋሃዱ ዓለም በፍልስፍና አማካኝነት የበራለት የፖለቲካ መሪ ለመቅረጽ ጥሩ እድል እንደሚሆን አስቦ ነበር:: ሆኖም ቤተ-መከራው የተሳካ ወጤትን አላረጋገጠም:: በዚህ ጊዜ ፕሌቶ እራሱን የፈላስፋ መሪ እሳቤው የተነነበት የፖለቲካ ውስስቦች ውስጥ አገኘው::

ፖለቲካስ ላይ ሀሳባዊ የፖለቲካ መሪ እሳቤውን በተመለከተ በመርህ ደረጃ አሁንም ቢሆን ቁርጠኛ ነው፤ ሆኖም አሁን ያነገበው ጭብጥ እንዲያ ያለ የፖለቲካ መሪ የመገኘቱ ነገር የማይሆን ነው የሚል ሲሆን በእርሱ ምትክ ሁለተኛው የተሻለ የመንግስት ዓይነት ድርጊታቸው በሕግ ገደብ የተበጀለትና ትክክለኛውን የሚያደርጉ መሪዎች የሚይዙት ይሆናል:: እንዲህ ያሉ መሪዎች እውቀት የላቸውም:: የፖለቲካ ሳይንስም ሆነ ጥበብ ምን እንደሆን ግንዛቤው የላቸውም:: ነገር ግን የመጠቁ ሕጐች ቢያነስ እውነተኛውን አመለካከት ይሰጧቸዋል፤ የእውነተኛ አመለካከት አገዛዝ ደግሞ ከአግባብ የለሽ እና ወደ አንድ ወገን ከሚያመዝን አገዛዝ የተሻለ ነው::

ይሁንና ግን እነዚህ ምጡቅ ሕጎች ከየት እንደሚመጡ በጥቅሉ ግልጽ አይደለም:: ፕሌቶ ምናልባትም ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ያዘጋጀው የመጨረሻ ምልልስ (ሎውስ) የሕግን የመጨረሻ ጫፍ ያስቀምጣል:: በዚህ ምልልስ ላይ «ማግኔዚያ» በመባል የተገለፀው ሀሳባዊ የፖለቲካ ማህበረሰብ በእያንዳንዱ ዝርዝር እንቅስቃሴ የሚተዳደረው «ኖክቸርናል» የተባለው ምክር ቤት በሚያወጣቸው እና ተግባር ላይ በሚያውላቸው ሕጎች ነው:: የምክር ቤቱ አባላት ሪፐብሊክ ላይ ከተገለፁት «ጠባቂዎች (ጋርዲያንስ)» ጋር ተመሣሣይ ናቸው፤ ነገር ግን አሁን የእነሱ ጥበብ በግላዊ የመወሰን ነፃነታቸው ብቻ ሀገሪቱን እንዲመሩ አያስችላቸውም:: ተግባራዊ ሊሆን የሚችልና ከሁሉም የተሻለ የመንግስት ዓይነት ፍፁሚዊ የሆነ ባይሆንም የጥበብ ስብስብ እና ጥርቅም ያለው በሕጎች የሚመራ ነው የሚለው የፕሌቶ የመጨረሻ አቋም ነው:: በእንዲህ ያለ አወቃቀር የዜጎች የሞራል ልዕልና በጣም ቁርጥራጫ (አናሳ) የሆኑትን ጨምሮ እያንዳዱን የህይወት ዝርዝር ክፍሎች ለሚቆጣጠሩ ሕጎች መገዛት ይሆናል::

ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ልዩ ቅኝት

በኤልያስ ገብሩ

# ክረምትና የፔንሲዮን ጓዳዎች




በአዲስ አበባ፣ በተለይም የሥራ፣ የንግድና የሰው እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም የመጠጥና የሌሊት ምሽት ክበቦች በሚበዙባቸው ዋና ዋና አካባቢዎች የአልጋ ኪራይ አገልግሎት የሚሰጡ ፔንሲዮኖች ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከተ እንደመጣ ይነገራል፡፡ አተኩሮ የተመለከተው በርግጥም ቁጥራቸው መብዛቱን ያረጋግጣል፡፡ እነዚህ «አልጋ» ቤቶች በእንግሊዘኛ «Guest House» (ገስት ሐውስ) ተብለው የእንግዳ ማረፊያነት ግርማ ሞገስንም ይጎናፀፋሉ፡፡

በተለምዶ ቺቺኒያ በሚባለው አከባቢ የሚገኘው ጌትነት ፔንሲዮን እንግዳ ማረፊያ ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ የሆነው አቶ ጌትነት አለሙ ሁለቱ ስያሜዎች ልዩነት እንዳላቸው ይናገራል፡፡ «እንግዳ ማረፊያ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ሁሉም ነገር ተሟልቶ ያለበት ሲሆን መኝታ ክፍል፣ ምግብ ማብሰያ፣ ፍሪጅ፣ የላውንደሪና የኢንተርኔት አገልግሎትን ይሰጣል፡፡ እንዲሁም እንግዶች ከ24 ሰዓት በላይ እንደየዕቅድና ፍላጎታቸው ይጠቀሙበታል» ሲል ይገልፃል፡፡ በተጨማሪም ለዚህ የሚከፍሉት ዋጋ ቁርስን ይጨምራል፡፡ ሁሉም ደንበኛ እንደየአገሩ ባህልና ልማድ ምግብ አብስለው እንደሚጠቀሙም አቶ ጌትነት ተናግሯል፡፡

ሆኖም ፔንሲዮን የአልጋ አገልግሎት ብቻ ይሰጣል፡፡ የአገልግሎት ጊዜውም ከ12 ሰዓት አይበልጥም፡፡ ብዙ ጊዜ የፔንሲዮን አከራዮች ደንበኞቻቸውን «ለአዳር ወይስ ለጊዜያዊ» በማለት ይጠይቃሉ፡፡ ቤቶቹ የሚከራዩት በሰዓት ሲሆን አንዳንዴ ደንበኞች በሚበዙበት ጊዜ [ቅዳሜና እሁድ] ለሁለት ወይም ለሦስት ሰዓታት ያህል ብቻ ይከራያሉ፡፡ ሰዓቱም ሲደርስ በሩን ማንኳኳት የተለመደ ነው፡፡ ደንበኛውም ክፍሉን መልቀቅ ካልፈለገ ተጨማሪ ብር መክፈል ግድ እንደሚለው የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡

አብዛኞቹ ፔንሲዮኖች ተመሳሳይ ፆታ ያላቸውን ሰዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ማሳደር ይከለክላሉ፡፡ አንዳንድ ቦታ ተጨማሪ ብር ከፍሎ ማደር ይቻላል፡፡ የተቀሩት (በተለይ የሌሊት ተረኛ አልጋ አከራዮች) በድብቅ ያሳድራሉ፡፡ «ገስት ሀውስ» ለ24 ሰዓት፣ ለቀናት፣ ለሳምንታትና ለወራት ባለ አንድና ሁለት መኝታ ክፍል ተብሎ ይከራያል፡፡ ዋጋቸውም ለውጭ አገር ዜጎች እና ለኢትዮጵያኖች የተለያየ ነው፡፡ [ለአበሻ ይቀንሳል፡፡]

«እዚህ አገር እንግዳ ማረፊያን እንደ ፔንሲዮን እንጠቀምበታለን» የሚለው አቶ ጌትነት የአገር ውስጥ በርካታ ኢትዮጵያኖች እንግዳ ማረፊያ አክብደው ስለሚመለከቱት፣ የውጪ አገር ዜጎች እና የተወሰኑ ሐብታምና ትልልቅ [ታዋቂ] ሰዎች ገብተው ሲወጡ ስለሚመለከቱ፣ እንዲሁም [በቂ ብር ያላቸው ሰዎች ጭምር] የሚከፈለው የብር መጠን ከፍተኛ መስሎ ስለሚታያቸው ለ«ገስት ሐውስ» ትልቅ ፍራቻ እንዳለ ይናገራል፡፡ በዚህም ምክንያት የአገር ውስጥ ደንበኞችን ለመሳብ (በአማርኛ) «ፔንሲዮን»፣ እንዲሁም የውጭ አገር ዜጐችን ለመያዝ ደግሞ በእንግሊዘኛ «Guest House» ተብሎ እንደሚፃፉ አስረድቷል፡፡

የ«ገስት ሐውስ» ሥራ ወቅታዊ በመሆኑ ምክንያት ሥራው በሚቀዘቅዝበት ጊዜ የፔንሲዮን ተጠቃሚዎች እንደሚጨምሩም ይገለፃል፡፡

## ጉዞ ወደ ኢትዮጵያ

በመካከለኛው ምስራቅ ባሉ የአረብ አገራት የአየር ንብረቱ ሞቃት በሚሆንበት [በኢትዮጵያ በክረምት ወራት] ጊዜ የበርካታ አረብ አገር ዜጎች [ባለትዳርና ወጣቶች] ትኩረት ወደ ኢትዮጵያ እንደሚሆን የምትገልፀው ወ/ሮ ፅጌረዳ ገረመው ነች፡፡ የተለያዩ የውጭ አገር ዜጐች፣ በውጪ የሚኖሩ ትውልደ ኢትጵያውያን እና የአረብ አገር ወንዶች በክረምት ወራት ወደ አገራችን ስለሚመጡ በመዲናችን አዲስ አበባ ከተማ በተለይም በተለምዶ «ቦሌ ሩዋንዳ» ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ያሉ እንግዳ መቀበያ ቤቶች ገበያቸው ደርቶ በብዛት እንደሚከራዩ ወ/ሮ ፅጌረዳ ትናገራለች፡፡

## የቦሌ ሩዋንዳ «ቢዝነስ»

በክረምት ወቅት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት የአረብ ወንዶች «ቪላ» ብለው የሚጠሩት የእንግዳ መቀበያ ቤት ንግድ ስለሚጨምር የውጭ ምንዛሪ መጠን ላቅ ያለ እንደሚሆን ይነገራል፡፡ በቦሌ ሩዋንዳ አከባቢም ያለው እንቅስቃሴ ከፍተኛ መሆኑም ይጠቀሳል፡፡ በዚህም ምክንያት የንግዱ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ስለመጣ እንግዳ መቀበያ ቤቶች የሚታጡበት ጊዜም እንዳለ የተገለጸ ሲሆን «አብዛኞዎቹ ባለትዳርና ወጣት የአረብ አገር ወንዶች በክረምት በዋነኝነት ወደ አገራችን የሚመጡት ከኢትዮጵያዊ ሴቶች ፍለጋ ነው» በማለት በግልጽ የምትናገረው ወ/ሮ ፅጌረዳ ለተለያዩ ጉዳዮችና ለኢንቨስትመንት ሥራም የሚመጡ እንዳሉ አስረድታለች፡፡

ይህንን ሀሳብ በመጋራት «የአረብ ወንዶች ዋና ዓላማቸው ሴት፣ ጫትና ሺሻ ነው፡፡ በቃ አለቀ፡፡» ስትል እየሳቀች የገለጸችው የጌትነት ፔንሲዮንና ገስት ሐውስ እንግዳ ተቀባይ (የአቶ ጌትነት ባለቤት) የሆነችው ወ/ሮ ረቂቅ አበበ ስትሆን አረቦቹ በክረምት እንደሚበዙ፣ ቪላ ቤት እንደሚወዱ፣ ሦስትና አራት በመሆን በጋር እንደሚኖሩ፣ ቪላ ፈልገው ሲያገኙ ደግሞ ገስት ሐውስን እንደሚለቁ ጠቅሳለች፡፡ አንድ አረብ ለወ/ሮ ረቂቅ ሴት እንደሚፈልግ ይገልጽላታል፡፡ እርሷም እንደማይጠፋ ገልፃለት ስታበቃ፣ «እኔ የምፈልገው ግን 13 እና 14 ዓመት የሆናችውን ሴቶች ነው» ባላት ጊዜ ቆሌዋ መገፈፉን (በጣም መደንገጧን) ታስታውሳለች፡፡ በኋላም «እንደዚህ ያለ ሴት የለም» ማለቷን በማለት መልሳለታለች፡፡

ከዚህ ቀደም በጣም ቆንጆ የተባሉ፣ የውጭ አገር ዜጋ ደንበኛ የነበራቸውና የአረብ ወንዶች «ቅምጥ» የያዟቸው ቆነጃጅቶች (ሴተኛ አፋሪዎች) እስከ 20 ሺህ ብር ድረስ ቤት በመከራየት አስፈላጊውን የቤት ዕቃ አሟልተው «ገስት ሐውስ» ያከራያሉ፡፡ እነዚህ ሴቶች ቢዝነሱን ካገኙ ራሳቸው ይሰራሉ፡፡ ሌሎች ሴቶችንም ከሌላ ቦታ እያመጡ ለቢዝነስ ሥራ በማሰማራት ሴቶቹ ከሚያገኙት 10 በመቶ ወይንም 50 እና 100 ብር እንደሚቀበሉ፣ የቤት ሠራተኞችን በ600 እና 700 ብር ቀጥረውለቢዝነስ ተጨማሪ የሰው ኃይል የሚያመቻቹ እንዳሉ ይገለፃል፡፡ «አንዳንድ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች ዋናው ቤታቸውን ለእንግዳ መቀበያነት በማከራየት «ሰርቪስ» ቤት ውስጥ ወይም ሌላ ቤት ተከራይተው እንደሚኖሩ አውቃለሁ፡፡» ትላለች ወ/ሮ ጽጌረዳ፡፡

የ«ገስት ሐውስ» ባለቤቶች ቢዝነስ ካርዳቸውን ወደ አረብና ሌሎች አገሮች በመላክ አዲስ ደንበኞች ወደ ኢትዮጵያ ቢመጡ ቆንጆ ሴቶችን ማግኘት እንደሚቻል ኢትዮጵያንና ሴቶቿን ጎብኝተው በሄዱ ወንዶች እንደሚያስነግሩ በሙያው የተሰማሩት ይገልፃሉ፡፡

## «ልጁ አሳዘነኝ»

በልደታ አከባቢ መንገድ ዳር ላይ «እሙ ፔንሲዮን» የሚባል አልጋ ማከራያ ይገኛል፡፡ አቶ አዳነ በርጋ የፔንሲዮኑ አልጋ አከራይ፣ ተቆጣጣሪና ኃላፊ ናቸው፡፡ አቶ አዳነ ከቀኑ ሥራ ይልቅ የማታው ቢዝነስ የተሻለ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ «ሁለት ወንዶችን በአንድ ክፍል ውስጥ በማሳደሩ ረገድ «የግብረ-ሰዶማዊነት ፍራቻ» አለ» የሚሉት አቶ አዳነ እንደዚህ ዓይነት ነገር የተከለከለ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ወንዶቹ «ተቸግረው ቢሆን እንኳን አናምንም» ባይ ሲሆኑ ገንዘብ እንጨምር ብለው የሚጠይቁ ደንበኞች መኖራቸውን አልሸሸጉም፡፡ ሴቶች ግን አብሮ ለማደር እንደማይጠይቋቸው አቶ አዳነ ገልጸዋል፡፡

አቶ አዳነ ስለ ገጠመኞቻቸው ሲናገሩ ሁለት ጥንዶች ምሽት ላይ ወደ ተከራዩት አልጋ ክፍል ከገቡ በኋላ «ከሌላ ወንድ ጋር አየሁሽ» በሚል ሰበብ ጭቅጭቅ ተነስቶ ወደ ድብድብ ጉዳይ ሲያመራ በመካከላቸው ገብተው ያስታርቋቸዋል፡፡ በድጋሚም ጥሉ ያገረሸና ፖሊሶች ይመጣሉ፡፡ ልጅቷም ከሱ ጋር ከሆነች እንደሚመታትና እንደሚያስቃያት በመናገሯ ፖሊሶቹ «እሷ ጋር እንዳትደርስ» በማለት ወንዱን ከክፍሉ ያስወጡታል፡፡ ልጁም ፖሊሶቹ ከሄዱ በኋላ ወደ ፔንሲዮኑ ተመልሶ በአጥር ላይ ሆኖ ሌሊቱን ሙሉ በመቆም ስሟን እየጠራ እንዳደረና እነሱም እንቅልፍ ሳይተኙ እንደነጋላቸው አቶ አዳነ ይናገራሉ፡፡ «የልጁ ህይወት አሳዘነኝ» ሲሉም ተናግረዋል፡፡

እሙ ፔንሲዮን እንደአብዛኞዎቹ ከእይታ «ሰወር» ያለ ቦታ ላይ ባለመሆኑ በአካባቢው ያሉ የሰፈር ልጆች ከሴት ወይም ከወንድ ጋር ሲገቡና ሲወጡ በጣም እንደሚሸማቀቁ፣ አንዳንዴም ተሸፋፍነውና ተደብቀው እንደሚሄዱ ተናግረዋል፡፡ እኔም የዚህ ቅኝት ፀሐፊ [እሁድ ምሽት] ሁለት ጥንዶች «ሰው አየኝ አላየኝ» በሚል ተጨናንቀው ከፔንሲዮን ቤቱ ሲወጡ ተመልክቻለሁ፡፡

## የባልና ሚስት ፍጥጫ

ከ22 ማዞሪያ ወደ ለም ሆቴል በሚወስደው መንገድ በስተቀኝ በኩል በሚታጠፈው ኮረኮንች መንገድ ዘልቀው ሲገቡ የተወሰኑ ፔንሲዮን ያገኛሉ፡፡ ታድሎ ተፈራ የተባለው የ14 ዓመት ታዳጊ ፈጣን እንግዳ ተቀባይ ነው፡፡ ታዳጊው ስሙ እንዳይገለፅበት የፈለገው ፔንሲዮን የቤተሰቦቹ ሲሆን፣ 17 የአልጋ ክፍሎች አሉት፡፡ ዋናው መኖሪያ ቤትም ደንበኞች ሲበዙ እንዳይመለሱ በሚል ለኪራይ ተዘጋጅቷል፡፡ ታድሎ ሰርቪስ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦቹን ትምህርት ሲዘጋ በክረምት ወራት በሥራ እንደሚያግዝ ይናገራል፡፡ የፔንሲዮን ቤቱ ደንበኞች የተለያዩና በርካታ ሲሆኑ፣ የኮሌጅ እና ዩኒቨርሰቲ ተማሪዎች፣ ምሽትና ሌሊት ላይ መጠጥ ጠጥተው የሚመጡ ሰዎች እና የውጪ አገር ዜጎች ይጠቀሳሉ፡፡

> አንድ አረብ ለወ/ሮ ረቂቅ ሴት እንደሚፈልግ ይገልጽላታል፡፡ እርሷም እንደማይጠፋ ገልፃለት ስታበቃ፣ «እኔ የምፈልገው ግን 13 እና 14 ዓመት የሆናችውን ሴቶች ነው» ባላት ጊዜ ቆሌዋ መገፈፉን (በጣም መደንገጧን) ታስታውሳለች፡፡



በእለቱ አንድ በእድሜ የገፋ ሰው «በግምት 16 ዓመት ቢሞላት ነው» ካላት ታዳጊ ሴት ጋር አብረው አድረው እንደወጡ ነገረኝ፡፡ «ቀደም ብለህ ብትመጣ ኖሮ ታያቸው ነበር» አለኝ፡፡ እንደዚህ ዓይነት ነገር የተለመደ እንደሆነና በእድሜ የማይመጣጠኑ ጥንዶች እንደሚመጡም ታዳጊው ይናገራል፡፡ አገባባቸውና አመጣጣቸው እንዴት ነበር አልኩት? ለምላሹ ፈጠን በማለት ማታ በሰውየው የቤት መኪና እንደመጡና ጥዋት ላይ እሷን በላዳ ታክሲ ከሸኙ በኋላ ሰውየው ከጥዋት ሁለት ሰዓት ገደማ እንደሄዱ ገለፀልኝ፡፡ «የቤት ልጆች» ከእድሜ ከሚበልጧቸው ትልልቅ ሰዎች ጋር ሲመጡ እንደሚያፍሩ፣ በቤት መኪና ውስጥ እንደሚደበቁ እና «ሰው እይልን» ብለው እንደሚጠይቁት፣ በሻርፕ ፊታቸውን እንደሚሸፋፈኑና ከወንዶቹ ቀድመው በእግር ሲወጡ ደግሞ «ሸኘን» ብለው እንደሚጠይቁና የተወሰነ መንገድ ድረስ እንደሚሸኛቸው ታዳጊው ተናግሯል፡፡

ከገጠመኞቹ መካከልም ሁሌም የማይረሳውን የባልና ሚስቶችን መገናኘት እየሳቀ እንዲህ ሲል ገለፀልኝ፡፡ ሁለት ባልና ሚስቶች ተጣልተው ነበር፡፡ አንድ ቀን ባልየው ከሌላ ሴት ጋር መጥቶ ከአልጋ ክፍል ሲወጣ ባለቤቱ እዚህ እንዳለ አውቃ ከሌላ ወንድ ጋር ስትገባ ይገናኛሉ፡፡ ባልየው ምንም ሳይናገር ከፔንሲዮኑ ሲወጣ ይዟት የነበረችው የቡና ቤት ሴት ተከትላው ስትወጣ ሚስቱ ግን እያለቀሰች ተመልሳ መሄዷን አውግቷል፡፡

እንዲሁም አንድ ሀብታም ሰው ሁለት ሴቶችን በመኪናው ይዞ ገብቶ ሁለት ክፍል በመያዝ ሌሊቱን ሙሉ ከአንዱ ወደ አንዱ ክፍል በመሄድ ማንጋቱን ተናግሯል፡፡ ለቢዝነስ አዳር መጥታ ብዙ ዩሮ፣ 1000 ዶላር እና ሶስት ሞባይል ከወንዱ ሰርቃ ልታመልጥ የነበረቸውን ሴት ይዞ የሰውን ንብረት እንዳስመለሰና 30 ብር (ቲፕ) እንደተሰጠው ታድሎ እየሳቀ አጫወተኝ፡፡

## የመኪና ታርጋ ሽፈና

22 ሁለት አካባቢ በሚገኘው ሰገን ፔንሲዮን የሚመጡ ደንበኞችን የሚያስተናግደው ወጣት በሁሉም የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎች አልጋ እንደሚይዙ፣ ከትዳራቸው ውጪ ከሌላ ሰው ጋር የሚመጡ መኖራቸውንና መኪና ይዘው የሚመጡ አንዳንድ ሰዎችም የመኪና ታርጋቸው እንዳይታይ «ሸፍኑልን» በማለት አጥብቀው የሚጠይቁ ደንበኞች እንደሚያጋጥሙት ገልጿል፡፡

ወደ ገፅ 18 ዞሯል

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

## ዜ ና ዎ ች

# ጃካራንዳ በአክሱም ሆቴል የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም አዘጋጀ

ጃካራንዳ ኢንተግሬትድ አግሮ ኢንዱስትሪ አ/ማ፣ የኩባንያውን እንቅስቃሴ አስመልክቶ በተከታታይ በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች ሲያዘጋጅ የቆየውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም በመቀጠል፣ ባለፈው እሁድ በአክሱም ሆቴል በርካታ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተገኙበት ስብሰባውን አከናወነ::

በአዋሽ ቢቮላ የዳልጋ ከብት ማደለብ ስራ፣ የፍየል እርባታና ማቆያ እንዲሁም የንብ ማነብ በማከናወን ላይ የሚገኘው አ/ምህበሩ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ቡኢ ከተማ ውስጥ የእንስሳት እርባታና የወተት ኃብት ልማት ሥራ በማከናወን ላይ እንደሚገኝ የኩባንያው ፕሬዝዳንት አቶ ደመላሽ ወጋየሁ በፕሮግራሙ ላይ ገልጸዋል:: በአሁኑ ወቅት ዓለምን በከፍተኛ ሁኔታ እያስጋት ያለው የአካባቢ አየር መዛባትና የምግብ ሰብል ችግር መሆናቸውን የተናገሩት አቶ ደመላሽ፣ ስጋቱንና ችግሩን ለመከላከል ዋነኛው አማራጭ የግብርና ስራን በአግባቡ መተግበር መሆኑን ጠቅሰዋል::

«ቀደም ሲል ቻይና፣ ሜክሲኮ፣ ማሌዥያ፣ ኮሪያ እና ሌሎች አገራት የነበራቸው የኢኮኖሚ እድገት ከኢትዮጵያ አይሻልም ነበር:: ይሁንና የግብርናውን ክፍለ-ኢኮኖሚ በትክክለኛው መንገድ በመተግበርና ካለው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ዛሬ ለደረሱበት ደረጃ ደርሰዋል» ያሉት ፕሬዝዳንቱ፣ «ከዚህ ተጨባጭ ተሞክሮ በመነሳት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ላይ ለውጥ ማምጣት የሚቻለው፣ አገሪቱ ያሏትን የተፈጥሮ ኃብቶች በአግባቡ መጠቀም ሲቻል ብቻ» መሆኑን አስምረውበታል::

በአቶ ደመላሽ እምነት፣ አሁን እየታየ ያለው የምግብ አቅርቦት እጥረት እጅግ አሳሳቢ ከመሆኑ የተነሳ መፍትሄ ሊያገኝ ከማይችልበት ደረጃ ላይ እየደረሰ ይገኛል:: ዛሬ አገራችን በምትመራበት ግብርና መር ፖሊሲ፣ የኃብት ባለቤቶች በአብዛኛው ግለሰቦች በመሆናቸው ከግለሰባዊ ኃብት ባለቤትነት ባሻገር የጋራ የኃብት ባለቤትነትን በመተግበር የጋራ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል አውስተዋል::

በዚሁ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ላይ የተሳተፉ በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎችና ተጋባዥ እንግዶች በገለፃው ደስታቸውን የገለፁ ሲሆን፣ ከሶስት ሳምንት በፊትም በሐዋሳ ከተማ ተመሳሳይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ተካሂዶ እንደነበረ ይታሰባል::

# በ2002 ዓ.ም፣ 12,035 ዜጎች ወደመካከለኛው ምስራቅ ሥራ ፍለጋ ከአገር ወጥተዋል

በሰናይት ግርማ

በያዝነው ዓመት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በአገናኝ ኤጀንሲዎች አማካኝነት በሕጋዊ መንገድ 12,035 ዜጎች ወደመካከለኛው ምስራቅ አገራት ለስራ ከአገር መውጣታቸውን የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሕዝብ ግንኙነት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ካሳሁን ጎፌ ባለሚ ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ:: እንዲሁም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና ከሕጋዊ ኤጀንሲዎች እውቅና ውጪ ከ2ሺህ በላይ ዜጎች ወደ ተመሳሳይ አገራት መሄዳቸውን አቶ ካሳሁን ገልፀዋል::

ከሥራ ጋር በተያያዘ በያዝነው ዓመት ከኢትዮጵያ የወጡ ሰዎች ቁጥር ብዛት ከ2001 ዓ.ም ጋር ሲነፃፀር በመጠኑ የመቀነስ አዝማሚያ እንደሚያሳይ ዳይሬክተሩ ተናግረዋል:: ለዚያም ምክንያቱ ቀድሞ በቁጥር 122 የነበሩት ኤጀንሲዎች በአሁኑ ወቅት በሕግ አማካኝነት ወደ 54 ዝቅ እንዲሉ በመደረጉ እንደሆነ አቶ ካሳሁን ጠቁመዋል::

ከሕግ አካላት ለሚቀርቡት ጥያቄዎች መረጃዎችን በመስጠት በሕገ-ወጥ መንገድ ዜጎችን ወደውጭ አገራት በሚልኩ አካላት ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እንደሚደረግ የገለጹት አቶ ካሳሁን፣ ከዚህም ጋር በተያያዘ በሕገ-ወጥ መንገድ ከአገር የወጡ 55 ዜጎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ መደረጉን አስታውቀዋል::

በአሰሪዎቻቸው የሚገባቸውን ክፍያ ለተከለከሉ 69 ዜጎች እዛው በሚገኙባቸው አገራት እያሉ ገንዘባቸውን ማግኘታቸውን እና 250 ኢትዮጵያውን ወደአገራቸው ተመልሰው ከቤተ-ሰቦቻቸው ጋር እንዲቀላቀሉ መደረጉንና በ2002 20 ዜጎች በአሰሪዎቻቸው የተወሰዱባቸው ፓስፖርቶች እንዲመለሱላቸው እንደተደረገ ዳይሬክተሩ ለአውራምባ ታይምስ ገልፀዋል::

# «ከሰበር ሰሚ ችሎት ፍትህ እንጠብቃለን»

## ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

በሰናይት ግርማ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ እና የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት መኢአድ፣ በግንቦት 15/ 2002 የተደረገው ምርጫ «መደገም አለበት» በሚል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ መደረጉ ይታወሳል:: ከዚህ በፊት ድርጅቶቹ ባስታወቁት መሰረት ጉደዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት በሐምሌ 1/2002 አቅርበዋል::

የመኢአድ ዋና ጸሐፊ አቶ ማሙሸት አማረ ለዝግጅት ክፍሉ፣ ፓርቲያቸው ለጠ/ ፍርድ ቤት ያቀረበው አቤቱታ «በሚገባ ስላልተመረመረ የሕግ ስህተት አለው:: የሕግ ስህተቱ እልባት እንዲያገኝ ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት አስገብተናል» በማለት ገልጸዋል:: የመድረክ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ ሰኞ ሐምሌ 5/2002 በሚውለው የሰበር ሰሚ ችሎት «ፍትህና ትክክለኛ ውጤት እንጠብቃለን» ሲሉ ለአውራምባ ታይምስ ገልጸዋል::

በተያያዘ ዜና በሐምሌ 11/2002 ወይም በሐምሌ 18/2002 ይደረጋል የተባለው የመድረክ ጠቅላላ ጉባዔ ለሐምሌ 24/2002 መራዘሙን ዶ/ር ነጋሶ አስታውቀዋል::

# የ165 ኢንቨስተሮች ፍቃድ ተሰረዘ

በሰናይት ግርማ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ የክልል ኢንቨስትመንት መ/ቤቶችን ጨምሮ ባለፉት አስር ወራት ድጋፍና ክትትል ተደርጎላቸው ወደሥራ ላልገቡ 165 ኢንቨስተሮች የተሰጠው ፍቃድ መሰረዙን የኤጀንሲው የኮርፖሬት ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጌታሁን ነጋሽ ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ::

ከኤጀንሲው ባገኘነው መረጃ መሰረት፣ ባለፉት አስር ወራት 3959 ኢንቨስተሮች የኢንቨስትመንት ፍቃድ የተሰጣቸው ሲሆን፣ የተመዘገበ ካፒታላቸውም 66 ቢሊዮን ብር መሆኑን ለማወቅ ችለናል:: ፍቃድ ከተሰጣቸው ውስጥ ከህንድ፣ ከቻይናና ከመካከለኛው ምስራቅ አገራት የመጡ ባለኃብቶች እንደሆኑ ዳይሬክተሩ ገልፀዋል:: ኢንቨስተሮቹም በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርና፣ በሪል-ስቴት እና በኮንስትራክሽን እና በሌሎች ዘርፎች ለመሰማራት የኢንቨስትመንት ፍቃድ የተሰጣቸው ናቸው::

የኢንቨስትመንት ፍቃድ ወስደው የቅድመ-ግንባታ ሥራቸውን የጀመሩ 3802 ሲሆኑ፣ በግንባታ ላይ የሚገኙ ሰማንያ ሁለት እንደሚጠጉ አቶ ጌታሁን ተናግረዋል::

የኢንቨስትመንት ፍቃድ የወሰዱ ኢንቨስተሮች፣ ፍቃዳቸውን በወሰዱ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደግንባታ መግባት እንዳለባቸው እና ጊዜው ካለፈ የተሰጣቸው ፍቃድ እንደሚሰረዝ ከዳይሬክተሩ ለመረዳት ችለናል::

# «ዝክረ ቴዎፍሎስ» የሕዝብ ት/ቤት ነገ ይመረቃል

በኤልያስ ገብሩ

ዝክረ ቴዎፍሎስ የሚባል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሙሉ ወጪ የተሰራውና በቤተክርስትያኗ ታሪክ ሁለተኛው ፓትርያርክ በነበሩት እና በደርግ መንግስት በተገደሉት አቡነ ቴዎፍሎስ ስም የተሰየመ የሕዝብ ትምህርት ቤት በነገው ዕለት እንደሚመረቅ የቤተክርስቲያኗ የካቴዴራል ደብር አስተዳዳር መላከ ፀሀይ አባ ሃይለመለኮት ለዝግጅት ክፍላችን ገልጹ::

ጉፋ ማዞሪያ አካባቢ የሚገኘው አዲሱ ት/ቤት፣ ከአፀደ ሕፃናት ጀምሮ እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ የተሟላ የማስተማር አገልግሎት ለመስጠት አቅም እንዳለውና ት/ቤቱን ሰርቶ ለማጠናቀቅም 2,650,500 ብር ገደማ ወጪ መደረጉን አስተዳዳሪ መላከ ፀሀይ አባ ሃይለመለኮት ገልጸዋል::

የት/ቤቱ አጠቃላይ የግንባታ ወጪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን የተሸፈነ ሲሆን በምርቃት ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ሊቃነ ጳጳሳት፣ የመንግስት ባለሥልጣናትና የተለያዩ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እንደሚገኙ አስተዳዳሪው ተናግረዋል::

# የሕፃናትን ጉልበት ብዝበዛን ለማስወገድ በሚል የተዘጋጀ የፋሽን ትርዒት ቀረበ

ፒፐል ኢን ኒድ እና ሚሽን ፎር ኮሚዩኒቲ ዲቨሎፕመንት ከፌዴራል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር «የሕፃናትን ጉልበት ብዝበዛ ለማስቆም እንነሳ» በሚል የፋሽን ትርዒት ከትላንት በስቲያ በሸውሩም ሬስቶራንት አዘጋጅተዋል::

በፕሮግራሙም የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዲኤታ ክብርት ወ/ሮ ዘነቡ ታደሰ እና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች የተገኙ ሲሆን፣ ወ/ሮ ዘነቡም መንግስት እየወሰዳቸው ያሉ እርምጃዎችን እና የዓለም የሥራ ድርጅትን ኮንቬንሽን የፈረሙ አባል አገራት የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን እስከ 2016 ለማስወገድ እየሰሩ መሆኑን እና ኢትዮጵያም እስከ 2014 እቅድ ይዛ እየተንቀሳቀሰች መሆኑን ገልፀዋል::

የፋሽን ትርዒቱ ዓላማም በኢትዮጵያ የባህል አልባሳት ውስጥ ከትምህርት፣ ከቤተሰብ ርቀው በቀን 13 ሰዓታትን በሽመና ሥራ ላይ የሚያገለግሉ ሕፃናት ስለሚሳተፉ ይሄን ለማስወገድ በሕፃናት የተሠሩ ምርቶችን ህብረተሰቡ ባለመግዛት አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ግንዛቤ ለመፍጠር ነው::

በኢንተርናሽናል ኦርጋናይዜሽን ማይግሬሽን የተዘጋጀው፣ «ያልተሰሙ ድምፆች የሕፃናት ዝውውር በኢትዮጵያ» የ15 ደቂቃ ዶክመንታሪ ፊልም የቀረበ ሲሆን የሕፃናት ሕገ-ወጥ ዝውውርን እና ከዚያም የሚደርስባቸውን ጥቃት አሳይቷል::

በዲዛይነር ፍቅርተ አዲስ የተዘጋጁ የባህል አልባሳትን በመጠቀም የፋሽን ትርዒቱን ያቀረቡት አስር ሴት እና አንድ ወንድ ሞዴሎች ነበሩ::

ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ



ቅደስ ፍስሐ

# የስደት ሰልፉ

## ማለቂያው መቼ ይሆን?

የሥራ አጥ ሴቶች፣ እንዲሁም ወንዶች የመጨረሻው አማራጭ «ስደት» እንደሆነ በየእለቱ ጠዋት ጠዋት ወደ ሥራ ለመግባት በምጣደፍበት ሰዓት የኢምግሬሽን ሰልፈኞችን ሳይ የማስተውለው እውነታ ነው:: ሁሉም የራሱ የሆነ ነገር ሰንቆ ነበር ወረፋውን የሚጠብቀው:: እኔ ግን አንድ ጠዋት ጠጋ ብዬ ሁኔታውን ለማየት ተሰለፍኩ::

ወረፋ ለመያዝ ለተደረደሩት ሴቶች አንድ ወጣት ያለመታከት እየሄደ በራሪ ወረቀት ያቀብላል:: ተቀብዬ ተመለከትኩት «ወደ አረብ አገራት በሕጋዊ መንገድ እንልካለን» የሚል ወረቀት ነበር:: ይሄም የሴቶቹን ቀልብ እንዲስብ ሆኗል:: አንዷም ሴት ልክ በመንገድ የተለያዩ የኮሌጆች ለማስታወቂያ እንደሚበትኑት በራሪ ወረቀት ዓይነት አንብባ አልጣለችውም:: ሁሉም ወደቦርሳቸው ከተውታል:: እኔም በእነዚህ ሴቶች ላይ ትኩረት አደረኩ::

ፓስፖርት ሊያወጣ ከተሰበሰበው ሕዝብ መሃል ቢያንስ 90 በመቶ ሴቶች ነበሩ:: ያስገረመኝ ነገር ደግሞ ከተሰበሰቡት ከ90 በመቶዎቹ ሴቶች ውስጥ፣ እንደ እኔ ግምት ቢያንስ 50 ከመቶ በላይ የሚሆኑት ካለመማራቸው ባሻገር አማርኛ መናገር እንኳን የማይችሉ ነበሩ::

ከጐኔ የተቀመጠች አንድ ወጣትን አናገርኳት፤ «ከየት ነው የመጣሽው?» አልኳት:: ፎርም ለመሙላት ስላልቻለች የሚረዳትን ሰው በዓይኗ እያማተረች ትፈልግ ነበር:: «እስቴ» ከሚባል ከተማ እንደሆነ ነገረችኝ:: እዚህ የመጣችው ፓስፖርት ለማውጣት እና እድል ከቀናት ወደ ውጭ ለመሄድ ልትሞክር እንደሆነ ነገረችኝ::

ለምን ስደትን እንደመረጠች ልጠይቃት ብፈልግም መልሷን ቀድሜ ስለማውቀው ለመጠየቅ አልደፈርኩም::

ሁላችንም ውስጥ አንድ ጥያቄ ያጭራል:: ስደትን እንደመፍትሔ ለምን እንወስዳለን? የሚል:: ምን አልባትም ለዚህ በቂ መልስ የሚሆነው በያዝነው ነገር አለመርካት ወይንም የያዝነው ነገር በቂ አለመሆኑ ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብኩ:: ስደት አንዱና አንዱ አማራጭ ነው::

እንዲህ አሰብኩ፣ ከነዚህ ከተሰበሰቡት ሴቶች አንዷ እንግዲህ ከአረብ አገር የመጣች ጐረቤት ትኖራት ይሆናል::

አረብ አገራት ተሰደው «ዛሬ እሞት ይሆን? ነገ እሞት ይሆን?» እያሉ ሰብዓዊ መብታቸው ተገፎ፣ ድብደባን፣ አስገድዶ ደፈራን፣ የጉልበት ሥራን ሁሉ ተቋቁመው ለአገራቸው መብቃት የቻሉ እህቶቻችንን ስናይ ሁላችንም ለመሄድ ያለን ፍላጎት ያይላል::


ነገር ግን ስደት ብዙ መጥፎ ጐኖች አሉት:: ከላይ የዘረዘርኩትን ነገር አልፋ መምጣት ያልቻለች፣ ርሃብ የሚቀጣት፣ ለአሰሪዋና ለጓደኞቹ የወሲብ ባሪያ ሆና ፓስፖርቷ ተነጥቆ ወይም ከፎቅ ተወርውራ በእግር ከወጣችበት አገር በ«ዊልቸር» የምትመለስ እና መሰል አደጋዎች ደርሶባት መሸሽ እና ማምለጥ ከማትችልበት የህሊና ወቀሳ ውስጥም ያለች ሴት ጐረቤትም ትኖረናለች::

ከጎኔ የነበረችውን ልጅ ተመለከትኳት:: ማንበብም ሆነ መፃፍ የማትችል መሆኗን ተገንዝቤያለሁ:: «እንዴት ሆና ይሆን ሰው አገር የምትሰራው?» አልኩ:: ምን አልባትም ሕገ-ወጥ ኤጀንሲዎች እንደ አሸን በፈሉባት አገራችን አንዱ እጅ ላይ ትወድቅ ይሆናል:: ከዚያም የራሷን ሃሳብ መግለፅም ሆነ መተግበር ወደማትችልበት ዓለም ይልኳታል:: እግዚአብሔር ከሷ ጋር እንዲሆን ተመኘሁ፤ እንዲሁም ከሁላችንም ጋር::

እንደሁላችንም ፍላጎት ስደት አንዱ አማራጭ ባይሆን ደስተኞች ነን:: ነገር ግን ከዚያ ውጭ አማራጭ ከሌለ ሕጋዊነት ያላቸውን ኤጀንሲዎች ብንጠቀም ጥሩ ነው እላለሁ:: ሥራ አጥነትን ማጥፋትም ሆነ መቀነስ የምንችለው እኛ ዛሬ ላይ ያለን ወጣቶች ነን:: የስደት ሚዛን የሚያጋድለው ደግሞ በሴቶቻችን ላይ ነው::

መንግስት ሥራ አጥነትን በመቅረፍ እና አንድ ሰው በሰራው ሥራ ልክ ተገቢውን ክፍያ እንዲያገኝ የራሱን አስተዋጽኦ ካላደረገ ስደት አይቆምም፤ በስደት ጅራፍ መገረፍም እንደዚያው::

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com



## ጤ ና ካ ስ

◆ በኤልያስ ገብሩ

# የአካላዊ ውጥረት ሕመም

## «ሪፒቴቲቭ ስትሬን ኢንጁሪ»

ሪቲቴቲቭ ስትሬን ኢንጁሪ [በአካል ክፍል ላይ የሚደርስ ተደጋጋሚ ውጥረት ምክንያት የሚፈጠር ሕመም (አር ኤስ አይ) ይባላል።]

የዚህ ህመም ዋናው መንስዔ በብዙ የሥራ መስኮች የሚታየው ፈጣን የሆነ ተደጋጋሚ እንቅስቃሴ ነው። መረጃዎች እንደሚያስረዱት ከሆነ ብዙውን ጊዜ ሰራተኞች ጤናቸውን ሊጐዳ የሚችል ሥራ እየሰሩ ከመኖር ሌላ ምንም አማራጭ እንደሌላቸው ነው።

በተጨማሪም በጡንቻዎችና በአንጓዎች ላይ ጫና ማብዛት [ከባድ ዕቃዎችን መሸከምና በመሳሰሉት ሁኔታዎች] እንዲሁም ጡንቻዎች የአካል ክፍሎች የሚያደርጉት ጥረት (static efforts) አር ኤስ አይን ሊያስከትል ይችላል። እንዲህ ዓይነቶቹ ድርጊቶች በተለይ አንድ ሰው አመቺ ባልሆነ ሁኔታ ላይ ሆኖ በሚሰራበት ጊዜ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ።

ተመራማሪዎች ለአር ኤስ አይ ህመም በይበልጥ የተጋለጡ ናቸው ብለው ከፈረጇቸው ሙያተኞች መካከል የብረታብረት ባለሙያዎች፣ የባንክ ፀሀፊዎች፣ በመኪና ጋራጅ የሚሰሩ ሰዎች፣ የስልክ ኦፐሬተሮች፣ በገበያ አዳራሽ ውስጥ የሚሰሩ ገንዘብ ተቀባዩች፣ አስተናጋጆች፣ ልብስ ሰፊዎች፣ ፀጉር አስተካካዩች፣ ሹሩባ ሰሪዎች፣ ሽንኮራ አገዳ የሚቆርጡ ሰዎችና የጉልበት ሰራተኞች ይገኙበታል።

አብዛኛዎቹ ሰዎች የአር ኤስ አይ ህመም የሚመጣው ተደጋጋሚ በሆነ ሥራ ምክንያት ብቻ እንደሆነ አድርገው ቢያስቡም ተመራማሪዎች ችግሩ የሚከሰተው በተደጋጋሚ እንቅስቃሴ ብቻ አለመሆኑን ጠበቅ አድርገው ገልፀዋል።

እንደ ህክምና ባለሙያዎች ገለፃም ከሆነ የግለሰቦች ሥራ የተደራጀበት መንገድ ማለትም የሚሰራው ነገር፣ በአስተዳደሩና በሰራተኛው መካከል ያለው ግንኙነት፣ በሥራው አካባቢ ያለው አጠቃላይ መንፈስ፣ የሰራተኛው የተሳትፎ መጠንና የስራው ሂደት ከበሽታው ጋር ጠንካራ ትስስር ካላቸው ነገሮች አንዱ ነው።

በበሽታውና በሥራ አደረጃጀት መካከል ያለውን ዝምድና ጥብቅ እንደሆነ ሲገለፅ የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች አንዱ ደካማ ጐን ሰራተኛው ስራው ከቁጥጥሩ ውጪ እንዲሆን የሚያደረግ አደረጃጀት መፍጠራቸው ሲሆን ይህ ደግሞ ሰራተኛው በአር ኤስ አይ ህመም እንዲያዝ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ቀደም ባሉት አመታት አንዳንድ ሰራኞች ተደጋጋሚ እንቅስቃሴ የሚጠይቅ ስራ ሲያከናውኑ የኖሩ ቢሆንም አር ኤስ አይ ያልያዛቸው አንዱ ምክንያት ስራው የሚደራጅበትና የሚከናወንበት መንገድ ከአር ኤስ አይ ህመም ጋር የቅርብ ትስስር ባለመኖሩ እንደሆነ ይናገራል።


## የበሽታው ምልክቶች

አር ኤስ አይ አንድ የተለየ በሽታ ብቻ ሳይሆን በርከት ያሉ ተዛማጅ በሽታዎችን የሚያመለክት ስያሜ መሆኑ መዘንጋት የለበትም ተብሎ ይገለጻል። በዚህ ሥር የሚካተቱት ሕመሞች በሙሉ በተለይ የላይኛዎቹን የእጅና የእግር ጡንቻዎች፣ ጅማቶች፣ አንጓዎችና ምራኖችን (ligaments) ይጐዳሉ። አር ኤስ አይ በርከት ያሉ በሽታዎችን የሚያመላክት በመሆኑ የተለያዩ ምልክቶች ሊታዩ የሚችሉ ሲሆን አንዳንዴም ምልክቶቹ ግልጽ ላይሆኑም ይችላሉ። በተጨማሪም በበሽታው መንስዔዎችና በምልክቶቹ መካከል ያለው ዝምድና ወዲያው ላይታወቅ ይችላል።

ከበሽታው ዋና ዋና ምልክቶች አንዱ በተጐዳው የአካል ክፍል ላይ [ትከሻ እና / ወይም ክንድ ሊሆን ይችላል] የሚሰማ እንደ ጭነት የሚከብድና ዕረፍት የሚነሳ ስሜት ነው። ይህ ደግሞ እያደገ ይሄድና ፋታ የማይሰጥ ህመም ውርር የሚያደርግ ስሜት ያስከትላል። በተጨማሪም ከቆዳ ሥር ቁጥር [ጥብቅ] ያለ ትንንሽ እብጠቶች ሊወጡ ይችላሉ። አር ኤስ አይ የከፋ ደረጃ ላይ በሚደርስበት ጊዜ እብጠቱና ሕመሙ በጣም ከባድ ስለሚሆን ግለሰቡ ፀጉር እንደማበጠርና ጥርስ እንደመቦረሽ ያሉ ቀላል ተግባሮችን እንኳን ማከናወን ይሳነዋል። አር ኤስ አይ ህክምና ካልተደረገለት የቅርፅ መበላሸትና አካለ ስንኩልነት ሊያስከትል ይችላል።

## አር ኤስ አይን መከላከል

ሥራው ተደጋጋሚ እንቅስቃሴ የሚጠይቅ ከሆነና የአር ኤስ አይ ምልክቶች እየታዩ ከሆነ ወደ ህክምና ማዕከልና ባለሙያ መሄድ ያስፈልጋል። በይበልጥም ችግሩን መርምሮ ሊያገኝና ግለሰቡን



ለመርዳት አስፈላጊ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚችል የአጥንት ስፔሻሊስቶችን ማማከር ወሳኝ ነው። የበሽታው የመጀመሪያ ምልክቶች በሚታዩበት ወቅት ለአር ኤስ አይ ተገቢውን ትኩረት ከሰጡ ከበሽታው የመዳን ዕድል በጣም የተሻለ ይሆናል።

ለሰው አር ኤስ አይን ለመዋጋትና ለመከላከል በጣም ጠቃሚ የሆነው መንገድ ለኤርጐኖሚክስ [ሰዎችና መሣሪያዎች እጅግ ምቹ በሆነና ለጉዳት በማያጋልጥ መንገድ ተጣጥመው መስራት የሚያስችላቸውን ንድፍና ቅርጽ የሚያመጣ ተግባራዊ ሳይንስ] ትኩረት መስጠት እንደሆነ በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች ጠቁመዋል።

ስለዚህ ኤርጐኖሚክስ የሥራ ቦታ ከሰው ጋር እንዲሁም ሰው ከሥራው ቦታ ጋር መጣጣማቸውን የሚከታተል የእውቀት ዘርፍ ሲሆን ይሁን እንጂ ይህ ጥበብ የአንድን የሥራ መገልገያ ዕቃ በማሻሻል ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አለመሆኑ ይገለጻል። እንዲሁም ይሄ የሰራተኛውን አእምሯዊና ስሜታዊ ፍላጐቶችን ግምት ውስጥ ማስገባትን ይጨምራል። ይህን ግብ ለመምታት ኤርጐኖሚክስ «ከሁሉም መስኮች የሚገኘውን ዳታ፣ መረጃና እውቀት ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚጠቅም ከመሆኑም በላይ ስለ ሰውና ስለስራው አንድ አዲስና የተሟላ እውቀት ላይ ለመድረስ ይጥራል» ሲሉ የዘርፈ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ።

ሆኖም አብዛኞቹ ሰራተኞች ስራ ቦታቸውን በኤርጐኖሚክስ የመለወጥ ሥልጣን ላይኖራቸው ይችላል። ባደጉ አገሮች ላይ በተደረገ ጥናት መሠረት ግን ሰራተኞቹ በኤርጐኖሚክስ ማሻሻያዎች እንዲሳተፉ የሚያበረታታው አንዱ ነገር የሰራተኞቹን አስተያየት ግምት ውስጥ ማስገባት እንደሆነ ተገልፆል።

እንዲሁም ሰራተኛው የሚሰራበትን ቦታና ሁኔታ እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ሐሳብ እንዲሰጥ ይጋብዟል። በተጨማሪም እንዲህ ዓይነቱ አሰሪ ከሰራተኞቹና ከአስተዳደሩ የተውጣጣ አንድ የአር ኤስ አይ ኮሚቴ እንዲቋቋም ያደርጋል። ይህ ኮሚቴ በሥራ ቦታው ለጉዳት የሚያጋልጡ ምቹ ሁኔታ ስለመኖሩ የማያቋርጥ ክትትል ያደርጋል። ይህም የአር ኤስ አይ ህመም መንስዔዎችን ያስወግዳል።

በሽታውን መከላከል የሚቻልበትን መንገድ ያመቻቻል። እንዲሁም በተቋሙ ውስጥ አር ኤስ አይን በመቆጣጠር ብሎም ጨርሶ በማስወገድ ረገድ አሰሪውና ሰራተኞቹ ያለባቸውን ኃላፊነት በመግለጽ ያስቀምጣል።

ህመሙ እንዳይከሰት መወገድ ካለባቸው ነገሮች መካከል፤ ከባድ ነገሮችን ተሸክሞ መቆየት፣ በአንጓዎች ላይ ከባድ ጫና መፍጠር፣ ምቹ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ እና ክንድን ከደረት በላይ ከፍ አድርጐ ለረዥም ጊዜ መስራት ይጠቀሳሉ። እንዲሁም መደረግ ካለባቸው ነገሮች ውስጥ ቀጣይ ሥራዎች በሚከናወኑበት ጊዜ እጆችን እያቀያየሩ በቀን ውስጥ የተለያዩ ስራዎችን መስራት ተገቢ እንደሆነ ይመከራል።

## የመፍትሔ እርምጃዎች

አር ኤስ አይን ለመከላከል የሚረዱ ነገሮች ከላይ ቢገለጹም የሚወሰዱ እርምጃዎች ከቤት ይጀምራሉ። ከአንቅልፍ ከተነሱ በኋላ የቀን ውሎ ተግባር እንቅስቃሴ ከመጀመር በፊት በመንጠራራት ጡንቻዎች እንዲፍታቱ ማድረግ ወሳኝ ነው። እንቅስቃሴው በቀን ውስጥ አልፎ አልፎ ቢደጋገም ጥሩ ሲሆን አንዳንዴ ማድረግ ግን የአጥንቶችንና የጡንቻዎችን ጤንነት ለመጠበቅ ይረዳል። ይህ የደም ዝውውርን የሚያፋጥን ከመሆኑም በላይ ጡንቻዎች ሥራቸውን ማከናወን እንዲችሉ የሚረዳቸውን የኦክሲጅን መጠን ይጨምራል። በተጨማሪም ቅዝቃዜ ሲኖርና በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ከመሳተፍ በፊት ይህን አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ይበልጥ አስፈላጊ ነው። በብዛት ጡንቻዎችን የሚያጠናክር የአካል እንቅስቃሴ ማድረግ ይመከራል። [ጠንካራ ጡንቻዎች በሥራ ቦታ የሚከናወኑ ነገሮችን በብቃት እንዲሰሩ ይረዳሉ]

በቤት ውስጥ ከሚወሰዱ እርምጃዎች በተጨማሪ በሥራ ቦታም የመከላከያ ፕሮግራም መኖር አለበት። አሰሪው በመካከሉ ዕረፍት የሚሰጥና የሥራ ለውጥ የሚፈጥር የሥራ ፕሮግራም በማውጣት እንዲሁም የተለያዩትን ሥራዎች የተለያዩ ሰራተኞችን በየተራ እንዲሰሩ በማድረግ በሰራተኞች መካከል የአር ኤስ አይ ህመም ችግር እንዳይኖር ሊከላከል ይችላል።

ኤር ኤስ አይን መከላከል የሚቻልበት ሌላው መንገድ ለሰራተኛው ትክክለኛውን ዓይነት መሳሪያ በማቅረብ እንደሆነም ይገልፃል።

## ቀይ መስቀል በ75ኛ ዓመቱ

**የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር 75ኛ የምስረታ በዓሉን ምክንያት በማድረግ በጎ ፍቃደኛ የሆኑ ግለሰቦች፣ ነባር የማሕበሩ አባላት እና ድጋፍ ሰጪ አካላት ከጎኑ ስመሆን እንዲወስኑ ጥሪ አስተላልፏል። ዝግጅት ክፍላችንም የቀይ መስቀል ዓለም አቀፍ ማሕበር በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመሰረተበትን ታሪካዊ አመጣጥና እንዲሁም መሠረታዊ መርሆችን ለአንባቢያን ግንዛቤ ይረዳል በሚል እንዲህ አቅርበነዋል።**

የቀይ መስቀል ማህበር አለም አቀፍ ተቋም ሲሆን መስራቹም ስዊዘርላንዳዊው ጄን ሄነሪ ዶናንት ይባላል። ይህ ተቋም በሚሰጠው ሰብዓዊ አገግሎት የተነሳ በብዙ ሚሊዮን የአለም ህዝቦች ዘንድ የተከበረ ነው። የተቋሙ ዋና ዓላማ በጦርነት ጊዜም ሆነ በሰላም ወቅት ተጐጂ የሆኑ ሰዎችን መንከባከብ እንደሆነ ይገለፃል።

የቀይ መስቀል ድርጅትን ለማቋቋም ሀሳብ የተፀነሰው ከተቋሙ መመስረት አምስት አመታት ቀደም ብሎ ነበር። ይህም የሆነው ከላይ በተገለፀው ግለሰብ ነው። እ.ኤ.አ በሰኔ 1959 ጄን ሄናሪ ዶናንት በሰሜን ጣሊያን በኩል የፈረንሳይ፣ የጣሊያንና የኦስትሪያ ወታደሮች እየተዋጉ ወደነበረበት ሶልፈሪም ወደተባለ የጦር ሜዳ ይጓዛል። በዚህ ጦር ሜዳም እ.ኤ.አ በሰኔ 24 1959 ለ15 ሰዓታት የቆየ አሰቃቂ ጦርነት ይደረግና በወታደሮች በኩል ከፍተኛ ጉዳይ ሲደርስ በአይኑ ይመለከታል። በጦር አውድማው ወደ 40 ሺህ የሚጠጉ ሰዎች ለህልፈተ ህይወት ተዳርገዋል። በቀጣዩ ቀንም ፈረንሳዩች ቁስለኞቻቸውን ለማከም ጥረት ቢያደርጉም የቁስለኞች ቁጥር በጣም ከፍተኛ በመሆኑ አገልግሎት አሰጣጡ በቂ ሳይሆን ይቀራል።

ዶናንት ይህንን በመመልከት በአቅራቢያው ያሉ ሴቶችንና ልጃገረዶችን በማሰባሰብ በሚጓዝበት አካባቢ ያገኛቸውን ቁስለኞች በህክምና የመርዳት ተግባር መፈፀሙን ቀጠለ። አገልግሎቱን የሚሰጡት ጣሊያኖች ሲሆኑ ቁስለኞቹ ደግሞ የእንደጠላት የሚፈሯቸው የሌላ አገር ሰዎች ናቸው። ሆኖም ዶናንት በተደጋጋሚ በጣሊያንኛ «Thtti fratelli» «ሁሉም ወንድሞች ናቸው» በማለት ደሃ የሆኑትን የአከባቢውን ሰዎች በማስተባበር ርህራሄ በተሞላበት ሁኔታ፣ በትዕግስትና በፍቅር የጦርነቱ ሰለባዎቹን እንዲያገለግሉ መከረ።

የዶናንት ደግነት በሳማሪተን ሶልፈሪኖ ታዋቂ እንዲሆን ረዳው። ነገር ግን ከጥረቱ ባሻገር በሺዎች የሚቆጠሩ ወንዶች ከጦርነቱን ተጉድተው ቢተርፉም የመጀመሪያው የህክምና ዕርዳታ ባለማግኘታቸው ምክንያት ሲሞቱ ዶናንት ተመለከተ። በአይኑም አይቶ ምስክር የሚሆንለትን ይህን አሰቃቂ ዕይታ ለዶናንት በአእምሮው ውስጥ የመጨረሻ መነቃቃትን ፈጠረለት።

የ«ሶልፈሪኖ ማስታወሻ» በሚል እ.ኤ.አ በህዳር 8 1862 ባሳተመው መፅሀፉ ውስጥ ሁለት ጥናታዊ ፅሁፎች ተካትተውበታል። አንደኛው ወታደሮች በጦርነት ጊዜ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚል ሲሆን ሁለተኛው በጦር ሜዳ ላይ የሚጎዱ ቁስለኞች እና ወታደሮችን የሚያክም ገለልተኛ አካል እንዲኖር የሚያሳስብ ነው።

መጽሐፋም በዘመኑ የነበሩትን ታላላቅ ግለሰቦች ቀልብ በመግዛት ስኬታማ ሆነ። የመፅሐፋም ፅንሰ-ሐሳብ መንግስታት ምግባረ ሰናይ ለሆኑ ማህበራት ዕወቅና እንዲሰጡ በሚወተውት በድን አባላት ዘንድ ለመንሸራሸር በቃ። የኮሚቴው ፀሐፊ ከነበረው ጂን ሔንሪ ዱናንት በተጨማሪ ጉስታቭ ሞይኔር የተባለ ጠበቃ፣ የስዊዝ ጦር ጠቅላይ አዛዥ የነበረው ጀነራል ጊላወውም ሔንሪ ዱፎር እንዲሁም ዶ/ር ሉዊስ አፒያና ዶ/ር ቴዎዶር ሞውኒር የተሰኙ ሁለት የሕክምና ባለሙያዎች የኮሚቴው አባላት ነበሩ።

በአነዚህ አመስት ሰዎች የተዋቀረው ኮሚቴ የመጀመሪያ ዓላማ የነበረው በየሐገሩ የሚገኙ ማህበራትን ግንኙነት የሚያጠናክር ዓለም አቀፍ ድርጅት መመስረት በመሆኑ የስዊዝ መንግስት «ዓለም ዓቀፍ የቁስለኞች መርጃ ኮሚቴ» በኋላም ስያሜው ወደ «ዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ማህበር» ነት የተለወጠው የተራድኦ ድርጅት እንዲያቋቁም ሐሳብ አቅርበዋል።

የቀይ መስቀል ማሕበር ጥንስስ የተጣለው የጦርነትን አስከፊ ገጽታ በማየት እንደመሆኑ መጠን የመጀመሪያ መሪ ቃሉ «Charity in the clashes of Arms» ወይም «በጦርነቶች መሐል እርዳታ» የሚል ነበር።

ማሕበሩ የጋበዛቸው ከ16 አገራት የመጡ ልዑካን በተገኙበት በወርሐ ጥቅምት 1863 ዓ.ም ጄኔቫ ላይ 10 ድንጋጌዎችን በማፅደቅ የቀይ መስቀልን መስራች ቻርተር ዕውን አድርጓል።

ጂን ሔንሪ ዱናንት

የቀይ መስቀል ማህበር መስሪች የሆነው ጂን ሔንሪ ዱናንት የተወለደው ግንቦት 8 ቀን 1828 ሲሆን ማሕበሩን እንዲያቋቁም ዋና ምክንያት የሆነው በሰኔ 1859 በሶልፌሪኖ ጦርነት የተመለከተው ዘግናኝ ዕልቂት ነው። በጦርነቱ ላይ ያስተዋለው ዘግናኝ ክስተት ከአዕምሮው ሊጠፋ ያልቻለው ሔንሪ ዱናንት በ1862 ዓ.ም «የሶልፌሪኖ ማስታወሻ» በማል ርዕስ ባሳተመው መፅሐፍ ለጀኔቫ ኮንቬንሽንና ለቀይ መስቀል ምስረታ መሠረት ጥሏል።

በንግድ ስራ ይተዳደር የነበረው ሔንሪ ስራውን ችላ በማለቱ የተነሳ ለኪሳራ በመዳረጉ ከቀይመስቀል ማህበር በመልቀቅ በ1868 ለስደት ተዳረገ። ለ15 ዓመታት ዱካውን አጥፍቶ የቆየው ሔንሪ በ1890 በአገሪቱ ገጠራማ ስፍራ እንደሚገኝ አንድ ጋዜጠኛ ይፋ አደረገ ከዛም በ1901 ዓ.ም ከፍሬድሪክ ፔሲ ጋር በጋራ የመጀመያውን የኖቤል ሽልማት ለመሸለም በቃ።

ከዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል ማሕበር በተጨማሪ የዓለም ወጣት ወንዶች ክርስቲያን ማህበር መስራች የሆነው ጂን ሔንሪ ዱናንት በ82 ዓመቱ ጥቅምት 30 ቀን 1910 ዓ.ም እኤአ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

የቀይ መስቀል ዓርማ

አሁን በጥቅም ላይ የሚገኘው ዓርማ በዓለም አቀፍ ደረጃ የማሕበሩን ገለልተኝነት የሚያረጋግጥ፣ የትኛውንም ሐይማኖት የማይወክል፣ ለየትኛውም ርዕዮት ጥብቅና ያልቆመና ከፖለቲካ አመለካከት የፀዳ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

«ቀይ መስቀል» የሚለውን ስያሜ ማህበሩ ያገኘው በነጭ መደብ ላይ ከሰፈረው የቀይ መስቀል ዓርማው ሲሆን ይህ ዓርማ የስዊዝ ባንዲራ ግልባጭ በመሆኑ በስዊዘርላንዳዊያን ዘንድ «የእኔነት» ስሜት ፈጥሯል ምንም እንኳን አብዛኞቹ ማሕበራት የቀይ መስቀል ዓርማ በኖራቸውም በሙስሊሙ ዓለም ያሉት አቻ ማሕበራት በቀይ መስቀል ፋንታ ቀይ ጨረቃን በዓርማነት ይጠቀማሉ። የቀይ ጨረቃ ምልክት ለመጀመሪያ ጊዜ ግልጋሎት ላይ የዋለው በ1876ዓ.ም በኦቶማንቱርክና በሩሲያ መካከል በተካሐደው ጦርነት ወቅት ሲሆን የቀይ መስቀል ዓርማን እንደ ክርስትና ምልክትነት የቆጠሩት ቱርኮች በእስልምና ውስጥ እንደቅዱስ በምትቆጠረው ጨረቃ ለወጡት።

በ1923 ዓ.ም ደግሞ ኢራን የቀይ አንበሳ እና ፀሐይ ዓርማን መጠቀም ጀምራ የነበረ ቢሆንም ዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማህበር ተጨማሪ ሶስተኛ ዓርማ መኖሩ አስፈላጊ መስሎ ስላልታየው ዓርማውን አግዶታል።

### የቀይ መስቀል መሠረታዊ መርሆዎች

#### ሰብዓዊነት

ይህ መርህ ማህበሩ ከተመሠረተበት የሰው ልጆችን ስቃይ የማቅለል ዓላማ ሳይነጣጠል የሚሔድ ሲሆን በሕዝቦች መሐል የጋራ መግባባትን መፍጠር፣ ትብብርና ዘላቂ ሰላም ማምጣት ዋንኛ መገለጫዎቹ ናቸው።

ያለአድልዎ መስራት - የቀይ መስቀል ማሕበር ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች እርዳታ በሚሰጥበት ወቅት ዜግነትን፣ ሐይኖትን፣ ጾታንና የቆዳ ቀለምን መሠረት የማያደርግ ሲሆን ጉዳታቸውና የስቃይ መጠናቸው ከፍተኛ ለሆኑት ብቻ ቅድሚያ ይሰጣል።

#### ገለልተኝነት

በሁሉም ወገኖች ዘንድ ተዓማኒነትን ለማትረፍ ሲል የቀይ መስቀል ማሕበር የጐሣ፣ የሐይማኖት አሊያም የፖለቲካ ግኝቶች በሚቀሰቀሱ ጊዜ አንድን ወገን ደግፎ የሌላውን ተፃርሮ አይቆምም።

#### ጥገኛ አለመሆን

የቀይ መስቀል ማሕበር ከማንኛውም አካል ጥገኝነት ነፃ ሲሆን በየሐገሩ የሚገኙትም ማሕበራት ለየሐገራቱ ሕጐች ከመገዛታቸው ውጪ ነፃነታቸውን ጠብቀው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል።

#### በጐ ፈቃደኝነት

የቀይ መስቀልን ስራ ከለሎች ማሕበራት ልዩ የሚያደርገው ምንም ዓይነት ትርፍን ለማግኘት ሳይሆን እንዲሁ ከራስ ተነሳሽነት ና ለሌሎች ቅን ከማሰብ የመነጨ መሆኑ ነው።

#### አንድነት

በአገር ውስጥ ያለው አንድ የቀይ መስቀል ማህበር ቅርንጫፍ አንድ ብቻ ቢሆን እንኳን አባላቶቹ እየተዘዋወሩ በመላው አገሪቱ ያሉትን የስቃይ ሰለባዎች እንዲያግዙ ይጠበቅባቸዋል።

#### ዓለም አቀፋዊነት

የቀይ መስቀል ማህበር ዓለም ዓቀፍ ተቋም እንደመሆኑ መጠን ሁሉም ማሕበራት እኩል መብት እና ግዴታዎችን ይጋራሉ፤ እርስ በርሳቸውም ይረዳዳሉ።

ስለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ተጠየቅ

በሱራፌል ግርማ

# የሸራተን ማስፋፊያ ፕሮጀክትና ውዝግቡ



ከ1996 ዓ.ም ወዲህ ሊከናወን ታቅዶ በተለያዩ ምክንያቶች የዘገየው የሸራተን ማስፋፊያ ፕሮጀክት ከዚህ ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚሆን መገለፁን ተከትሎ የማስፋፊያ ሥራው ከሚያካልላቸው አካባቢዎች አንዱ በሆነው አሮጌው ቄራ አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች ቅሬታቸውን ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ::

በቦታ ተመን አሰራር ላይ እና አሁን ካሉበት ቦታ ሲነሱ በተለዋጭነት የሚሰጣቸውን ቦታ በተመለከተ ቅሬታ ያቀረቡት ነዋሪዎቹ፣ ለሸራተን ማስፋፊያነት እንደሚፈለግ በተገለፀላቸው ወቅት ከቀያቸው ሲነሱ በቂ ካሳና ከከተማ ያልራቀ ቦታ እንደሚሰጣቸው ከመንግስት ቃል ተገብቶላቸው የነበረ ቢሆንም፣ አሁን ግን በአተማመን ሂደቱ ላይ ወጥነት ካለመኖሩ በተጨማሪ በተለዋጭነት የሚሰጣቸው ቦታ በትክክል የእነሱ ስለመሆኑ ሕጋዊ ማረጋገጫ ሰነድ ሊያገኙ አለመቻላቸውን ይናገራሉ:: በሚተመንላቸው ገንዘብ እንዲሰሩት የሚጠበቅባቸውን «ደረጃውን የጠበቀ» ቤት ሊገነቡ ቀርቶ ገንዘቡ ለአጥር እንኳን እንደማይበቃ ነዋሪዎቹ ጨምረው ይገልፃሉ::

በአካባቢው ላይ መኖር ከጀመሩ 50 ዓመታትን ያስቆጠሩት ወ/ሮ ስለሁኔታው ሲገልጹ «40 ሺህ ብር ተተምኖልኛል ነገር ግን በዚች ገንዘብ ምን እሰራባታለሁ? ከዚህ በፊት ሰብስበው ሲነግሩን ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ እንደሆነ አድርገው ነው:: ፍላጐታችን ምን እንደሆነ ጠይቀው ፍላጐታችን ገንዘብ ሳይሆን ቤት መሆኑን ነግረናቸው ነበር:: ባለፈው ወስደው ያሳዩን ቦታ ግን በአራዳ ክፍለ ከተማና በቂርቆስ ክ/ከተማ ፕሮጀክቱ የሚያቅፋቸው ቦታዎች ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ይሆናል የተባለ ነው፤ ይህም ሆኖ ግን እስካሁን ተሸንሽኖ ያልተሰጠንን መሬት በቦሌ አያት በሳሚትና በሲኤምሲ አካባቢ ወስደው ሲያሳዩን ዝም ብለው ይሄ ነው የናንተ ቦታ ከማለት ውጪተጨባጭ የተዘጋጀልን ነገር የለም::» በማለት ያስረዳሉ:: ነዋሪዋ አክለውም «እኛ ልማት አንጠላምና እንሄዳለን፣ ነገር ግን የምንሄድበት ቦታ የተሟላ ማሕበራዊ አገልግሎቶችና መሠረተ-ልማት የለውም፤ ከድህነታችን፣ ከመሐይምነታችንና ከጭቁንነታችን የተነሳ ንቀውናል::» በማለት ብሶታቸውን ያሰማሉ::

በአራዳ ክ/ከተማ እየተሰራ ያለው የቦታ ግምት ትክክል አለመሆኑን የሚናገረው ስሙ እንዲጠቀስ ያልፈለገ ወጣት በ195 ካሬ ሜትር ላይ ላረፈው ቦታቸው የተተመነው 218 ሺህ ብር እጅግ አነስተኛ መሆኑን በመግለጽ «በትክክል የሚገባንን ያክል እየገመቱ አይደለም፤ 60ም ሆነ 70 ካሬ ሜትር ይዞታ ያላቸው የሚሰጣቸው የ90 ካሬ ሜትር ግምት ነው ተብሏል:: ከ90 በላይ ደግሞ የሆኑት የሚሰጣቸው ባላቸው መሠረት ነው የሚል ነው፤ ሆኖም ግን በዚህ ስሌት ሲሰራ በትክክል የተገመተለት ከስንት አንድ ነው::» ይላል::

እኛም የነዋሪዎቹን ቅሬታ አስመልክቶ ስለ ገንዘቡ መጠን ማነስ፣ ክፍያው በካሬ ሲሰላ ስንት እንደሆነ እንዲሁም ለነዋሪዎቹ በተጨባጭ የተዘጋጀ ምትክ ቦታ ስለመኖሩ ጥያቄ ያቀረብንላቸው በአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማት ባንክ እና ከተማ ማደስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ አንተነህ መስፍን፣ ለካሳው ገንዘብ ማነስ ዋናው ምክንያት

**«40 ሺህ ብር ተተምኖልኛል ነገር ግን በዚች ገንዘብ ምን እሰራባታለሁ? ከዚህ በፊት ሰብስበው ሲነግሩን ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ እንደሆነ አድርገው ነው:: ፍላጐታችን ምን እንደሆነ ጠይቀው ፍላጐታችን ገንዘብ ሳይሆን ቤት መሆኑን ነግረናቸው ነበር:: እስካሁን ተሸንሽኖ ያልተሰጠንን መሬት በቦሌ አያት በሳሚትና በሲኤምሲ አካባቢ ወስደው ሲያሳዩን ዝም ብለው ይሄ ነው የናንተ ቦታ ከማለት ውጪ በተጨባጭ የተዘጋጀልን ነገር የለም::»**

ቤቶቹ ያሉበት ሁኔታ መሆኑን ገልጸው «ክፍያው የሚሰላው በካሬ ሜትር ብቻ ሳይሆን ቤቱ ካለበት ይዞታ አንፃርና ከምን እንደተሰራ በመነሳት ነው፤ እንዲሁም ምትክ ቦታው እየተሸነሸነ ነው» የሚል ምላሽ የሰጡ ቢሆንም ነዋሪዎቹ ግን በአንፃሩ ስለ መሬት ሽንሽናው የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ይናገራሉ::

## ተጨባጭ ቦታ ሳይኖር ቤት መስሪያ?

በሸራተን ማስፋፊያ መርሐ-ግብር የተነሳ አካባቢውን ለቀው «ወደተዘጋጀላቸው» ቦታ በቅርብ ቀናት ውስጥ እንደሚሄዱ የተነገራቸው ነዋሪዎች ቀጣዩን የመኖሪያ ቦታቻውን ሳይረከቡ በግራ መጋባት ውስጥ ባሉበት ሁኔታ ሰሞኑን አራዳ ክ/ከተማ ለግል ባለይዞታዎች የተመነላቸውን ገንዘብ እንዲወስዱ እያደረገ ነው፤ ይሄ የክ/ከተማው ድረጊት «ቦታ ሣይኖር ቤት መስሪያ ምን ያደርጋል?» የሚል ጥያቄን የሚያጭር ሲሆን ከነዋሪዎቹ ውስጥ ጥቂቶች በክ/ከተማው የተተመነላቸውን ገንዘብ ሲወስዱ አብዛኞቹ ግን ገንዘቡን ከመቀበል ተቆጥበዋል::

በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን ከሰጡ ነዋሪዎች መካከል አንዱ የሆነው መስፍን ተረፈ ገንዘብ መሰጠት መጀመሩ በራሱ ሕዝቡ ውስጥ ጭንቀት መፍጠሩን ይናገራል:: ለዚህም እንደማሳያ የሚያስቀምጠው ብዙ ሰዎች የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎቻቸውን መሸጥ መጀመራቸውን ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ገንዘብ እንዲወስዱ የተደረጉት ማንበብ የማይችሉ ሰዎች መሆናቸውን የሚናገረው መስፍን «... ነገር ግን ከወሰዱ በኋላ ምንም እንደማይጠቅማቸው ሲገነዘቡ ለመመለስ የፈለጉ አሉ፤ እንዲሁም 'ከቤቴ አልወጣም እንደፈለጉ ያድርጉኝ' እያሉ ናቸው::... ሌሎች ደግሞ እንደማይቀበሉ አስታውቀዋል» ሲል ይገልፃል::

«ክ/ከተማው የሚሰራው ብዙ ነው» የሚለው መስፍን «'ብሩን ተቀብላችሁ ካነሳችሁ ትከራከራላችሁ' የሚል ነገር አለ:: ሄደውም በእርግጥ ያስጨመሩ ሰዎች አሉ:: አንድ ሰው ሔዶ 'ጨምሩ' ሲላቸው ከጨመሩ መጀመሪያውኑ አሰራሩ ትክክል አልነበረም፤ የቀረ ገንዘብ አለ ማለት ነው» ሲል ይናገራል:: ነገር ግን የመስፍንን አስተያየት ውድቅ የሚያደርጉት አቶ አንተነህ፣ እስካሁን ድረስ ቅሬታ አቅርበው ጭማሪ የተደረገላቸው አንዲት ግለሰብ ብቻ መሆናቸውንና የጭማሪው ገንዘብ መጠንም 4ሺህ ብር ብቻ መሆኑን በማስታወቅ ያስተባብላሉ::

እየተሰጠ ያለው የገንዘብ መጠን አነስተኛ በመሆኑ ማስተካከያ እንዲደረግ ለክ/ከተማው በገለፁበት ወቅት ያገኙት ምላሽ ከባንክ የሚበደሩበት ሁኔታ እንደሚመቻች ቃል የሚገባ ቢሆንም ነገሩ ያልተዋጠለት መስፍን፣ ከባንክ መበደር ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን «አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በጡረታ የሚተዳደር ችግረኛ በመሆኑ የተበደረውን መክፈል ስለማይችል የሚሰራው ቤት በሐራጅ ይሸጣል ስለዚህ መጨረሻው ጨለማ ነው» በማለት አብራርቶ «ታዲያ ይሄንን ካሳ ከሚሉት ጉዳት ቢሉት አይሻልም?» ሲል ይጠይቃል::

አንድም ቤት የመስሪያ ቦታ ስላልተሰጣቸው፣ ሁለትም በክ/ከተማው የተተመነው የቦታ ግምት አነስተኛ በመሆኑ የተነሳ ገንዘቡን ለመቀበል ካልፈቀዱት መካከል አንዷ የሆኑት አዛውንት «መሐይምነታችንን ተጠቅመው ሊያሞኙን ነው የሚፈልጉት:: የት ቦታ ወስደው ሊያፈሱን እንደሆነ አላውቅም:: ቦታ እስካልተረከብኩ ድረስ አልፈርምም፣ አልቀበልምም» የሚሉ ሲሆን አንድ ወጣት ደግሞ በበኩሉ በገንዘብ አሰጣጡ ዙሪያ ያለውን ስጋት «መሬት ሳይሰጥ ገንዘብ ቅድሚያ መስጠት ሌላ ትልቅ ችግር ይፈጥራል፤ ገንዘቡ ሲያልቅ ሰዉ ወደ ጐዳና ነው የሚወጣው» በማለት ከገለፀ በኋላ የሚሰጠው የገንዘብ መጠን የቤተሰብ አባላት ቁጥርን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን እንደሚገባ ያስገነዝባል::

## «ያልመረጠንንም ሕዝብ እናገለግላለን»

በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ስሌት መሠረት የዘንድሮውን ምርጫ አሸናፊ የሆነው ኢሕአዴግ ከውጤቱ መገለፅ በኋላ በጠራው ሰልፍ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የግንባሩ ሊቀመንበር አቶ መለስ ዜናዊ ፓርቲያቸውን የመረጠውን የሕብረተሰብ ክፍል አመስግነው ያልመረጣቸውን ደግሞ «በሥራ እንክሳለን» ማለታቸው የሚታወስ ነው:: አቶ መለስ ከሚኖሩበት ቤተ-መንግስት ፊት ለፊት ያሉት የአሮጌው ቄራ ነዋሪዎችም የተጋፈጡትን ችግር ከአቶ መለስ ንግግር ጋር በማያያዝ የየራሳቸውን አስተያየት በመስጠት ላይ ይገኛሉ::

«መለስ፣ 'እስካሁን አልሰራንም ከአሁን በኋላ እንሰራለን' ብሎ ቃል ገብቶ ሳለ የበታች ባለስልጣኖች በክረምት አውጥተው ሊጥሉን ነው» የሚሉት የዕድሜ ባለፀጋ ልማት አዋኪ አለመሆናቸውን፣ ነገር ግን ልማቱ ሲካሄድ ነዋሪውንም ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባሉ:: የዕድሜ ባለፀጋዋ ከተተመነላቸው አነስተኛ ግምትና ተጨባጭ የሆነ ቦታ ሊያገኙ ካለመቻላቸው በተጨማሪ በክረምት እንዲወጡ መደረጋቸው እጅግ እንዳሳዘናቸው በመግለጽ «እንደዚህ ከሚበድሉን በትራክተር ቢጭኑብን ይሻላል፣ ወገን በወገኑ ላይ እንዴት እንዲህ ይከፋል? ፋሺስት ጣልያን እንኳን እንዲህ አልከፋብንም» ሲሉ ያማርራሉ::

ስሙ እንዲጠቀስ ያልፈለገ ወጣት ደግሞ በበኩሉ «መንግስት እንዳደረገላቸው እና ከተማዋ መልማቷን የሚናገሩ ሰዎች አሉ... እርግጥ ለጥቂቶች አድርጐ ሊሆን ይችላል ግን የተቀሩት በመሉ ጨለማ ውስጥ ናቸው፤ አሁን እየተፈጠረ ያለውን የሐብታም ከተማ፣ የደሃ ከተማ የሚል ነገር አጥፍቶ ችግር ውስጥ ላሉት ቆንጆ ቤቶችን ሰርቶ ቢያስረክብ ነው የሚመሰገነው» የሚል ሀሳብ ይሰነዝራል::

በአራዳ ክ/ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት አሰራር እጅጉን መማረራቸውን የሚገልፁት ነዋሪዎች የክ/ከተማው ኃላፊዎች የሕዝቡን ሮሮ ላለመስማት «ጆሮ ዳባ ልበስ» ማለታቸውን ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት እንዲያወቁ እንደሚፈልጉ ይናገራሉ::

## የፖሊስና የቀበሌው ሕገ-ወጥ ድርጊት


አካባቢው ለሸራተን ማስፋፊያነት እንደሚያስፈልግ በተገለፀበት ወቅት ነዋሪዎች እነሱን ወክሎ በጉዳዩ ላይ የሚሰራ ኮሚቴ መርጠው የነበረ ቢሆንም ኮሚቴው ከ1996 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ ለስድስት ዓመታት ምንም ዓይነት ተጨባጭ ውጤት አለማምጣቱን እና ሥራውን በአግባቡ አለመስራቱን በመግለጽ፣ የአባላቱን አድራሻ እንደማያውቁ የሚናገሩት ነዋሪዎች ሐሙስ ሐምሌ 1 ቀን 2002 ዓ.ም በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 15/16 ጽ/ቤት አዳራሽ ውስጥ ባደረጉት ስብሰባ አዲስ ኮሚቴ አዋቅረዋል::

እኛም በስፍራው በመገኘት ዘገባችንን በምናጠናቅርበት ወቅት ካገኘናቸው ወደ አዳራሹ እንዳይገቡ ከተከለከሉ ነዋሪዎች መረጃ ማሰባሰባችንን ከወንጀል የቆጠሩት የቀበሌ 15/16 አመራር የሆኑት አቶ አጽብኻ ገ/መድሕን፣ የቀበሌ15/16 ኮሚኒቲ ፖሊስ ኦፊሰር ኮንስታብል አህመድ ዓሊ፣ እንዲሁም ጉዳዩ በምን ዓይነት መልኩ እንደሚመለከተው ግልጽ ያልሆነልን በዚያው ቀበሌ የወጣት ሊግ አመራር የሆነው ኤፍሬም ለማ ከቦታው ዞር እንድንል ጠይቀውን ነበር:: ሆኖም ለሕብረተሰቡ ጠቃሚ መረጃ መሰብሰብ ሕገ-መንግስታዊ መብታችን መሆኑን አንቀጽ ጠቅሰን ለማስረዳት ጥረት ብናደርግም የተጠቀሰላቸውን አንቀጽ እንኳን ከመጤፍ ሳይቆጥሩት፣ በተለይም ኮንስታብል አህመድ እና አቶ አጽብኻ ከፍተኛ ወከባና እንግልት አድርሰውብን ከቀበሌው ቅጥር ግቢ እንድንወጣ ተደርገናል:: ይህ ሥነ-ምግባር የጎደለው ድርጊት «ሕገ-መንግስቱን አስጠብቃለሁ» ከሚል ፖሊስ እና «ሕዝብ መርጦኛል» ከሚል የቀበሌ አመራር የማይጠበቅ ከመሆኑም በላይ ስለ ጉዳዩ በአውራምባ ታይምስ መዘገቡ መበሳጨታቸው «እንዲታወቅ የማይፈለግ ድብቅ ገመና ይኖር ይሆን?» የሚል ጥያቄን ያጭራል::



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ማስታወቂያ




# አፍሪካ እና የልማት...

ራሷን እንዳትረዳ የሚያደርጋት ወይም ራሷን የመርዳት ብቃቷን የሚያቀጭጭ ሱሰኝነት የሚፈጥር ነው:: እርዳታ በተደጋሚ የአንዲትን አገር ዓመታዊ በጀት እና ሙሉውን የካፒታል ወጭ እስከመሸፈን ሄዶ የበጀቱን ትልቁን ድርሻ የሚይዝ ከሆነ ለዜጎች ዴሞክራሲንና ተጠያቂነትን የሚቀጭጭባቸው ነው የሚሆነው:: መንግስቶቻችን ሥልጣን ላይ ያሉት በእኛ ግብር ካልሆነ ስለምን ለእኛ ተጠያቂ እንዲሆኑ እንጠብቃለን? ለሚከፍሏቸው አካት ነው ተጠያቂ የሚሆኑት:: ለዚያም ነው መሪዎቻችን ለአለቆቻቸው የሚጠበቅባቸውን ታማኝነትና ጥሩ ሰዎች መሆናቸውን ለማሳየት ወደ ለንደን፣ ዋሽንግተን፣ ፓሪስ፣ ብራሰልስና ወደ ሌሎች የአፍሪካ አገራት ወዳልሆኑ አገራት የሚጓዙት::

እንደአለመታል፣ ለእኛ ዎቹም ስኬታማ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይህ መከራከሪያ የሚሰራ ነው:: መንገዳችን፣ ት/ቤቶችን ወይም ሆስፒታሎችን መገንባት የማይችሉ መንግስታት፣ ሁሉንም አይነቶች ኢ-ፍትሃዊ ጦርነቶች ለማወጅ ወይም ከፍተኛ ሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን (ካለ አይ.ኤም.ኤፍ./ ዓለም ባንክ) በራሳቸው ዜጎች ላይ ለመፈፀም ዝግጁ፣ ፈቃደኛና አቅሙ ያላቸው ሆነው የራሳቸውን ህዝብ ጤንነት ፣ ትምህት ወደ ውጭው ዓለም እርዳታ ለመጠየቅ መዞራቸው የሞራል መሰረት የሌለው ነው» (ታጁዲን ራህማን፣ 2006)::

«ተኝታኞች፣ ለአይ.ኤም.ኤፍ ያልተንበረከኩ አገራት በይበልጥ ውጤታማ መሆናቸውን አረጋግጠዋል:: ቻይና ቀዳሚ ምሳሌ ነች:: ቻይና ዓለም አቀፍ ኢንቨስተሮችን ለማበረታታት የአይ.ኤም.ኤፍ. ፖሊሲዎችን ተግባሪዊ ብታደርግም፣ በድርጅቱ ከተቀነቀነው እጅግ የተለየ አካሄድ ነበር የተገበረችው:: ቻይና፣ ሕንድና ሲንጋፖር ተቋሙን እምቢኝ ብለዋል፤ ኢኮኖሚያቸውም ጠንካራ ሆኖ ለመቀጠል ችሏል::

የተወሰኑ እንደ ሴራሊዮን፣ ላይቤሪያና ሶማሊያ ያሉ የበርካታ ዓመታት የአይ.ኤም.ኤፍ. እና የዓለም ባንክ ዋነኛ እርዳታ ተቀባዩች የነበሩ የአፍሪካ አገራት፣ በኋላ የወደቁ አገራት ሆነዋል:: እንደውም አንድ የዓለም ባንክ ሪፖርት፣ ሕዝባቸውን ከድህነት ጐትተው ለማውጣት ከፍተኛውን ስራ ያከናወኑ ሶስት አገራት ኩባ፣ ቻይናና ቬየትናም መሆናቸውን አምኖ ተቀብላሏ:: ሆኖም ሪፖርቱ ሳይጠቅስ ያለፈው እነዚህ አገራት ምንም አይነት የአይ.ኤም.ኤፍ እና የዓለም ባንክ እርዳታ ያልተቀበሉ መሆናቸውን ነበር:: በአፍሪካ ውስጥ ራሱ፣ በተሻለ መሰረት ላይ ያለ እየተጠናከረ የሄደ ኢኮኖሚ ያላቸው አገራ በጣም ጥቂት ወይም ምንም የድርጅቶቹን እርዳታ ያልተቀበሉት ናቸው:: ቦትስዋና የድርጅቶቹን እርዳታ አትቀበልም ሆኖም በጥሩ መሰረት ላይ የቆመ ልማት እና መልካም አስተዳደር እየጎለበተባት ያለች አገር ናት:: በመልካም አስተዳደርና በሕግ የበላይነት የዓለም ባንክ የኢካኖሚ ፎረም ሪፖርት ከአፍሪካ አገራት የ21ኛነትን ደረጃ ሰጥቷል:: በጥናቱ መሰረት መጠነ ሰፊ የድርድቶቹን እርዳታ በዓመታት ውስጥ የቀበለችው ቻድ እጅግ አስከፊ ሕዝባዊ ተቋማት ያላት የሚል ገረጃ ተሰጥቷታል:: ናሚቢያም ከሁለቱም እርዳታ ትቀበልም፤ ሆኖም ባላት መልካም አስተዳዳር፣ ጥሩ መሰረተ-ልማት እና ዝቅተኛ የሙስና ደረጃዋ ትታወቃለች (ትሪቮር ጆንስ፣ 2009)::

አብዛኞቹ የአፍሪካ አገራት እርዳታ አያስፈልጋቸውም፤ ሕዝቡን የሚያከብር፣ መልካም አስተዳደር፣ ፍትሃዊነት ያለው ሕግ የሚያሰፍን እና ከግል ጥቅም ባሻገር የህዝብ ጥቅም የሚያስቀድም አግባብነት ያለው መንግስት ነው የሚያስፈልጋቸው፤ ስለምን የዓለም ባንክ ወይም አይ.ኤም.ኤፍ. ወይም ሌላ አካል ለናይጄሪያ እርዳታ ይሰጣል? ናይጄሪያ ከበቂ በላይ ኃብት ቢኖራትም በመንግስት አመራር አስተዳደር የሚገባትን አላገኘችም:: የምዕራብ አገራት አፍሪካን መርዳት በትክክል ከፈለጉ ሌሎች ማድረግ የሚችሏቸው አያሌ ነገሮች አሉ::

አንደኛ:- የምዕራቡ መንግስታትና ተቋማት በእኛ ጉዳት እነርሱ የሚጠቀሙባቸውን ለነፃና ፍትሃዊ ግብይት እንቅፋት የሆኑ ጋሬጣዎችን - አይ.ኤም.ኤፍ/ የዓለም ባንክ፣ የዓለም የንግድ ደርጅት ወይም ሌላ የአገራት ስምምነቶችን - በጠቅላላ ማስወገድ አለባቸው:: ሁለተኛ፣ በሁሉም የአፍሪካ አገራት ያለ ብድር በሙሉ ለሁሉም ሊሰረዝ ይገባል የሚለውን መቀበል አለባቸው:: ሶስተኛ፣ የምዕራብ አገራት አፍሪካና ሌሎች የሶስተኛ ዓለም አገራት በገበያቸው በፍትሃዊነት እንዳይፎካከሩ እያገዷቸው ያሉ ሁሉም የንግድ፣ ቀረጥና ቀረጥ የማያስከፍሉ ጋሬጣዎችን በማስወገድ ያላቸውን ቁርጠኛነት ማሳየት አለባቸው::

አራተኛ፣ ዓለም አቀፉን ድህነትና ከአህጉር አህጉር ካለአንዳች እንቅፋቶች ወይም ጋሬጣዎች የሰው የመንቀሳቀስ ነፃነትን እውን ማድረግን በተመለከተ ግሎባላይዜሽን እንደመጠሪያው በትክክል እውን መሆን አለበት:: ወደአፍሪካ የሚላከው የገንዘብ መጠን በአሁኑ ጊዜ ለእርዳታ ከሚመደበው አጠቃላይ በጀት የበለጠ ሲሆን በአንደንድ አገራት እንደውም ከብሔራዊ በጀት በላይ የሚሆንበትም አጋጣሚ አለ:: እነዚህ በአውሮፓና በአሜሪካ ያሉ ሕገ-ወጥ ስደተኞች ሕጋዊነት ያላቸው ሆነው አገራቸውን ለማልማት ድጋፌቸውን ይስጡ:: እንደዚህ ካልተደረገ ለአፍሪካ የሚሰጠው እርዳታ፣ ሰው እየደበደቡ እንባ መጥረጊያ መሀረብ እንደመስጠት ነው የሚቆጠረው:: አሁን በትክክል በተቆረጠለት ጊዜ ውስጥ ይህን የእርዳታ ጥገኝነትን ለማስወገድ የአፍሪካ መንግስታት የመውጭያ ስትራቴጂ የሚነድፍበት ወቅት ነው::

በረጅም ጊዜ አሉታዊ ውጤት አንፃር እርዳታ ከኤ.አይ.ዲ.ኤስ የባሰ ነው:: ኤ.አይ.ዲ.ኤስን ለመከላከል አግባብነት ያላቸውን አርምጃዎች የማይወስዱ የተወሰኑ ሰዎችን ነው የሚገድለው:: እርዳታ በተፃራሪው የአሁኑንና ቀጣዩን ትውልድ የሚገድል ነው:: በመንግስታት ቁርጠኝነት፣ በዜጐች እና በንግድ እንቅስቃሴዎች ከአገር ውስጥ የሚግኝን ገቢ በይበልጥ ተቀማጭ በማድረግ ተቀማጩን ለበለጠምርታማነት የማዋል ብቃታቸውን በሚያሳጉ ነገሮች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ነው የአንዲትን አገር ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚያስጀምረውና የሚያፈጥነው እንጂ የውጭ እርዳታ አይደለም::

አፍሪካ ለጋሾችን ለማስደሰት ማሻሻያዎችን ከመውሰድ የአገር ውስጥ የስራ ፈጠራንና የግል ሴክተሩን የሚያበረታቱ ማሻሻያዎችን በአስቸኳይ መውሰድ አለበት:: በአፍሪካ ውስጥ ያሉ የቅርብ ልማቶች በአጠቃላይ የሚያሳዩት፣ ሰዎች ከመጠን በላይ በሆነ የመንግስት ብዝበዛ እየተሰቃዩ ያሉ መሆናቸውን ነው:: ለአፍሪካውያን ኑሮ መሻሻል አብዛኞቹ የአፍሪካ መንግስታ ቃል ቢገቡም፣ ሁሉም በመጨረሻ የግል ነፃነቶችን በመንጠቅ ቃላቸውን ያመክናሉ፤ ከዚያም አልፎ በህዝብ ደህንነት ስም ሕዝብን እስከማሸበር ይደርሳሉ:: በመጨረሻ እኛ አፍሪካውያን ለየአገራቶቻችን የሚሰጠው አብዛኛው የውጭ እርዳታ፣ የአይ.ኤም.ኤፍንና የዓለም ባንክን ጨምሮ፣ ቁጥጥርን ማዕከል ያደረገ መሆኑን እንወቀው::

በቅርቡ አንድ አፍሪካዊ የሀርቫርድ እና አክስፎርድ ምሩቅ ኢኮኖሚስት (ከአስር ዓመታት በላይ በዓለም ባንክና በጐልድማን ሳቼስ የሰራ) እና በትውልድ ዛምቢያ የሆነው ዳምቢሳ ሞያ፣ ለአፍሪካ አገራት የገንዘብ ድጋፍ ማድረጊያ አራት አማራጮችን ያቀርባል፤ ከአራቱ አንዳቸውም የልማት እርዳታ አይነት አሉታዊ ውጤቶች የሌሏቸው ናቸው:: እነዚህም:- «የመጀመሪያው፣ የአፍሪካ መንግስታት በዓለም አቀፍ የቦንድ ገበያዎች ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን የኢሲያን እየፈረጠሙ ያሉ ገበያዎችን መከተል አለባቸው፤ ሁለተኛ፣ ቻይናን በመሰረተ-ልማት ላይ ያደረገችውን መጠነ-ሰፊ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ማበረታታት አለባቸው:: . . . ሶስተኛ፣ ለእውነተኛ የግብርና ምርት ነፃ ገበያ ጫናቸውን ማሳደር መቀጠል አለባቸው፤ ማለትም አሜሪካ፣ የአውሮፓ ሕብረትና ጃፓን ለገበሬዎቻቸው የሚከፍሏቸውን የተለያዩ ድጐማዎችን ማስወገድ አለባቸው፣ ይህም የአፍሪካ አገራት ከመጀመሪያ ደረጃ የግብርና ውጤት ኤክስፖርት የሚያገኙትን ገቢ ለማሳደግ ያስችላቸዋል::

አራተኛ፣ የገንዘብ አማራጮችን ማበረታታት አለባቸው፤ በተለይ በእሲያና በላቲን አሜሪካ አገራት እንዳሉት ያሉ የጥቃቅን የፋይናንስ ተቋማት መስፋፋትን ማጠናከር ይጠበቅባቸዋል:: የፔሩያዊውን ኢኮኖሚስት የሆነውን ዲ ሶቶን ምክር መከተል፤ ማለትም ጉስቁልቁል ያሉ ከተማዎች ነዋሪዎች ለመኖሪያ ቤቶቻቸው የባቤትነት ሕጋዊ ሰነድ መስጠት እና ቤቶቹንም እንደመያዥ መጠቀም እዲቻላቸው ማድረግ::»

የአፍሪካ አገራት እና መንግስታት፣ የዚህን ታላቅ አፍሪካዊ ኢኮኖሚስት ጥበብ ይተገብሩ ይሆን? ያን በጊዜ ሂደት የምናየው ይሆናል::

**/ተስፋዬ ሀቢሶ፣ ቀደም ሲል በደቡብ አፍሪካና በዩጋንዳ የኢትዮጵያ አምባሳደር ነበሩ/**

# የተቋማት የገለልተኝነት...

«እንቅልፍና እድሜ» በሚለው መጽሐፍ ውስጥ የላይኛውን ታሪክ የሚያጠናክር አንድ ወግ አለ፤ ካሱ የተባለው መምህር «የመተማ ጦርነትና የአፄ ዩሃንስ ዕጣ» የሚል ጥናታዊ ፅሁፍ በመድረክ ላይ ያቀርባል:: በምሽት የቴሌቪዥን የዜና እወጃ ግን ቴሌቪዥኑ የመምህር ካሱን ምስል እያሳየ «በኢትዮጵያ ዘንድሮ የተካሄደው ምርጫ ፍትሃዊና እንከን የለሽ መሆኑን አንድ ምሁር ገለፁ::» የሚል ሀተታ ያቀርባል:: ካሱ በድንጋጤ በድን ይሆናል:: ተሳስተው ነው፣ ማስተካከያ ያደርጋሉ ብሎ ቢጠብቅም ምንም ነገር የለም:: ይህን ጭንቀቱን ለወዳጁ ሲያዋየው «እንዲህ አይነት ስህተት ይፈጠራል፤ አርፈህ ስራህን ቀጥል» ይለዋል:: ወደ ቴሌቪዥን ጣቢያው ሄዶ «ይታረምልኝ፣ እኔ አላልኩም» ለማለት ወኔውን ያጣል:: በቀረበው ዘገባና በወቅቱ የፖለቲካ ውጥረት ምክንያት እንቅልፍና ረፍት ይሸሹታል:: በዚህ ሁኔታ ከእለት እለት ሽብር በሽብር ሲሆን እናየዋለን:: የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን የት ላይ እንዳሉና ዜጐችም ምን ጉድጓድ ላይ እንደቆምን የሚያሳይ ወግ ይመስለኛል::

በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ የማያባራ ትችት ይቀርባል:: የምርጫ ቦርዱ በተቃዋሚዎች ታስሷል፤ የመንግስት ንብረት ለፓርቲ አገልግሎት እየዋለ ነው ተብሏል:: የፀጥታ ኃይሉም ተመሳሳይ ጥያቄን ያስተናግዳል፤ ፍርድ ቤቶችም እንኳ ከዚህ ጥርጣሬ ውጪ መሆን አልቻሉም:: የግሉ ሚዲያም የገዥውን ፓርቲ ሃሳብ ማስተናገድ ተስኖታል የሚል ቅሬታ ይቀርብበታል:: በቅርቡ ደግሞ ሌላ ዜና ሰምተናል:: አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ የሚደርሱን የፖስታ መልዕክቶች ተቀደው ይታዩብኛል ብሏል:: ይህ የተቋማት የገለልተኝነት ጥያቄ ከቀን ቀን እየተሻሻለ መሄድ ሲገባው እየባሰ መጥቷል ማለት ነው::

እነዚህ መሰረታዊ የሕዝብ ተቋማትስ በዚህ አይነቱ የመታመን ጥያቄ ላይ ወድቀው ዴሞክራሲን መገንባት ምን ማለት ይሆን? «ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ» አይሆንም? እያንዳንዱ ዜጋ በተቋማቱ የማይተማመን፣ ፍትሃዊ እና ብቁ አገግሎት ይሰጡኛል ብሎ ካላመነ ተቋማቱን እንዴት ሊገነባቸው፣ እንዴት ሊጠብቃቸውና ወደተሻለ ደረጃ ሊያሸጋግራቸው ይችላል? የፖሊስ አባላት ለሕገ መንግስቱ ሳይሆን ለገዢው አካል የወገኑ ናቸው ካልኩ ተቋሙን ልፈራው እንጂ ልመካበት አልችልም:: ፍርድ ቤቶች የተወሰነ ቡድንን ልዩ ጥቅም ያራምዳሉ፣ አድሎአዊ ናቸው የሚል እምነት ከያዝኩ በአገሬ የመኖር ሕልውናዬም አደጋ ላይ ያለ ነው ማለት ነው:: የምርጫ ቦርዱ ገለልተኝነት ካጠያየቀን በምርጫ የመሳተፉ ትርጉም ምንድን ነው? የምርጫ ቦርድ ገለልተኛ ካልሆነ ቀዳሚ አጀንዳ የሚሆነው የተቋሙን ነፃነትና ገለልተኝነት የማስከበር ትግል ነው:: የታመመ አካልን ይዞ መንገድ መግባት አያዛልቅም::

«ተቋማት ነፃ አይደሉም» የሚል አመለካከት መኖሩ በራሱ ተቋማት ለዴሞክራሲና ለአገር ልማት የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ የሚያቀጭጭ ይሆናል:: ነፃ አለመሆናቸው ደግም እጅግ የባሰው አደጋ ነው:: የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣን የፖስታ መልዕክቶች የመቀደድ ዜና ስሰማ በበኩሌ ደንግጫለሁ:: ድንጋጤዬ ለደቂቃዎች ከቆየ በኋላም ወደ ሀዘን ስሜት አሸጋግሮኝ ሄዷል:: አንድ ሰው ገላውን ሲታጠብ በበር ቀዳዳ አጮልቆ የሚያየው ሰው ካለ ያ ሰው የአዕምሮ ችግር እንዳለበት ብዙዎቻችን እናምናለን:: የሌላውን ሰው የፖስታ መልዕክት ሰርቆ ማየትስ ከዚህ የተለየ ምን መጠሪያ ይኖረዋል? በእርግጥ የመንግስት እጁ ረጅም ነው:: ይህ ባለጌ እጅ ግን የማነው? እኔ በበኩሌ ይህ እጅ የመንግስት እጅ እንዳይሆን እመኛለሁ:: ተግባሩም በባህልም ነውር፣ በሕግም ቢሆን ወንጀል ነው:: እንግዲህ ከተቋማት የገለልተኝነት ጥያቄ ውጪ የሆነ ማን ቀረን ይባላል?

ባለፈው ሳምንት ፒያሳ አካባቢ ነበርኩ:: አንድ አሽከርካሪ የትራፊክ ፖሊስ ይዞት የያዘው ፖሊስ ክስ እንዳይጽፍበት ይለምነዋል:: ትራፊክ ፖሊሲ ሊፅፍ ካለበት ቀና ብሎ፣ «ምነው ልመና አበዛህ! ከጐጃም ነው እንዴ የመጣኸው?» ሲል በቁጣ አፈጠጠበት:: እኔ ደነገጥኩ:: የትራፊክ ፖሊስ ተቋም እንዲህ አይነት አቋም አለው ብዬ ፈጽሞ አላምንም:: ሆኖም በውስጡ ያሉት ሰዎች ተቋሙን የሚወክሉ መሆናቸው እሙን ነው:: ትራፊክ ፖሊሱ እንዲህ ያለውን ነውር በአደባባይ ለመናገር ያበቃው ድፍረት ከየት የመጣ ይሆን? የሚል ጥያቄ ግን አለኝ:: በበኩሌ የዚያ አካባቢ ተወላጅ አይደለሁም:: ይህን ነውር ለመቃወም ግን ሰው መሆን ብቻ ይበቃኝ ነበር:: አልፌ ከሄድኩ በኋላ እስካአሁን ድረስ ለምን አልተቃወምኩም ከሚል የሕሊና ክስ መዳን ግን አልቻልኩም:: ማርቲን ኒምሌር የተባሉና በናዚዎች የተሰቃዩ ካህን እንዲህ አሉ:- «መጀመሪያ ናዚዎች አይሁዶችን አሳደዱ፤ እኔ ግን አይሁድ አልነበረኩምና አልተቃወምኩም:: ከዚያም ካቶሊኮችን አሳደዱ፤ እኔም ካቶሊክ አልነበረኩምና ተቃውሞ አላሰማሁም:: ቀጥሎም የሰራተኛ ማሕበር መሪዎችን አሳደዱ፤ ይህም አይመለከተኝም ነበርና አልተቃወምኩም:: ቀጥሎም ወደ እኔ መጡ:: ግን ተቃውሞ የሚያቀርብ የተረፈ ሰው አልነበረም::» ካህኑ እውነት አላቸው፤ ክፋትን አለመቃወም ክፋትን መተባበር ነው:: ፍትህ ፍትህን፣ ግፍም ግፍን ይወልዳል::

በአሁኑ ጊዜ ከታችኛው የመንግስት አካል (ቀበሌ) አንስቶ እስከ ከፍተኛው የሚኒስቴር መ/ቤት ቢሮዎች ድረስ በሚያማምሩ የሥነ-ምግባር መርሆች አሸብርቀዋል:: እሰየው የሚያሰኝ ነው፤ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ ቅንነት፣ አለማዳላት እንዴት ደስ የሚሉ ቅዱስ ሀሳባች ናቸው: እኒህ የሥነ-ምግባር መርሆዎች ግን የግድግዳ ጌጥ ብቻ መሆን የለባቸውም:: በየግድግዳዎቹ ላይ የተለጠፈውና በየጠረጴዛው ላይ የሚሰራው መስማማት መቻል አለባቸው:: ግልጽነት የሚል መርህ ለጥሮ መረጃ የሚሰጥ አካል ከጠፋ፤ ተጠያቂነት የሚል መፈክር ሰቅሎ አቤት የሚሉበት ከሌለ ይህም ቢሆን በሰው ቁስል እንጨት መስደድ ነው:: በሌላም በኩል ዜጐች «ስልኬ ይጠለፋል፤ ፖስታዬ ይበረበራል፤ በፀጥታ ኃይሎች እሰለላለሁ . . .» የሚል ስጋት ካደረባቸው፣ ዜጐችና ተቋማቱ አጋር ከመሆን ይልቅ እንደክፉ ባላንጣ ሚተያዩ ይሆናሉ::

የዋናው ፖስታ ቤት የፖስታ አገልግሎት ኃላፊ ለጋዜጣው ሲናገሩ፣ «በፖስታ ሳጥኑ ላይ ልዩ ክትትል እናደርጋለን» ማለታቸው ደስ አሰኝቶኝ ነበር:: ለውጭዎቹ ሰዎች (ለፈረንጆቹ) በሰጡት ምላሽ ግን፣ «ስለጉዳዩ የማውቀው ነገር የለም» ብለዋል:: በአንድ እራስ ሁለት ምላስ:: ካሉብን በሽታዎች መካከል አንድም ይሄ ነው:: ለሕዝባችን የምናወራው ሌላ፣ ለውጭዎቹ የምንላቸው ሌላ::

ለዘመናት መልካም አገልግለት ሲሰጥ የኖረው የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት በዚህ ብልሹ ተግባር መልካም ስሙ መነሳቱ ለቅን ሰራተኞቹም ሆነ ለደንበኞቹ የሚያሳዝን ነው:: የተቋሙ ኃላፊዎችም ሆኑ የመንግስት ባለሥልጣናት በችግሩ ላይ አፋጣኝ እርምት እንደሚያደርጉ ተስፋ አለኝ:: የዚህ ጽሑፍ መሰረታዊ አላማም በተለያዩ ተቋማት ላይ የሚታየው የእምነት ማጣት አሳሳቢ ነው፤ እነዚህን የአገር ተቋማት እናድን፤ እንክብካቤ፣ ፍትሃዊና ነፃ አገልግሎት ይሰጡን ለማለት ነው::

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ::

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com









ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com